# የቅዱሳን በአየር መነጠቅ

(...ጌታን በአየር ለመቀበል ...በደመና እንነጠቃለን።)

መጋቢ ተኩ ከበደ

የመጀመሪያ እትም 1999 ዓ.ም.

የመጀመሪያው ዕትም ለናዝሬት ምሥራቅ
መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠ

ይህንን መፅሐፍ ያለ ደራሲው ፈቃድ
ማባዛት ወይም ማሣተም
በሕግ የተከለከለ ነው።

Pastor Teku Kebede
All Rights Resereved
Printed In Ethiopia
© 2007

# ምስጋና

ካለመኖር ወደ መኖር ካለማወቅ ወደ ማወቅ፣ ከማወቅ ወደ ማሳወቅ፣ በንግግር፣ በአኗኗር ዕውነትን ከመግለጥ ወደ መፃፍ ያደረሰኝን እውነተኛውን አባቴን፣ አምላኬም፣ ጌታዬም የብርታቴም ምንጭ የሆነውን ሁሉን አዋቂውን እግዚአብሔርን እጅግ አድርጌ አመሰግነዋለሁ::

በተጨማሪም ለዚህ መጽሐፍ መገኘት ከ1980ዎቹ ጀምሮ ጽሑፉን በመተየብና በኮምፒውተር አዘጋጅቶ የስቀማ ሥራን በመስራት፣ ከ20 ዓመታት በላይ በፀሎትና በሐሳብ የረዳችኝን ከማይሳሳተው የጋብቻና የህይወት መሃንዲስ የተቀበልኳትን ውድ ባለቤቴን እህት ምሥራቅ አበበን አመሰግናለሁ:: እንዲሁም:

1. በጽህፈት ሥራ የረዱኝን የደቡብ አጥቢያ መሠረተ ክርስቶስ ቤ/ክ ፀሐፊዎች እህት መሠረት አያሌውን እና እህት ገዳምነሽ ወርቁን
2. በ1983, 1984 ዓ.ም በሾኔ አምቡርሴ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያንና በ1980ዎቹ አጋማሽ በቃለ ህይወት ቤተ ክርስቲያናት በተካሄደው ኮንፍራንስ ስለምፅዐት መጽሐፍ እንድፅፍና ስአገልግሎቴም አጥብቃችሁ በጉባኤ የፀለያችሁልኝን
3. በነገረ ፍጻሜ ትምህርት ተጋብዤ ባገለገልኩባቸው አጥቢያዎች በፀሎት፣ በምክር፣ ማቴሪያል በመስጠትና በማደፋፈር የፀለያችሁልኝን
4. «ቶሎ ቶሎ ባታገለግልበት ይህ ፀጋ ይወስድብሃል በርታ » በማለት በምክር ያነቃችኝን ወንጌላዊት ጥሩነሽ ይመር/ቺካጎ-አሜሪካ/.
5. ይህንን ጽሑፍ በማየት በአርትኦት ስራ የረዱኝን ስማቸው በዚህ መጽሐፍ ላይ የተጠቀሰውን ውድ ወገኖች
6. መጽሐፉን ለሕትመት ያበቁትን የናዝሬት ምስራቅ መሰረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ አገልጋዮችና ምዕመናንን

7. ለእኔ መገኘትና መበረታታት፣ ዕድገትና መንፈሳዊ መነቃቃት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለመሩኝ፣ ለፀለዩልኝና ላበረታቱኝ የመ/ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አመራር፣ አገልጋዮችና አጥቢያዎች በሙሉ
8. ይህንን የጌታ ምፅዐት ትምህርት እንዳስተላልፍ የመጽሔት፣ ጋዜጣ፣ የሬድዮ/ህያው ተስፋ/ የጉባኤ መድረክ ላመቻቻችሁልኝ ቤተዕምነቶች፣ /አጥቢያዎች/፣ ኅብረቶች፣ ለጋስ ድርጅቶችና በሩቅና በቅርብ ላላችሁ ጓደኞቼ በሙሉ
9. ለሰዓሊ ካሌብ በለጠ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

የሥራው ባለቤት እግዚአብሔር ይባርካችሁ

መጋቢ ተኩ ከበደ



# መግቢያ

ተኩላዎች በሚኖሩበት ጫካ ረፍራፊ ረሃብ ይገባል:: የጓደኞቻቸውን ዕልቂት የተረዱ ሁለት ጓደኛሞች ተኩላዎች ተቀምጠው በጉዳዩ ላይ ጥልቅ ምክር ያካሂዳሉ:: ከብዙ ውይይት በኋላ ባገኙት መላ ተስማምተው ያንን አካባቢ ጥለው ምግብ ያለበት ፍለጋ ወደ ሌላ ጫካ ይጓዛሉ:: ጫካው ውስጥ እንደገቡ ሁለቱም ሳይራራቁ ምግብ ፍለጋውን ይያያዙታል:: ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሁለቱም የሚፈልጉትን አግኝተው በተራበ ጉልበት ሆዳቸው እስኪወጠር በልተው ይጠግባሉ:: በመቀጠልም ሁለቱም ጋደም ጋደም ይላሉ:: ሁለቱ እኩል ቢጠግቡም አተኛኘታቸው ግን ለየት ያለ ነበር:: አንደኛው ተኩላ እግሮቹን ወደ ላይ ገልብጦ ሲተኛ ሌላኛው ግን ነገር አዋቂ ስለነበር ጋደም ባለበት ቦታ አካባቢውን እየቃኘ ተኝቶ ነበር::

እነዚህ ሁለት ተኩላዎች በልተው፣ ጠጥተውና ጠግበው በተኙበት አካባቢ ግን ሌላ ትዕይንት ይካሄድ ነበር:: ይኼውም አንድ በጣም የተራበ ነብር ምግብ እየፈለገ ወደ ተኩላዎች መቅረቡ ነበር:: ይህ ነብር ወደ ተኩላዎቹ በቀረበ ጊዜ አስቀድሞ የተመለከተው ጋደም ቢልም እንቅልፍ ያልወሰደውን ተኩላ ነበር:: ልክ ነብሩ ተኩላውን ሲያየው ተኩላውም ነብሩን ተመለከተው: ነብሩ አቅም ተኩላው ደግሞ ልብ በማጣታቸው ሁለቱም በፍርሃት ተፋጠጡ፣ በዚህ ፍርሀት ውስጥ እያሉ ሁለቱም በቋንቋቸው ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ፤ ነብሩ አምላኬ ሆይ! እኔ በረሃብ ልሞት ነውና ይህንን ተኩላ አብላኝ! አብላኝ! አብላኝ! በማለት ሲጸልይ ተኩላው ደግሞ እግዚአብሔር ሆይ! እኔ ፈርቻለሁና ከዚህ ከነብር አውጣኝ! አውጣኝ! አውጣኝ! በማለት ጸለየ:: ሁለቱም በዚህ ሁኔታ ተፋጥጠው ባሉበት እግዚአብሔር ይፀልይ ለነበረው ነብር ዞር ብሎ እንዲያይ ይነግረዋል:: ነብሩም ዞር ብሎ ሲያይ ሁለተኛው ተኩላ ሙሉ በሙሉ ተኝቶ ያገኘዋል:: ነብሩም በተኛው ተኩላ ላይ በመዝለል ይበላዋል::

ይህ ታሪክ ምሳሌያዊ አነጋገር አለው ይኸውም ለውጣኝ ያለ ወጣ፣ ኣገባኝ ያለ በላ፣ ዝም ያለ ተበላ የሚል ነው::

ከላይ ለተጠቀሰው ታሪካዊ ሃተታ የተለያዩ አመለካከቶች ቢሰነዘሩም አንድን ትልቅ ቁም ነገር እንደሚይዝ ማመልከት እፈልጋለሁ:: ይህ ዘመን የምቾት ዘመን ነው:: ሰው ሁሉ ምቾት ውስጥ(Comfort Zone) ለመግባት ዋጋ በመክፈል ላይ ይገኛል:: ይህም ከችግር ለመሸሽ ሲሆን ይችላል:: ሰው ከችግር ሲሸሽ ዓላማው ይብዛም ይነስ ምቾት ውስጥ ለመግባት ነው:: ምቾት ደግሞ የራሱ አሉታዊ /ጥሩ ያልሆነ/ ተፅዕኖ አለው:: ለምሳሌ ሰው ሲመቸው እንደ ጠቢቡ ሰለሞን ያመቻቸለትን ፈጣሪ ማየት ሊያቅተው ይችላል፣ ሰው ሲመቸው የበለጠ ምቾትን ይከተላል:: ሲመቸውም መልከ ብዙ ተከታዮች፣ ይከብቡትና አጀንዳዎችን ያበዙበታል፤ ያበዙለታል:: በዚህም ምክንያት ልቡ ይከብድና ከፈጣሪው በመለየት ፈተና ውስጥ ይወድቃል::

አሁን ያለንበት ጊዜ አብዛኛው ሰው ከቴክኖሎጂው ጋር ለመራመድ ደፋ ቀና የሚልበት ወቅት ነው:: በኤኮኖሚ በፖሊተካ በማሕበራዊው አኗኗር ከፍተኛ ውድድር እየተካሄደ ያለበት ጊዜ ነው:: በመጠን የመኖር ምርጫ እንደ ድህነትና ውርደት የሚቆጠር ስለሆነ እንደ ሌላው ወይም ከሌላው ሰው በላይ አልፎ ወይም ተመሳስሎ ለመገኘት ሁሉም ነገር ጥረት ጠያቂ የሆነበት ዘመን ነው:: ከዚህም የተነሳ በሉቃ 21:34 እንደተጠቀሰው በተወሰኑት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የልብ መከበድ ይታያል::ልብ ደግሞ ሲከብድ አቅጣጫው /ዝንባሌው/ ወደ ምድራዊ ነገር ይሆናል::

ጌታ ኢየሱስ ሲያስተምር የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ ሁለት ሰዎች በአንድ እርሻና ወፍጮ እንደሚሆኑ ሆኖም ከሁለቱ አንደኛው ብቻ እንደሚወሰድ ተናግሮአል:: ማቴ24:40-41:: የአንደኛው/ዋ/ አለመወሰድ ከእምነት ብልሽት ወይም ማነስና መጥፋት ጋር የተያያዘ መሆኑን ያሳያል::



መቼም ክርስቶስ ሲመጣ ሲል እርሱን እየጠበቁ ከእርሱ ጋር በመስማማት መሄድ አለመቻል እጅግ አሳፋሪ ነው:: በአሁኑ ጊዜ ከእግዚአብሔር በረከትን የሚካፈሉ ብዙ ሰዎች አሉ:: በአንጻሩ ደግሞ ከበረከቱ የራቁም አሉ:: ሰዎችን ከጊዚአዊውና ዘላለማዊው የጌታ በረከቶች እንዲርቁ ከሚያደርጋቸው ዋነኛ ምክንያቶች አንዱ ስለ ተገለጠው የእግዚአብሔር ዕውነት ማወቅ አለመፈለግ ወይም ካወቁ በኋላ በእምነቱ ተሳታፊ መሆንን አለመፈለግ ናቸው::

አንዳንድ ክርስቲያኖች በዕምነታቸው ጥብቅ መሆንን አይፈልጉም:: የማይፈልጉበትም ምክንያቶች ነፃነታቸውን የሚያጡ፣ በጓደኞች የሚናቁ/የሚገፉ/፣ ተቀባይነትን የሚያጡ፣ ችግር የሚገጥማቸው ወዘተ መስሎ ስለሚታያቸው ነው:: ሆኖም ግን የሚያዋጣው ቢከብድም በአፍ ጣፍጦ በሆድ/በኑሮ/ መራራ ቢሆንም /ራዕይ10:9/ ዕውነትን መፈለግና ማግኘት ከዚያም ከዕውነት ጋር መጣበቅ ነው:: ምክንያቱም ዕውነት ባለበት መሄጃው መንገድ ይታወቃል፣ ያም መንገድ ጌታ ኢየሱስና የላከው መንፈስ ቅዱስ ናቸው:: ዕውነትና መንገድ ባለበት ህያወት፣ ህይወትም ባለበት ብርሃን፣ ብርሃንም ባለበት ቅድስና ቅድስናም ባለበት ነፃ መውጣት አለ:: ዩሐ14:3 ፣ 1:3 17:17:: ኑሮን በዚህ ዓይነት መንገድ ካላስተካከሉት በስተቀር የአካባቢውን ሁኔታ መቃኘት ተስኖት በእንቅልፍ ተውጦ የነበረው ተኩላ የደረሰበት አደጋ እኛም ላይ ሊደርስ ይችላል:: ከዚህ አውጣኝ ማለት ትልቅ ጸሎት ነው:: ጥንቃቄ ያልተደረገበት ምኞትና ምቾት ፍለጋ ሩጫ በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ ከፍተኛ መንፈሳዊ እንቅልፍን ያመጣል::

ስለሆነም ይህ መጽሐፍ ክርስቶስ ኢየሱስ በራሱና በታማኝ አገልጋዮቹ የገለጠልንን የቅዱሳን ከመጨረሻ ዋና ዋና ተስፋዎች ውስጥ አንዱ ስለሆነው ስለ ቅዱሳን መነጠቅ /ስለ አሁኗ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ/ እርግጠኛነት ለማሳወቅ የተፃፈ ነው:: መጽሐፉ አስራ ሁለት ዋና ዋናና ተጨማሪ ንዑሳን ክፍሎች አሉት::

ክፍል አንድ ስለ መነጠቅ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምን እንደተፃፈ ይገልጽልናል::
ክፍል ሁለት ስለ መነጠቅ ትርጉምና ምንነት ያትታል:: ክፍል ሦስት ለብዙ አማኞች ልዩነቱን ለማየት አስቸጋሪ ስለሆነባቸው በመነጠቅና በጌታ ዳግም ምፅዓት መሃከል ያለውን ልዩነት ያሳያል:: ክፍል አራት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተጠቀሱት የተለያዩ የመነጠቅ ዓይነቶችና በምን ጊዜ እንደሚሆኑ ይገልፃል:: ክፍል አምስት ይህ መነጠቅ ከመከራው በፊትና በኋላ ወይስ በመሃል ላይ በየትኛው ጊዜ እንደሚፈፀም ያብራራል::

ክፍል ስድስትና ሰባት - መነጠቅ ከመከራው በፊት ስለመሆኑ የቀረቡ ማስረጃዎችና በመነጠቅ ጊዜ በዚህ ምድር ስለሚከናወኑት ሁነቶች ያብራራል:: ክፍል ስምንት - እግዚአብሔር መነጠቅን ስላዘጋጀበት ምክንያቶችና ዓላማዎች ይዘረዝራል:: ክፍል ዘጠኝ ከመነጠቅ በኋላ በሰማይና በምድር ስለሚፈፀሙ ትዕይንቶች እንዲሁም በክፍል አስርና አስራ አንድ በወቅቱ  ያለነው ለመነጠቅ የምንፈልግ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያናት ለመነጠቅ ምን ማሟላት እንዳለብንና ይህንኑ መነጠቅ ለምን መናፈቅና ማስቸኮል እንዳለብን ያትታል:: በመጨረሻም በክፍል አስራ ሁለት በክርስቶስ አማኝ ነኝ/ነን/ የሚሉ ስለ መነጠቅ በተሳሳተ መንገድ ከመረዳት ወይም ካለማወቅ የተነሳ አሳዛኝ ነገር እንዳይደርስባቸው ምን ዓይነት ልምምዶች ላይ ማትኮር እንዳለባቸው ይገልፃል::

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ በቅድሚያ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን በቃሉ ውስጥ ስለ መነጠቅ ምን እንደተጻፈ ለማሳወቅና የመነጠቁን ቀን በማስቸኮል እንዲጠብቁ ማበረታታትና ማነሳሳት ነው፤ ሆኖም በማጠቃለያው እንደተጠቀሰው የመነጠቅን ትክክለኛ ቀን በሚመለከት ከሚፈጠረውም ቀውስ ኣማኙ ራሱን እንዲጠብቅ ለማዘጋጀት ነው:: በተጨማሪም ይህ የመነጠቅ ዕድል ሊያመልጣቸው ላሉት ከቤተ ክርስቲያን



ለራቁ ከሃዲዎችና ጌታን ሳልተቀበሉ ሁሉ እውነቱን ለማመልከት እንዲቻል ለቅዱሳን ሁሉ መገልገያንና ማገልገያ መሣሪያን ለማስጨበጥ ነው::

... በረኛው እንዲተጋ አዘዘ ማር 14፥34

መጋቢ ተኩ ከበደ

# የቅዱሳን በአየር መነጠቅ

ማውጫ


- ምስጋና .................................................................I
- መግቢያ ...............................................................III

ክፍል አንድ: መነጠቅ በመጽሐፍ ቅዱስ ..........................................1
ክፍል ሁለት: የመነጠቅ ፍቺ ...........................................................4
ክፍል ሦስት: የቤተ ክርስቲያን መነጠቅና የዳግም ምፅዓት ልዩነት....6
ክፍል አራት: የመነጠቅ ዓይነቶች ..................................................9
ክፍል አምስት: የመነጠቅ ጊዜ አመለካከቶች (ቅድመ መከራ፣ መንፈቀ-መከራና ድህረ-መከራ) ..................................17
ክፍል ስድስት: የቅድመ መከራ መነጠቅ ማስረጃዎች (መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን ይኖራል?) .......................................23
ክፍል ሰባት: ትዕይንተ-መነጠቅ ..................................................70
ክፍል ስምንት: የመነጠቅ ዓላማዎች (እግዚአብሔር የመነጠቅን ሥርዐት ለምን አዘጋጀ?) ...............................................84
ክፍል ዘጠኝ: ድህረ-መነጠቅ ሁነቶች (ከመነጠቅ በኋላ በሰማይና፣ በምድር ምን ይከናወናል?) .........................................92
ክፍል አስር: ለመነጠቅ መሟላት ያለባቸው ልምምዶች(ዝግጅቶች).100
ክፍል አስራ-አንድ: መነጠቅን ለምን መናፈቅ ይኖርብናል? ......................113
ክፍል አስራ-ሁለት: ማስጠንቀቂያ ..................................................121
ማጠቃለያ .................................................................152
ልዩ ማስታወሻ ..........................................................153
ሙዳየ-ቃላት .............................................................154
ምህጻረ-ቃላት ...........................................................167
መዘክረ-መጻህፍት ......................................................167




# ክፍል አንድ

## ስለመነጠቅ የሚያመለክቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች

| ተ.ቁ. | የሚገኙበት ቦታ | የተጠቀሰው ዓረፍተ ነገር |
|---|---|---|
| 1. | ሉቃ. 21:36 | እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ ስትፀለዩ ሁልጊዜ ትጉ:: |
| 2. | ዮሐ. 14:3 | ሔጄም ሥፍራ ባዘጋጅላችሁ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ:: |
| 3. | ኤፌ. 5:27 | እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንደዚህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ |
| 4. | 1ኛቆሮ.15:51-53 | እነሆ አንድ ሚስጢር እነግራችኋለሁ ... የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበተ ዓይን እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሳሉ እኛም እንለወጣለን:: |
| 5. | ፊልጵ. 3:21 | ... የተዋረደው ሥጋችንን ...ይለውጣል.. 2ኛቆሮ. 5:1-9 ... በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሰራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሰራ ሕንጻ እንዳለን እናውቃለንና ከሰማይም የሚሆነውን መኖሪያችንን እንድንለብስ እንናፍቃለንና:: ...በሥጋ ስናድር... ከሥጋ ተለይተን... |

| | | |
|---|---|---|
| 6. | 1ኛተሰ. 4:13-17... | በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሳሉ ከዚያም በኋላ እኛ ህያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታን በአየር ለቋቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና <u>እንነጠቃለን</u>:: |
| 7. | 2ኛተሰ. 2:1-7 | ... ወደ እርሱ <u>ስለመሰብሰባችን</u> ... ብቻ ከመንገድ እስ<u>ኪወገድ</u> ድረስ አሁን የሚከለክል አለ፤ |
| 8. | ቆላ. 3:4 | ... በዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር <u>በክብር ትገለጣላችሁ</u>:: |
| 9 | 1ኛዮሐ. 3:2 | ... ዳሩ ግን ቢገለጥ (እኛነታችን) እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን:: |

ከላይ የተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጎች የተለያዩ ቢሆኑም ስርወ-ግንዳቸው ሲመረመር በቀጥታ መነጠቅን ያመለክታሉ::

በሉቃስ 21:36 ያለው "*<u>ለማምለጥ</u>*" የተሰኘው ቃል የሚያመለክተው በመጨረሻው ዘመን ያሉ ቅዱሳን በምዕራፉ ከተጠቀሱት ቁጣዎች ማምለጥ የሚችሉት በመነጠቅ መሆኑን ነው:: "*<u>ማምለጥ</u>*" የሚለው ቃል ራሱ የሚያመለክተው ከአንድ ሁኔታ መሰወር፣ ለሁኔታው አለመጋለጥን፣ መሸፈንን ነው:: በሉቃስ 21 የተጠቀሱት ጌታ ኢየሱስ በመጨረሻው ዘመን እንደሚሆኑ የገለጻቸው ሰውን የሚያስጨንቁ ሁኔታዎችን ላለማየት የሚቻለው በመነጠቅ ነው::

በዮሐንስ 14፣1-3 ደግሞ ጌታ ኢየሱስ "*<u>እወስዳችኋለሁ</u>*" ሲል ቅዱሳን ከዚህ ዓለም ወደ ተዘጋጀላቸው ሰማያዊ ስፍራ የሚሸጋገሩበትን መንገድ ያመለክታል:: ይህም መንገድ መነጠቅ ነው:: ጳውሎስ ለኤፌሶን ቅዱሳን ሲጽፍ ጌታ ኢየሱስ ያለ ነውር የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ የሚያቀርበው



በመነጠቅ እንደሆነ ያመለክታል:: "<u>እንዲያቀርብ</u>" የሚለው ቃል በምድር ያሉትን ቅዱሳን ወደ ሰማይ ማጓጓዝን (ማንቀሳቀስን) ያመለክታል:: ይህም መነጠቅን ይጠቁማል::

በ1ኛቆሮ. 15:51-53 ባለው ክፍል "*እንለወጣለን*" "*ይነሳሉ*" የሚሉት ቃላት የኋለኛው መለከት በሚነፋበት ጊዜ ቅዱሳን የሚያልፉበትን ሁኔታ ያመለክታል:: ትንሳኤ በሚሆንበት ጊዜ ቅዱሳን በሙሉ በቅጽበተ ዓይን ተለውጠው ጉዞ ይጀምራሉ:: ትንሳኤ ሆነ ማለት መለወጥ ሆነ ማለት ነው:: አላሶ ወይም አላሶሜታ የሚለው የግሪኩ ***የእንለወጣለን*** አቻ ቃል የሚያመለክተው ከአንድ ሁኔታና ማንነት ወደ ሌላ ማንነት መቀየርን ወይም መግባትን ነው::

በ2ኛቆሮ. 5:1-9 የተጠቀሱትም ሐረጎች ማለትም "<u>ከእግዚአብሔር የተሰራ ህንጻ፣ "መኖሪያችንን እንድለብስ</u>" የተሰኙት ቃላት ሰው ከዚህ ከሚችና በስባሽ አካል ከተለየ በኋላ የሚጐናጸፈውን ዘላለማዊ ሰውነት ያመለክታል:: ይህም ሰውነት በመነጠቅ ጊዜ የሚገኝ ነው::

ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ቅዱሳን "<u>ስለመሰብሰባችን</u>" በማለት የተጠቀመው ቃል የሚገልጸው ቅዱሳን ወደ ጌታ የሚሰበሰቡት በመነጠቅ እንደሆነ ለማመልከት ነው:: የእውነተኛው የክርስትና ሕይወት የእድገት መጨረሻ ጌታ ኢየሱስ ነው:: እድገታችንም ወደ ክርስቶስ ሙላት ነው:: ጌታ ኢየሱስ ሁለንተናው ፍጹምና ያለ ኃጢአት ነው:: የእኛም የእድገት አቅጣጫ ክርስቶስን ወደ መምሰል ያተኩራል:: አዲሱን አካላችንን ስንለብስ ማንነታችን ይገለጣል:: ይህም ሰውነታችን የክርስቶስን አካል የሚለብሰው በመነጠቅ ወደ እርሱ ስንደርስ ነው::

# ክፍል ሁለት

## የመነጠቅ ፍቺ

የነገር ብልሽት ወይም ፈር ይዞ መሔድ መሠረቱ ለነገሩ የተሰጠው ፍቺ ወይም ትርጉም ነው:: ትክክለኛ የሆነ ፍቺ (ትርጉም) የተሰጠው ነገር አገልግሎቱም ያንኑ ያህል ጥራትና አስተማማኝነት ያለው ይሆናል:: እውነተኝነት በሌለው መንገድ የተብራራ ጉዳይ ደግሞ ያንኑ ያህል አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሳ ረብ የለሽ ይሆናል:: ስለዚህ ትክክለኛ የሆነ አመለካከትን ለመያዝ የመነጠቅን ፍቺ ማየቱ መልከም ነው:: ..*መነጠቅ*.. የሚለውን ቃል ትክክለኛ ፍቺ/ትርጉም በሚከተለው መንገድ በዝርዝር እንመለከታለን::

### 2.1. የጥሬ ቃሉ ትርጉም

..መነጠቅ.. የሚለው የግሪኩ ቃል ..ሃርፓጂስምታ.. ሲሆን የላቲኑ ደግሞ ..ራፔመር.. ነው ፍቺውም ..ወደላይ መወሰድ..፣ ..መወገድ..፤ ..መነሳት.. ማለት ነው:: ወይም ደግሞ ወደ ግራ ወይም ወደ ቀኝ ዞር ማለት ሳይሆን ከታችኛው ወደ ላይኛው ክፍል/አቅጣጫ መንቀሳቀስን የሚያመለክት ነው::

### 2.2. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉም

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም መነጠቅ ማለት የኋለኛው መለከት በሚነፋበት ጊዜ፤

***በመጀመሪያ ደረጃ*** በጌታ ያንቀላፉ (ጌታን እንደግል አዳኛቸው ተቀብለው የሞቱ) ቅዱሳን የማይሞተውን፣ ዘላለማዊውን፣ ያልተዋረደውን ነገር ግን የተከበረውን፣ የማይበሰብሰውን፣ ምድራዊ ያልሆነውን ነገር ግን ሰማያዊውን፣ መንፈሳዊ የሆነውን፣ የክርስቶስን አካል የመሰለውን፣ የማይጠፋውን አዲስ ሰውነት (አካል) ለብሰው በመነሳት፤ በሁለተኛ ደረጃ በዚህ ዓለም በሥጋ ያሉት (ያልሞቱት) ቅዱሳንም የሚነሱት የለበሱትን ዓይነት ዘላለማዊ አካል ለብሰው በቅጽበተ ዓይን በመለወጥ፤ ጌታን ክርስቶስ



ኢየሱስን ከሰማይ ሲመጣ በአየር ለመቀበል ወደተወሰነ የሰማይ ክልል የሚያደርጉት ጉዞ መነጠቅ ይባላል:: 1ኛተሰ. 4:13-17፤ 1ኛቆሮ. 15:20-57::

በዚች ምድር እግዚአብሔር የራሱ ርስት አለው:: ይህም ርስቱ ቤተ ክርስቲያን ናት:: እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በልጁም በኢየሱስ ክርስቶስ የፀጋ ሥራ ከነገድ፣ ከወገን፣ ከቋንቋና ከሕዝብ ሰዎችን አድኗል፤ ከዲያብሎስ እጅ፣ ከክፉ ቀንበር ነጻ አውጥቷል:: በራሱ ጊዜና ፈቃድ በመላው ዓለም የክርስቶስን የድነት ጥሪ አምነውና ገሃነምን (የዘላለሙን ቅጣት) ፈርተው ወደ እርሱ የመጡትን ሁሉ ወደ ሰማያዊቱ ከተማ ይሰበስባል:: እግዚአብሔር በልጁ በጌታ ኢየሱስ በኩል ዋጅቶ በመንፈስ ቅዱስ ያተማቸውን እውነተኛ አማኞች በቅርብ ጊዜ ውስጥ ወደ ሰማያዊ ስፍራቸው ይወስዳቸዋል::

## ክፍል ሦስት

## የመነጠቅና የጌታ ዳግም ምጽዐት ልዩነቶች

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመፍታት ከሚያስቸግሩ ጉዳዮች ውስጥ አንደኛው የጊዜና የቅደም ተከተል ነገሮች ናቸው:: አንዱ ትዕይንት ከሆነ በኋላ የሚቀጥለው የትኛው እንደሆነ ለመለየት አስቸጋሪ ቢሆንም ጊዜንና ልብን አገናኝቶ በመንፈስ ቅዱስ በመመራት ለታገለ የእግዚአብሔር ሰው ግን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን እውነት እንደሚገለጥለት አሌ የማይባል ሐቅ ነው:: ምክንያቱም ወደ እውነት ሁሉ የሚመራው መንፈስ ቅዱስ ስላለ ነው:: ዮሐ.16:13::

አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያጠኑ የእግዚአብሔር ሰዎች በመነጠቅና በጌታ ዳግም ምጽዐት መካከል ልዩነት እንዳለ ሳይገነዘቡ ቀርተዋል:: ጌታ ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመምጣቱ ሁኔታ በግልጽ ይሁን በስውር (ሁኔታውን) የሚመጣበት ጊዜ (ወቅት) ለምሳሌ ከመከራው በኋላ ወይስ በፊት የሚለውን የሚመጣባቸውን ምክንያቶች፣ ከማን ጋር እንደሚመጣ፣ ማለትም ቅዱሳኑን ሲወስድ፣ ከቅዱሳኑ ጋርም ሲመጣ፣ ሌሎችንም አጠቃላይ ሁኔታዎች ከሚከተለው ሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል::

| | <u>በመነጠቅ ጊዜ</u> | | <u>በዳግም ምጽዐት ጊዜ</u> |
|---|---|---|---|
| 1. | ጌታ ኢየሱስ ለቅዱሳን ብቻ ይታያል 1ኛተሰ. 4:17 | 1. | ለዓለም ሁሉ ይገለጻል (ይታያል) ራዕይ 1:7፣ ማቴ. 24:30 |
| 2. | በአየር ውስጥ ይገለጣል 1ኛተሰ. 4:17 | 2. | ወደ ምድር ይመጣል:: ራዕይ 19:11-19:: ማቴ. 24:30፤ ሐሥ.. 1፣11 |
| 3. | ቅዱሳኑን ለመውሰድ ይመጣል ዮሐ. 14:3 | 3. | ከቅዱሳኑ ጋር ይመጣል ይሁዳ. 14-15፤ ዘካ.14:5፤ ራዕ. 19:14 |
| 4. | በቅዱሳኑ ሊከበርና ሊገረም ይመጣል 2ኛ ተሰ. 1:9-10:: | 4. | በምድር ነዋሪዎችና በቅዱሳኑ ዘንድ ሊከብር 2ተሰ.1:10፣ ኢሳ.11:9:: |
| 5. | ለመዋጋት ሳይሆን ቅዱሳንን ለመውሰድ ይመጣል:: ራዕይ 19:11፣14-20:: | 5. | ለመዋጋትና በጽድቅ ለመፍረድ ይመጣል:: 1ኛተሰ. 4:17-18:: |
| 6. | በ70ኛው ሱባኤ መጀመሪያ ይመጣል 2ኛተሰ. 2:6-7:: | 6. | በ70ኛው ሱባኤ ማብቂያ ይመጣል ዳን.9:27ና 2ኛተሰ.2:3-8 ይነጻጸር |
| 7. | ሐሰተኛው ክርስቶስ ሳይገለጥ 2ኛተሰ. 2:3-8:: | 7. | ሐሰተኛው ክርስቶስ ተገልጾ ከሰራ በኋላ:: 2ኛተሰ. 2:3-8:: |



ከላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጋር ተነጻጽረው በቂ መረጃ ሊሆኑ ይችላሉ::

የመነጠቅ ዓይነቶችን በዝርዝር አልተመለከትንም:: ከመነጠቅ ዓይነቶች ውስጥ ..የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ.. በዚህ ክፍል ከተጠቀሰው የጌታ ዳግም ምጽዐት ጋር ሊወዳደር የሚገባው ነው:: ሌሎቹ የመነጠቅ ዓይነቶች ከቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ጋር ሲነጻጸሩ አፈጻጸማቸው አንድ ዓይነት ይሁን አይሁን በግልጽ የተጻፈ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም::

በመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን መነጠቅና የጌታ ዳግም ምጽዐት መካከል የአንድ ሱባኤ ወይም የሰባት ዓመታት(ሙ.ቃ.ይ.) ልዩነት አለ:: በራዕይ መጽሐፍ ምዕራፍ ሁለትና ሦስት ውስጥ ስለቤተ ክርስቲያን መኖር በዝርዝር ይናገራል:: በምዕ. 19:14 ላይ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ከቅዱሳን ጋር

ተዳምራ ወደ ምድር ስትወርድ ይታያል:: ይህ የክርስቶስ ወደ ምድር መምጣት በሺሁ ዓመት መጀመሪያ በ70ኛው ሱባኤ መጨረሻ ከሆነ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በራዕይ 4:1 ላይ ወይም በቤተ ክርስቲያን ዘመን ማብቂያ ላይ ሆኗል ማለት ነው:: ይህም ከጉቱ የመከራ ዓመታት በፊት ነው:: ስለሆነም የቤተ ክርስቲያንን መነጠቅ ጊዜ ከክርስቶስ ዳግም ምጽዐት ጋር አንድ እንደሆነ ልናስብ አይገባም:: ሁለቱ ልዩነት አላቸው:: መነጠቅ የክርስቶስ መፅአት አይደለም:: መነጠቅ የሚሆነው ጌታ ለቤተ ክርስቲያን ብቻ ሲመጣ ሲሆን ዳግም ምጽአት ግን በግልጽ ለአለም ህዝብ ሁሉ እየታየ ነው:: ራዕይ. 19:11-19::



# ክፍል አራት

## <u>የመነጠቅ ዓይነቶች</u>

በዚህ ክፍል ስለ መነጠቅ ዓይነቶች ሲገለጽ ልናተኩርበት የሚገባው ነገር መነጠቅን ከጊዜና ከቅደም ተከተል ከኳያ መመልከቱ ላይ ነው:: በመጀመሪያው ትንሳኤ የሚፈጸሙ አምስት የመነጠቅ ዓይነቶች አሉ:: እነዚህም የመነጠቅ ዓይነቶች አፈጻጸማቸው በቅደም ተከተል ነው:: ስለ መነጠቅ ጊዜ (በቅድመ-መከራና፣ በመከራው መካከል ስለመሆን) የተለያዩ አመለካከቶች ሊፈጠሩ ከቻሉባቸውም ዐበይት ምክንያቶች ውስጥ አንደኛው የመነጠቅን ዓይነቶች በዝርዝር አለማወቅ ነው:: በተጨማሪም የቅድመ መከራ ቅዱሳንና የመከራውን ዘመን ቅዱሳንን አብሮ ከማያያዝ የተነሳ ነው:: ምልክቶችንና መንፈስ ቅዱስን መሰረት በማድረግ የመነጠቅን የጊዜ አካባቢ፣ ለመረዳት ዋነኛው መሠረት መነጠቅ ማንን እንደሚመለከትና በምን ዓይነት ሁኔታዎችና ጊዜአት እንደሚፈጸም ከእግዚአብሔር ቃል በትጋት መመርመር ነው::

### አምስቱ የመነጠቅ ዓይነቶች

እስካሁን በተደረገው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አምስት የመነጠቅ ዓይነቶች ተገኝተዋል:: ሆኖም ግን አንዳንዶች በሰባኛው ሱባኤ መጨረሻም ላይ በቅድመ ሺህ ዓመት ጅማሬ ላይ ስድስተኛውን የመነጠቅ ዓይነት ማመልከት የሚፈልጉም መኖራቸው ሊዘነጋ አይገባም:: አምስቱ ዋና ዋና የመነጠቅ ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው::

### 4.1. የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን መነጠቅ

ልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ስንመለከት ጌታ ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጐ የሞትና የሲኦልንም መክፈቻ ወስዶ ከተነሳ በኋላ በብሉይ ኪዳን ዘመን በህይወታቸው ዘመን ሁሉ በሰይጣን አስፈራሪነት በስጋት ይሰቃዩ የነበሩትን የአማኞች (ዕብር. 2:14) ነፍሳት ከማረከ በኋላ አሁን ባዶ ከሆነው ከታችኛው ገነት (ሙ.ቃ.ይ.) ወደ ላይኛው ገነት ጠራርጐ ወስዷቸዋል:: አሁን እነዚህ ነፍሳት በዕብ. 12፣23 እንደተጠቀሰው ..በጻድቃን መንፈሶች ጉባኤ ይገኛሉ:: ማቴ. 27፣52-52፤ ኤፌ.4፣8-10፤ 1ኛጴጥ. 3፣18-19::

እነዚህ ነፍሳት ያለ እኛ ፍጹማን ስለማይሆኑ ከታችኛው ገነት ወደ ላይኛው ገነት በመነጠቅ ተወሰዱ እንጂ አዲሱን አካል አልለበሱም:: ጌታ ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጐ እስከተነሳበት ጊዜ ድረስ ሰይጣን እያስፈራራቸው ይፎክርባቸው ነበር:: በኋላ ግን ..ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ ድል መንሳትህ የት አለ? እንደተባለ ጌታ ሞትን ድል ሲያደርግ በሞት ፍርሃት በህይወታቸው ከሚሰቃዩበት ከታችኛው ገነት (የአብርሃም ዕቅፍ) ነጻ በማውጣት ወደ ላይ ማለትም ወደ አራተኛው ገነት(አሁን ቅዱሳን ሲሞቱ የሚሄዱበት ስፍራ) ወስዷቸዋል:: ለዚህም ነው «ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ ለሰዎችም ሥጦታን ሰጠ» በመባል የተጻፈው ነው ኤፌ.4:8:: ይህንን ጉዞ የመጀመሪያው መነጠቅ እንለዋለን:: እነዚህም ቅዱሳን (ያልተገለጠውን ነገር እንዳለ ትተን) ከአቤል ጀምሮ እስከ ጌታ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ ያንቀላፉትን ቅዱሳን በሙሉ የሚጨምር ነው::

በዚህ ክፍል መነጠቅ ስንል ከታችኛው ገነት ወደ ላይኛው ገነት የተካሔደውን የነፍሳትን መዛወር እንጂ አዲሱን አካል ለብሰዋል ለማለት አይደለም:: ይህ አዲሱን አካል የመልበሱ ጉዳይ ፍጹም የሚሆነው ወደፊት የመጨረሻው መለከት ከተነፋ በኋላ ነው::



### 4.2. የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ

ይህ የመነጠቅ ዓይነት፡ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደግል አዳኛቸው በማድረግ የተቀበሉትንና የዳግም ልደትን ህይወት በማግኘት የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑትን ቅዱሳን አማኞች በሙሉ የሚያጠቃልል ነው:: እነዚህም ሁለት ክፍሎች አላቸው:: ይኸውም በጌታ ያንቀላፉ ማለት ጌታን አምነው የሞቱና በህይወት ሳይሞቱ ያሉ ናቸው:: እነዚህ ክፍሎች የመከራውን ዘመን ቅዱሳን አማኞች ወይም የመከራውን ዘመን ቤተ ክርስቲያን አይጨምርም:: እነዚህ ቅዱሳን ጌታ ኢየሱስ በማቴ. 16፣18 ቤተ ክርስቲያኔን እሰራለሁ እንዳለ ቤተ ክርስቲያንን ከመሰረተበት ጊዜ አንስቶ እስከ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ያሉት ቅዱሳን ናቸው::

በዚህ ክፍል እውነተኛ አማኞች የሆኑ ሁሉ ፈጽሞ አይቀሩም ሁሉም ይነጠቃሉ:: ወደ ተዘጋጀላቸውም የእረፍት ስፍራ ይወሰዳሉ:: ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች መመልከት የበለጠ ይጠቅማል:: 1ኛቆሮ.15፣23፤ 51-54፤ ዮሐ. 14፣1-3፤ ሉቃስ 21፣34-36፤ 2ኛቆሮ.5፣1-8፤ ኤፌ.5፣27፤ ፊልጵ. 3፣20-21፤ 1ኛተሰ. 2፣19፤ 2ኛተሰ. 2፣1፣7፤ 1ኛዮሐ. 2፣28፤ 3፣2፤ 1ኛጴጥ. 5፣4::

የኋለኛው መለከት ሲነፋ በዘመኑ ፍጻሜ በክርስቶስ ያመኑና የሞቱ በህይወትም ያሉ ሁሉ የትንሳኤን ህይወት ወይም በቅጽበተ-ዓይን የመለወጥን ህይወት አግኝተው ይነጠቃሉ:: አንዳንድ አማኞች እንደሚሉት ደካማ ህይወት ያላቸው ያልነቁ ቅዱሳን አይነጠቁም የሚሉት ፈጽሞ ስህተት ነው:: ሆኖም ግን ጌታን ከተቀበሉ በኋላ በዕብ.10፣26 እንደተጠቀሰው ወደው በድፍረት ኃጢአት የሚሰሩና መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝኑ ከሆነ ከወይኑ ግንድ የመቆረጫው ወይም ከጌታ አፍ የመተፊያው አንዱ መንገድ ..መነጠቅ.. እንዳይሆን መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል::

### 4.3. የ144000 አይሁዶች መነጠቅ

እግዚአብሔር የራሱ የሆነ ዓላማ አለው:: ይህንንም ዓላማውን ከፍጻሜ ለማድረስ የሚጠቀምባቸው የራሱ የሆኑ አሰራሮች አሉት:: መላዕክት፣ ሰዎችና ልዩ ልዩ ፍጥረታት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከሚፈጽሙት ኃይላት ውስጥ ዋነኞቹ ናቸው:: እግዚአብሔር የሰይጣንን ፈቃድና ሐሳብ ለማፍረስ በመከራው ዘመን ካቆማቸው (ከተከላቸው) አገልጋዮቹ ውስጥ 144000 አሁዶች ዋነኞቹ ናቸው::

እነዚህ 144000 አይሁዶች በራዕይ 12፥4-5 ..ህጻን.. ወይም ..ወንድ ልጅ.. ተብለዋል:: በዚህ ክፍል (ራዕይ 12) ሴት የተባለችው የእስራኤል አገር፣ ዘንዶው የተባለው ሰይጣን፣ በተጨማሪም ወንዱ ልጅ የተባለው 144000 አሁዶች እንደሆኑ መገንዘቡ እጅግ ጠቃሚ ይሆናል:: ..ወንድ ልጅ.. የሚለው ሐረግ ትርጉም ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስን ሰዎች ያጨቃጨቀ ቢሆንም ትክክለኛ ፍቺውን በመልቀቅ ሴቲቱን እንደ ማርያም ወይም ቤተ ክርስቲያን: ወንዱን ልጅ እንደ ጌታ ኢየሱስ በመተርጐም መውሰድ ከታሪክና ከትንቢት አንጻር ሲተረጐም የማይጣጣም ሁኔታን ይፈጥራል:: ምክንያቱም የራዕይ መጽሐፍ የተጻፈው በአብዛኛው በመጨረሻው ዘመን ሲሆኑ ላሉ ነገሮች ስለሆነና የ[illegible]ም ነገሮች ፍጻሜ ቅደም ተከተላዊ በመሆኑ ነው::

አንዳንድ የ[illegible] ቅዱስ ሰዎች «ወንዱን ልጅ» ጌታ ኢየሱስ: ሴቷን ደግሞ እንደ ቤተ ክርስቲያን እንደሆኑ ለማስረዳት ይሞክራሉ:: ይህ ግን ከመዓዕያን: ከታሪካውያንና ከሐላፍያን የአቡቀለምሲሳዊ የትርጉም ሕግ አንጻር ሲታይ የሚጣረስ ይሆናል:: ምክንያቱም፤

4.3.1. <u>የራዕይ መጽሐፍ ከ1-3 ስለቤተ ክርስቲያን ዘመን ከተናገረ በኋላ ቀጥሎ ከ4-22 ያለው በሙሉ የሚናገረው ስለ ወደፊቱ ማለትም የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ</u> ከሆነ በኋላ ያለውን በመሆኑ፤ ራዕይ 12 ስለ ማርያምና ጌታ ኢየሱስ የሚናገር ከሆነ፤ ማርያም በህይወት አለች:: ኢየሱስም ገና



ይወለዳል ወደሚል ትርጉም ሊወስደን ነው:: የራዕይን መጽሐፍ ቁልፍ ሐሳብ የያዘው ራዕይ 1፥19 ..ከዚህ በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን.. ሲል የሚያመለክተው ከራዕይ 4፥1 በኋላ ያለውን ነው:: ስለሆነም ራዕይ 12 ፈጽሞ ገና አልተፈጸመም ስለ ጌታ ኢየሱስና ስለ ማርያምም አይገልጽም::

4.3.2. *<u>በራዕይ 12፥6 እና 12፥14 የተጠቀሰው 1260 ቀናትና ዘመን፣ ዘመናትና የዘመንም እኩሌታ</u> የሚያመለክተው በዳን. 9፥24-27 እንደተጠቀሰው የ70ውን ሱባኤ ሁኔታ ስለሆነ ይህም*

*ሱባኤ ገና ወደፊት የሚፈጸምና ሱባኤውም የተነገረው ስለ እስራኤል መሆኑ፤*

4.3.3. <u>በኢሳ. 66፥7-8 የተነገረው ትንቢት እስከ አሁን በዓለም ታሪክ አለመፈጸሙ፤ ነገር ግን ወደፊት በ70ኛው ሱባኤ አጋማሽ የሚፈጸም መሆኑ</u> በዚህ ክፍል ኢሳይያስ .....ወንድ ልጅ ወለደች.. .....በአንድ ጊዜ ህዝብ ይወለዳልን?.. .....አገር በአንድ ቀን ታምጣለችን.. በማለት ይናገራል:: በማያያዝ ወላጇ ሴት እንደሆነች እርሷም ..አገር.. እንደሆነች የተወለደው ወንድ ልጅ ደግሞ ..ሕዝብ.. እንደሆነ ይገልጻል:: ይሔ ትንቢት እስካሁን አልተፈጸመም:: አገር ያላት ጽዮንን እንደሆነ በማሳየት ጽዮን አገር (እስራኤል) ከሆነች ሕዝቧ ደግሞ እስራኤላውያን ማለትም 144000 አይሁዶች መሆናቸውን ኢሳ.66 እና ራዕይ 12ትን በማገናዘብ መረዳት ይቻላል::

4.3.4. <u>ሴቷ የምትወክለው ..ብሔራዊ እስራኤልን.. ማለትም ህዝብን ከሆነ ሴቷ የምትወልደውም ..ወንድ ልጅ.. ባህሪዋን የሚመስል ልጅ ህዝብ መሆን ስላለበት ነው::</u> እነዚህ 144000 አይሁዶች ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ስለመነጠቃቸውና በምድር ስለሚገጥማቸው ሁኔታ ለመጻፍ በራዕይ 12፥4 ላይ ..ዘንዶውም ሴቲቱ በወለደች ጊዜ ህጻንዋን እንዲበላ ልትወልድ ባላት ሴት ፊት ቆመ.. የሚለው ዓረፍተ ነገር ትርጉም ማየት ያስፈልጋል :: በእስራኤል እግዚአብሔር እነዚህን 144000 አይሁዶች በራዕይ 7፥3 እንደተጠቀሰው በ70ኛው ሱባኤ ለአገልግሎቱ ይለያቸዋል:: እነርሱም

በታተሙበት ዓላማ መሠረት የመጀመሪያውን ሦስት ተኩል ዓመታት ካገለገሉ በኋላ ማንነታቸው በአውሬው ይታወቃል:: በዚህ ጊዜ ሐሰተኛው ክርስቶስ ሊያጠፋቸው ይነሳባቸዋል:: በዚህ ወቅት ወደ ሰማይ ይነጠቃሉ መነጠቃቸውም የሚረጋገጠው በራዕይ 14፣1-3 ባለው ክፍል ነው:: ራዕይ 7፣1-8 መታተማቸው (መለየታቸው) ይታያል:: ባሪያዎች ናቸውና አገልግሎታቸውን ከፈጸሙ በኋላ በራዕይ 12፣5 እንደተጠቀሰው በመከራው ዘመን እህዛብን በብረት በትር ገዝተው አገልግሎታቸውን ከፈጸሙ በኋላ ወደ ሰማይ ወደ ተዘጋጀላቸው ስፍራ (ይወሰዳሉ) ይነጠቃሉ:: ይህም የ144000 (መቶ አርባ አራት ሺ) አይሁዶች መነጠቅ.. ይባላል::

### 4.4. የታላቁ የመከራው ዘመን ቅዱሳን መነጠቅ

ይህ አራተኛው የመነጠቅ ዓይነት ነው:: እነዚህ ቅዱሳን በ7ቱ ዓመታት መከራ ውስጥ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው በመቀበል ደህንነትን ያገኙ ቅዱሳን ናቸው:: በራዕይ 6፣1-19፤21 በተገለጸው የመከራ ጊዜ ከነገድ፣ ከወገንና ከቋንቋ የተቤዡ ናቸው (ራዕይ 7፣9):: እነዚህ ቅዱሳን በዳን. 9፣27 ከተጠቀሰው 70ኛው ሱባኤ ወይም ሰባት ዓመታት የመከራ ዘመን ውስጥ ስመዳናቸው ማስረጃ የሚሆኑን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ራዕይ 7፣14 እና 20፣4 ናቸው::

በራዕይ 7፣14 ላይ ..እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው.. የሚለው ዓረፍተ ነገር፣ ሐሳቡ የሚያመለክተው ከመከራው ጅማሬ እስከ ፍጻሜ ኖረው ከመከራው ውስጥ የወጡና በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት የቀረቡ ቅዱሳን መሆናቸውን ነው:: ቁጥራቸው ሊታወቅ አልተቻለም:: እነዚህ አይሁዶች ብቻ ናቸው ለማለት አይቻልም፤ ምክንያቱም ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ውጪ ይሆናል:: ከዚህ ጋር ማያያዝ የምፈልገው ነገር አለ:: ይኸውም እነዚህ ቅዱሳን ከመከራው ውስጥ ከምድር ወጥተው በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ለመቅረብ ያበቃቸው ልብሳቸውን በበጉ ደም ማጠባቸው መሆኑን ነው:: ይህም ከሆነ የመዳን በር በመከራው ዘመን ለአይሁዶችም ሆነ ለአህዛብ ዝግ



አለመሆኑንና የመከራው ዘመን ጽኑ የእግዚአብሔር ቁጣ ቢገለጽበትም ለንስሀ ዕድል የማይሰጥበት የፍዳና የቁጣ ዘመን ብቻ አለመሆኑን መረዳት ያሻል::

የራዕይ 20፣4 ሐሳብ ደግሞ ..በሺሁ ዓመት.. መንግስት ከክርስቶስ ጋር የመንገስ ስልጣን የተሰጣቸው ለአውሬውና ለምስሉ ያልተንበረከኩ ቅዱሳን እንደሆኑ ይገልጻል:: አውሬው (ሐሰተኛው ክርስቶስ) የምድር ነዋሪዎች እንዲሰግዱለት ማስገደድ የጀመረው ስልጣን ከጨበጠበት ጊዜ አንስቶ ነው:: በኖረበት ሰባት ዓመታት በግዛቱ ያሉትን አስገብሯል (ያስገብራል):: ያልሰገዱለትን ሁሉ ከተነጠቁት በቀር በሰባቱም ዓመታት ውስጥ በራዕይ 17፣6፤ 18፣24 እንደተጠቀሰው በጋለሞታይቱ ቤተ ክርስቲያን በኩል አስጨፍጭፏል (ያስጨፈጭፋል):: እነዚህ ቅዱሳን፤ ማለትም ከጌታ ጋር ለሺህ ዓመት ኖረው የሚነግሱት በአውሬው ዘመን በአገልግሎታቸው ምክንያት (ራዕይ 20፣4) ራሶቻቸው የተቆረጡባቸው ከሆኑ ለዚህ ዕድል የበቁት በመጀመሪያው የቅዱሳን ትንሳኤ (ራዕይ 20፣6) ዕድል ፈንታ የነበራቸው ናቸው ማለት ነው:: የትንሳኤው ጊዜ የተከናወነበትን ትክክለኛ ጊዜ ለማወቅ የሚያስቸግር ቢሆንም 70ኛው ሱባኤ ማለቂያ፣ የሺሁ ዓመት መንፍስት መጀመሪያና የገሃነም ደጆች አለቃ መታሠሪያ ጊዜ ላይ መሆኑን መገመት ይቻላል::

### 4.5. የሁለቱ ነቢያት መነጠቅ

የሁለቱ ነቢያት መነጠቅ ከቀሩት ሁሉ የመነጠቅ ዓይነቶች የመጨረሻው ነው ተብሎ ይገመታል:: እነዚህ ነቢያት የእግዚአብሔርን ፈቃድና ሃሣብ በአውሬውና በተከታዮቹ በቀሩትም የምድሪቱ ሐጢአተኞች ላይ የሚገለጹ የእግዚአብሔር የቁጣው በትሮች ናቸው:: የአውሬውን (የሐሰተኛውን ክርስቶስ) ፈቃድ ሙሉ በሙሉ የሚቃወሙ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው:: ከሁለቱ የመከራ ክፍሎች በኋላኛው የሶስት ተኩል ዓመታት ታላቅ መከራ መጀመሪያ ላይ ተነስተው ለ3፡ ዓመታት ያህል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይፈጽማሉ:: በመጨረሻም (ራዕይ 11፣7-11)

አገልግሎታቸውን ከፈጸሙ በኋላ አውሬው ከጥልቁ ይወጣል ይዋጋቸዋል፤ ያሸንፋቸውማል፤ ይገሉላቸውማል:: ስጋቸውም ለ3½ ቀናት ይሰቀላል:: ሰዎችም ሁለቱ ነቢያት በመሞታቸው ይደሰታሉ:: ከዚያም የህይወት መንፈስ ይገባባቸዋል ወደ ሰማይም ይነጠቃሉ:: ይህ 5ኛው መነጠቅ ነው::



# ክፍል አምስት

## <u>የቤተ ክርስቲያን የመነጠቅ ጊዜ</u>

በዚህ ክፍል የምንመለከተው መነጠቅ ምን ጊዜ እንደሚሆንና ለተሰጡትም የመነጠቅ ጊዜ ሃሣቦች የቀረቡትን መረጃዎች ይሆናል:: ..የመነጠቅ ጊዜ.. ሲባል ከመጨረሻ ነገሮች ውስጥ ማለትም የምልክቶች መታየት፣ የሺህ ዓመት ሥርዓት፣ የመከራው ዘመንና የጌታ ዳግም ምጽፀት የመሳሰሉትን ስናስብ <u>*አሁን ያለችው ቤተ ክርስቲያን የመነጠቅ ጊዜዋ በቅደም ተከተል ሲቀመጥ የት ስፍራ እንደሚሰለፍ ለማመልከት ነው::*</u>

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች በዚህ ሃሣብ ላይ የተለያዩ ማስረጃዎችን በማቅረብ መጻሕፍት ጽፈዋል:: መነጠቅ የሚፈጸምበትን ትክክለኛ ቀን፣ ሰዓትና ወር ለማወቅ ባይቻልም ከፍጻሜ ነገሮች አሰላለፍ አኳያ ግን መነጠቅ ከምን በፊትና በኋላ እንደሚሆን ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር ማወቅ ይቻላል:: የመነጠቅ ጊዜ ከትንቢቶች ፍጻሜ ቅደም ተከተል አንጻር መቼ እንደሚሆን ሃሣብ የሚያቀርቡ ሦስት ክፍሎች አሉ:: እነርሱን ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን::

### ስለ መነጠቅ ጊዜ የቀረቡ አመለካከቶች

ስለ መጨረሻ ዘመን ስናስብ ከስድስቱ መሰረታዊ ቅደም ተከተላዊ ትዕይንቶች ውስጥ ማለትም 1ኛ. ምልክቶች 2ኛ. መነጠቅ 3ኛ. ታላቁ መከራ 4ኛ. የጌታ ዳግም ምጽዐት 5ኛ. የሺህ ዓመት መንግስትና 6ኛ. የዘላለም መንግስት ውስጥ ***መነጠቅ*** ሁለተኛውን ደረጃ ይይዛል:: ከመከራው ጋር በተያያዘ ደግሞ የመነጠቅ ጊዜ መቼ እንደሚሆን ሶስት ዋና ዋና ሃሣቦችና አመለካከቶች ጎልተው ይታያሉ:: እነርሱም የሚከተሉት ናቸው::

5.1. ቅድመ-መከራ መነጠቅ አመለካከት

5.2. መንፈቀ-መከራ መነጠቅ አመለካከት

5.3. ድህረ-መከራ መነጠቅ አመለካከት ይገኛሉ:: የእነዚህንም አመለካከቶች ዋና ዋና ሃሣቦችና ፍቺ በጥቂቱ እንደሚከተለው ይሆናል::

## 5.1. ቅድመ-መከራ-መነጠቅ አመለካከት

በቅድመ-መከራ መነጠቅ የሚያምኑ ክፍሎች 70ኛው በዳንኤል የተባለው ሱባኤ (የሰባቱ ዓመታት መከራ) ከመጀመሩ ወይም አውሬው ከእስራኤልና ከዓለም ሕዝብ ጋር የአንድ ሱባኤ ቃል ኪዳን አድርጐ በግልጽ ከመውጣቱ በፊት የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ይሆናል የሚሉ ናቸው:: በዚህ ጊዜ የሚነጠቁት ጌታን ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው የተቀበሉ አማኞች ሁሉ እንደሚሆኑ ያምናሉ:: የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከመከራው በፊት እንደሚሆን የሚያቀርቧቸው ማስረጃዎች አሉ:: እኔም በቅድመ መከራ መነጠቅ ከሚያምኑት ክፍል ስለሆንኩ ዝርዝር እውነቶችንና ማስረጃዎችንም ጭምር በሚቀጥሉት ክፍሎች እንመለከታለን::

## 5.2. መንፈቀ-መከራ መነጠቅ አመለካከት

የዚህ አመለካከት ተከታዮች የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በመከራው አጋማሽ እንደሚሆን የሚያምኑና የሚያስተምሩ ክፍሎች አቋማቸው እንደሚከተለው ነው:: መከራው የመጀመሪያው ሦስት ተኩል ዓመታት ..አነስተኛ መከራ.. እና የኋለኛው 3½ ዓመታት ..ታላቁ መከራ.. የሚል ሁለት ክፍሎች እንዳለው ያምናሉ:: በመጀመሪያው 3½ ..አነስተኛ የመከራ.. ዘመን ቤተ ክርስቲያን እንዳለችና በመከራው ውስጥ እንደምታልፍ ከዚያም የኋለኛ ው ..ታላቁ መከራ.. ማለትም ታላቁ የእግዚአብሔር ቁጣ ሳይጀምር የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ይሆናል ይላሉ::

በዚህ በመከራው አጋማሽ መነጠቅ እንደሚሆን ከሚያስተምሩት መሪዎች ውስጥ ኢ.ኤ.አ. በ1895-1976 የኖረው ጄምስ ኦ በዝዌል እና በ1874-1960 የኖረው ኖርማን ቢ. ሃሪዘን ዋነኞቹ ናቸው:: ሆኖም ግን ኖርማን ቢ ሃሪዘን ከጄምስ ኦ በዝዌል በላቀ ሁኔታ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በመከራው አጋማሽ መሆኑን ያጠነክራል፣ ያስተምርማል:: እንደ ሪቻርድ ኤሪክሰን አገላለጽ በ«መንፈቀ-መከራ» መነጠቅ አምነው ከሚያስተምሩት ሰዎች አንዱ



ሃሪዘን ሃሣቡን ለማጽናት ከሚያቀርባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው::

5.2.1. እስከ ራዕይ 11 የተጠቀሰው መከራ ..ታላቁ መከራ.. ሳይሆን ..የምጥ ጣር መጀመሪያ.. ከሰባቱ ዓመታት የመጀመሪያው 3ኟ ዓመታት ቤተ ክርስቲያን ታልፍና ልክ ግማሽ ላይ ትነጠቃለች::

በማቴ. 24:8፤ቁ.21ና በራዕይ 6-9 የተጠቀሱት የሰባቱ መለከቶችና የሰባቱ ማህተሞች ቁጣ ሲፈጸም ቤተ ክርስቲያን ትኖራለች ይላል:: ሃሪዘን የተባለው የዚሁ የመነጠቅ ክፍል አማኝ ..የእግዚአብሔር ቁጣ.. የሚፈጸመው ..በታላቁ መከራ.. ጊዜ እንደሆነ ይህም ታላቁ መከራ የእግዚአብሔር የሰባቱ የቁጣ ጽዋዎች የሚፈሱበት ጊዜ መሆኑን ገልጿል:: በመለከቶቹና በማህተሞቹ ጊዜ ..ቁጣ.. እና ..መቅሰፍት.. የሚለው ቃል ስላልተጠቀሰ ይህ የምጥ ጣር መጀመሪያ ነው:: ራዕይ 14:10፤ 19፤ 15:7፤ 16:1:: በራዕይ 11:18 ላይ ..ቁጣ.. የሚለው ቃል ገና መጠቀሱ ስለሆነ ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ጽኑ ቁጣ ከቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በኋላ መጀመሩን ነው ይላል::

5.2.2 . የ1ኛው ቆሮንቶስ 15:52 ..የኋለኛው መለከት.. መነፋት

በመከራው አጋማሽ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ይሆናል የሚሉ ክፍሎች በመረጃነት የሚያቀርቡት ጥቅስ በቆሮንቶስ የተጠቀሰው ነው:: በ1ኛ ቆሮ. 15:52 የተጠቀሰው የኋለኛው መለከት በራዕይ 11 ውስጥ ከተጠቀሰው 7ኛው መለከት ጋር አንድ ዓይነት ነው:: በራዕይ 11:15 ሰባተኛው መልዐክ የነፋው መለከት የመጨረሻው ነው:: ከዚያ በኋላ ሌላ መለከት አልተነፋም፤ ይህ የኋለኛው መለከት በመሆኑ ከቆሮንቶስ ጋር ይሄዳል፤ በመቀጠል የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ይሆናል የሚል ማስረጃ ያቀርባሉ::

ከላይ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች በሚመለከት ትክክለኛ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሌሎችንም ማስረጃዎች ..በቅድመ-መከራ-መነጠቅ.. በምዕራፍ ስድስት ውስጥ አቀርባለሁ::

## 5.3. ድህረ-መከራ መነጠቅ አመለካከት

ይህንን ትምህርት የሚከተሉ አማኞችና ቤተ ክርስቲያናት ያላቸው አቋም የሚከተለው ነው:: ቤተ ክርስቲያን በታላቁ መከራ (በሰባኛው ሱባኤ) ውስጥ ታልፋለች:: መከራው ካለቀ በኋላ የቤተ ክርስቲያን መነጠቀ ይሆናል የሚሉ ሲሆኑ ይህንንም አቋም አንዳንድ የሮም ካቶሊክ፣ የግሪክ ካቶሊክ፣ ወግ አጥባቂ የሆኑ የፕሮቴስታንትና የሌሎችም ቤተ ክርስቲያናት በጥብቅ ይከተላሉ::

የድህረ-መከራ መነጠቅ አመለካከት ቀላል ዓይነት ፍቺ ያለው ቢመስልም፣ በውስጡ ሦስት ያህል የተለያዩ ክፍሎችን ይዟል:: እነርሱም፣

5.3.1. አምናዊ ድህረ-መከራ መነጠቅ

5.3.2. ከፊል-አምናዊ ድህረ-መከራ መነጠቅ

5.3.3. ነጋዊ-ድህረ-መከራ መነጠቅ ናቸው::

### 5.3.1. አምናዊ-ድህረ-መከራ መነጠቅ

በዚህ የመነጠቅ ጊዜ የሚያምኑ ክፍሎች መከራው ገና ዱሮ በቤተ ክርስቲያን ላይ ስለሆነ ታላቁ መከራ ተፈጽሟል (አልፏል) የሚሉና ምናልባት ከሩብ ያነሰው መከራ እንደሚቀር የሚያምኑ ናቸው::

የዚሁ የአምናዊ-ድህረ-መከራ መነጠቅ መሪ ከሆኑት ሰዎች አንዱ ጂ-ባርተን ፓይን ስለ መከራው የተነገሩት ትንቢቶች መፈጸማቸውን ያጠነክራል:: ከዚሁም ጋር የተያያዘውን ማስረጃ በሚከተሉት አራት ነጥቦች ማጠቃለል ይቻላል፤ ባርተን ፓይን፤

5.3.1.1. የክርስቶስ ዳግመኛ ምጽዐት ቅጽበታዊ ሆኖ የቤተ ክርስቲያንንም መነጠቅ ይጨምራል::

5.3.1.2. ይህም ዳግም ምጽዐት ከመከራው በኋላ ይሆናል::

5.3.1.3. በቅድመ-ዳግም-ምጽዐት የሚሆነው መከራ ግልጽ ወይም ቃል በቃል የሚፈጸም (ሊትራል) ሳይሆን ምሳሌያዊነትን ወይም ረቂቅ ትርጉምን (ፊገራቲቭ) የያዘ ነው::

5.3.1.4.1. ከክርስቶስ ዳግም ምጽዐት በኋላ ግልጽ የሆነ-የሚታይ (ሊትራል) የሺህ ዓመት ሥርዓት ይቀጥላል ይላል::

ፓይን ይህንን ሃሣቡን በይበልጥ ያገኘው ከቀደሙት አባቶች ትምህርት መሆኑን ገልጿል:: ከእነዚህም ውስጥ ..የመጀመሪያው የቀሌምንጦስ መልዕክት..፣ ..የበርናባስ መልዕክት..፣ ..የኢግናቲየስ መልዕክት ወደ ኤፌሶን ሰዎች.. እና ..የኢግናቲየስ መልዕክት ወደ ፖሊካርፕ.. ጥቂቶቹ ናቸው:: በተጨማሪም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚጠቅሳቸው ክፍሎች አሉት::

### 5.3.2. ከፊል አምናዊ-ድህረ-መከራ መነጠቅ

የዚህ መነጠቅ ዓይነት አመለካከት ያላቸው ተከታዮች ደግሞ የመከራው ዘመን ቀድሞ ጀምሮአል፤ በከፊል ተፈጽሟል፤ ሆኖም ግን ሙሉ በሙሉ አላለቀም የሚል ሃሣብ አላቸው:: ይህንንም ሃሣባቸውን በማጠናከር የመከራው ዘመን ቀደም ብሎ የጀመረና አሁን ቤተ ክርስቲያን ካለች መነጠቅ ወደፊት ይሆናል የሚለውን የቅድመ-መከራ መነጠቅ አማኞችን አመለካከት እንደ ሞኝነት ይቆጥራሉ:: እነዚህም ቢሆኑ እርስ በርሳቸው የተለያየ አመለካከት አላቸው::

የከፊል-አምናዊ ድህረ-መከራ መነጠቅና ባጠቃላይ የድህረ-መከራ መነጠቅ አመለካከት ተከታዮች ስለ መነጠቅ ወይም ስለ ፍጻሜ ነገሮች ሲያስቡ የትንቢቶችን አፈጻጸም ቃል በቃል ሳይሆን በረቂቅ ሁኔታ እንደሚያልፉ ያምናሉ::

### 5.3.3. ነጋዊ-ድህረ-መከራ መነጠቅ

የነጋዊ-ድህረ-መከራ መነጠቅ አመለካከት ያላቸው ክፍሎች መከራው (ታላቁ መከራ) ፈጽሞ ገና እንዳልጀመረና ወደፊት እንደሚቀጥል ያምናሉ:: መከራው ተጀምሮ ካለቀ በኋላ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ይሆናል:: በቤተ ክርስቲያን መነጠቅና በክርስቶስ ዳግም ምጽዐት መካከል የለባት ዓመታት የጊዜ ርዝመት እንዳለ ያምናሉ:: እስከ ሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ይህ አመለካከት በሰዎች ዘንድ ጉልቶ አልታወቀም ነበር::

በድህረ-መከራ መነጠቅ የሚያምኑ ክርስቲያኖች ቀደም ብሎ ካየናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች በተጨማሪ የሚያቀርቧቸው አሉ:: ለምሳሌ በሐሥ 8:1-3 ..በዚያን ቀንም በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ፤ ሁሉም ከሐዋርያትም በቀር ወደ ይሁዳና ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ::.. ይላል:: ይህንንም እውነት በመጥቀስ ..ታላቅ ስደት.. የሚያመለክተው ..ታላቅ መከራን.. ነው:: የእስጢፋኖስም መወገር ታላቁ መከራ መጀመሩን ከሚያመለክቱት መረጃዎች አንዱ ነው:: ጌታ ኢየሱስም በማቴ. 24:21 ..ታላቁን መከራ.. ለመግለጽ የተጠቀመበት ..ስሊፕሲስ.. የተሰኘ ው የግሪክ ቃልና በሐሥ. 8:1 ላይ የተጠቀሰው ..ታላቅ ስደት.. የሚለው ቃል አንድ ዓይነት ስለሆኑ የመከራው ዘመን ቀድሞውኑ ጀምሯል ይላሉ:: በምዕራፍ አምስት ..የመነጠቅ ጊዜ.. ንዑስ ርዕሶች ስር ስለ አመለካከታቸው እንጂ ሊሆን ስለሚገባው ትክክለኛ ሃሣብ ምንም ማስረጃ አልቀረበም::



# ክፍል ስድስት

## ቅድመ-መከራ መነጠቅ

በዚህ ክፍል ስለ ቅድመ-መከራ መነጠቅ ምንነት፣ አመለካከት፣ የቀረቡትንም ልዩ ማስረጃዎችና የታወቁትን የዚህ እምነት ተከታይ መሪዎች በዝርዝር እንመለከታለን::

### 6.1 የቅድመ-መከራ መነጠቅ አመለካከት

የዚህ መነጠቅ ክፍል ተከታዮች ቀደም ብሎ በምዕራፍ አምስት እንደጠቀሰው በዳንኤል የተባለው ሰባኛው ሱባኤ (የሰባቱ ዓመታት መከራ) ሳይጀምር የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ይሆናል:: የከራዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን እንጂ አሁን ያለችው ቤተ ክርስቲያን በ ታላቁ መከራ ውስጥ ፈጽሞ አታልፍም:: በቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ጊዜ ክርስቶስ ኢየሱስ ለዘህ ዓለም ለመታየት በግልጽ አይመጣም፤ ሆኖም ግን ወደ ተወሰነ የአየር ክልል መጥቶ ቅዱሳኑን በመውሰድ በሰማይ ወደ ተዘጋጀው ስፍራ ይመለሳል:: ከዚያም የመከራው ዘመን ካለፈ በኋላ ለሺህ ዓመት ለመንገስ ወደ ምድር ይመለሳል የሚሉት ዋና ዋናዎቹ አቋሞቻቸው ናቸው::

### 6.2. የቅድመ-መከራ መነጠቅ ማስረጃዎች

ከነባራዊ እውነታ ጋር በተያያዘ አንድ ነገር ሲነገር ወይም ሲደረግ፣ ለዚያ ለተከናወነው ነገር እውነተኝነት ማስረጃ ይቀርባል:: ያም ማስረጃ የአንድን ድርጊት ወይም አባባል ርቱእነተ ለማስረገጥና በሌሎችም ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ሁኔታዎችን ለማመቻቸት በወኪልነት ለመቆም ብቃት ያለው ይሆናል:: ሆኖም ግን የማስረጃ ሁሉ ብቁነት (ትክክለኛነት) የሚጸናውና የሚጸድቀው ማስረጃውንና አቅራቢውን የሚዳኝ ሌላ የበላይ የሌለው እውነተኛ እስኪገለጥ ይሆናል::

ቀደም ባለው ምዕራፍ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ የሚሆንበትን ጊዜ ለማመልከት ሦስት ያህል ዋና ዋና ሃሣቦች እንዳሉ ጠቅሻለሁ:: በዚህኛው

ምዕራፍ ግን ባለፈው ምዕራፍ በቂ ማብራሪያና ገለጻ ያልሰጠሁበትን የ..ቅድመ-መከራ መነጠቅ.. ሁኔታ ማስረጃዎችን አቀርባለሁ:: እኔም ብሆን የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከመከራው በፊት ይሆናል፤ ቤተ ክርስቲያን በ70ኛው ሱባኤ መከራ አታልፍም ከሚሉት ስለሆንኩ በተለያዩ ጊዜያት ከመጽሀፍትና ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከታሪክም ያገኘኋቸውን ማስረጃዎች ለማቅረብ እሞክራለሁ::

*__የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከመከራው በፊት እንደሚሆን የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት::__*

### 6.2.1. __የ..ዮሐንስ ራዕይ.. መጽሐፍ ቅደም ተከተላዊ አቀማመጥ__

ከ66ቱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ውስጥ ሐዋርያው ዮሐንስ የጻፋቸው መጻሕፍት የክንዋኔዎችን ቅደም ተከተል ከጊዜ አንጻር ከሚገልጹት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: ከእነዚህም ውስጥ የሐዋርያው ዮሐንስ ወንጌልና የዮሐንስ ራዕይ ናቸው:: በሁለቱ የዮሐንስ መጻህፍት ውስጥ አንድ ድርጊት ከተፈጸመ በኋላ ሌላው እንደሚቀጥል የሚያመለክቱ ሐረጐች ብዙ ጊዜ ተጠቅሰዋል::

ለምሳሌ:- ..__ከዚህም በኋላ__..፣ ..__ከዚያም በኋላ__..፣ ..__ከእነዚህም ነገሮች በኋላ__.. ... __የተሰኙት ይገኛሉ::__ እነዚህንም ሐረጐች በዮሐ. 3:22፤ 5:1፤ 6:1፤ 7:1፤ 21:1፤ 5:14፤ 13:7፤ በራዕይ 1:19፤ 4:1፤ 7:1፤ 9:12፤ 18:1፤ 19:1፤ 15:5፤ 20:3፤ እናገኛቸዋለን::

እነዚህ ሐረጐች የተጠቀሱበት ምክንያት የነገሮችን ክንዋኔ ከጊዜ አንጻር ለማመልከት ነው:: የእነዚህ ሐረጐች (በተለይም ..ከዚህ በኋላ.. የሚለው) በዮሐንስ ተደጋግመው መነገራቸው የዮሐንስ መልዕክት በይበልጥ ነገሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ላይ ያተከረ እንደሆነ ያመለክተናል (ያረጋግጥልናል):: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱትን እነዚህን ሐረጐችና



ጠቅታዊውን የታሪክ ምስክርነት መሠረት በማድረግ የዮሐንስ ራዕይን መጽሐፍ በአምስት ተከታታይ ክንዋኔዎች መክፈል ይቻላል::

*__የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ አከፋፈል__*

| __ተ. ቁ.__ | __ምዕራፍ__ | __ትዕይንቶች__ |
|---|---|---|
| 1 | 1 | አጠቃላይ መልዕክት (መግቢያ) |
| 2 | 2-3 | የቤተ ክርስቲያን ዘመን ክንዋኔ |
| 3 | 4-5 | ቅዱሳን በሰማይ (ድህረ-መነጠቅ) |
| 4 | 6-19 | የታላቁ መከራ (70ኛው ሱባኤ) ጊዜ |
| 5 | 20 | የሺህ ዓመት መንግሥት ክንዋኔ |
| 6 | 21-22 | የዘላለም መንግሥት (የአዲስ ሰማይና ምድር ሥርዓት) |

በተራ ቁጥር 4 ላይ ጥቂት ምዕራፎች የመከራውን ዘመን ትዕይንት የሚያመለክቱ አሉ::

ማንኛውም የራዕይን መጽሐፍ የሚያጠና የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ጥራት ላለው መረዳት በሠንጠረዡ ውስጥ እንደተቀመጠው ቅደም ተከተል መጽሀፉን ለማጥናት ካልሞከረ ችግር ይገጥመዋል:: በመንፈቀ-መከራ መነጠቅና በድህረ መከራ መነጠቅ ለሚያምኑ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከመከራው በፊት እንደሚሆን እንዳይቀበሉ ካረጋቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ የራዕይን መጽሐፍ በቅደም ተከተል መቀመጥ አለመገንዘብ ነው::

*__የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ቁልፍ ጥቅስ የሆነውን ምዕ.1:19 ስንመለከት በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍሏል:: ይኸውም:-ያየኸውን፣ አሁንም ያለውን የሚለውና ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን የሚሉት ናቸው::__*

..ያየኸውን.. ሲል በራዕይ 1:11-17 ያለው፤ ..አሁንም ያለውን.. ሲል በራዕይ 2 እና 3 በወቅቱ ያለውንና የወደፊቱ የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ፤

..ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን.. ሲል ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ሁኔ ካበቃ በኋላ (በራዕይ 4:1 እንደተመለከተው) ማለትም የቤተ ክርስቲያ መነጠቅ ከሆነ በኋላ የሚፈጸመውን ለማመልከት የቆመ ሃሣብ (እውነት ነው:: የራዕይ መጽሐፍ የተጻፈበት ዋነኛ ሃሣብ ከራዕይ 1:1 ስንመለከት ..ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ለማሳወቅ (ለማሳየት) ነው:: ምዕራፍ 1:19ኙንም ስናይ መጽሐፉን በሦስት ክፍሎ አጠቃላይ መልዕክቱን በቅደም ተከተል ያስቀምጥልናል:: የራዕይ መጽሐፍ በሙሉ በቅደም ተከተል በመጨረሻው ዘመን ለሚፈጸሙ ነገሮች (ትዕይንቶች) የተጻፈ ለመሆኑ በ መረጃ ልናገኝ የምንችለው የቅድመ-መከራ መነጠቅን ማስረጃዎች በሙሉ ከተመለከትን በኋላ ስለሚሆን ወደሚቀጥለው ማስረጃ ማለፉ ይመረጣል::

ከዚያ በፊት ግን በራዕይ መጽሐፍ በቅደም ተከተል ላይ ጥያቄ ቢኖር የዘላለም መንግስትና የሺሁ ዓመት መንግሥስት አለመጀመሩ በጥብቅ መረዳት፤ በተጨማሪም 70ኛው ሱባኤ (የሰባቱ ዓመታት መከራ) ላለመጀመሩ ዋነኛ ማስረጃ የሐሰተኛው ክርስቶስ ከእስራኤል ጋር የአንድ ሱባኤ ቃል ኪዳን አለማድረጉን መረዳት አንዱ ማስረጃ መሆኑን ማወቅ መልካም ነው:: ስለሆነም የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከራዕይ መጽሐፍ አሰላለፍ አንጻር ከመከራው በፊት ይሆናል ማለት ነው::

## 6.2.2. <u>የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በራዕይ 4:1 እንደሚሆን መረጃዎች መኖራቸው፡</u>

በራዕይ ምዕራፍ ሁለትና ሦስት ውስጥ ስለ ቤተ ክርስቲያን መኖር ይናገራል:: እንደ ኀላፍያንና ታሪካውያን አተረጓጎም ሁለቱ ምዕራፎች ስለ ሰባቱ የወቅቱ ቤተ ክርስቲያናት ሲናገር፣ እንደ መጻዕያንና በድጋሚ እንደ ታሪካውያን አተረጓጎም ደግሞ ሁለቱ ምዕራፎች እስከ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ድረስ በመላው ዓለም የምትገኘውን የዐለምአቀፋዊቱን ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ታሪካዊ ይዘት የሚያሳይ ነው:: ራዕይ 2ና3 ስለ ቤተ ክርስቲያን የሚተርከው በ 4:1 ላይ ሰማይ ከመከፈቱ በፊት ነው:: ራዕይ 4:1



ላይ ግን ሰማይ ስከፈት ያሳያል:: ለምን? ደግሞ ቤተ ክርስቲያን የበጉ ሚስት ክፍል ሆና በ19:14 ላይ ለሺህ ዓመት ስርዓት ከሰማይ ወደ ምድር ስትወርድ ያሳያል (ራዕይ 17:14):: ከራዕይ 19ኛው ምዕራፍ በኋላ ሰማይ ተከፍቶ አልታየም:: በዚህ ክፍል ግን ከሰማይ በአምባላይ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ፊት ፊት እየሄደ የሚመራቸው ከሰማይ የሚመጡትን ቅዱሳን ነው:: እነዚህ ቅዱሳን በራዕይ 17:14 እንደተጠቀሰው ከጌታ ኢየሱስ ጋር ሆነው አውሬውን በመዋጋት የሚያሸንፉ (ድል የሚያደርጉ) ናቸው (ራዕይ 19:19)::

በራዕይ 19:14፣17:14 የተጠቀሱት ቅዱሳን በራዕይ 19:11 ከተጠቀሰው በጽድቅ ፈርዶ ከሚዋጋው ከጌታ ኢየሱስ ጋር የሚተባበሩ ናቸው:: አውሬውንም ለመዋጋት የሚመጡትም ከሰማይ ከሆነ ደግሞም ..የበጉ ሚስት.. ቅዱሳን ከሆኑ ..የበጉ ሚስት.. የተባሉት ደግሞ የዘመናት ቅዱሳን ከሆኑ ..የበጉ ሰርግ.. የተካሄደው በሰማይ ከሆነ እነዚህ ቅዱሳን እንዴት ሆነው ወደ ሰማይ ወጡ ወደሚል ጥያቄ እንደሚመራን አሌ የማይባል ሐቅ (እውነት) ነው::

መልሱ በበጉ ሰርግ ተካፋይ የሚሆኑት የታመኑት የተጠሩትና የተመረጡት ቅዱሳን ከምድር ወደ ሰማይ የተሸጋገሩት በመነጠቅ ነው:: ይህም መነጠቅ (በራዕይ 4:1፣ 7:13-14፣ 7:1-8ትን ከ14:1-3 እና 12:5እን በማወዳደር) የተፈጸመና የተከናወነ ነው ማለት ነው:: ስለእነዚህ ቅዱሳን ዝርዝር ነገሮችን ለማየት በምዕራፍ አራት ..የመነጠቅ ዓይነቶችን.. ይመልከቱ:: የራዕይ 4:1 መነጠቅ ግን በተለይ የበጉ ሚስት ክፍል ከሆኑት ቅዱሳን ..በቤተ ክርስቲያን መነጠቅ.. ላይ ያተኩራል:: የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በራዕይ 4:1 ላይ ይሆናል:: አሁን ላለችው ቤተ ክርስቲያን ከራዕይ 4:1 የተለየ የመነጠቂያ ቦታ የለም:: ራዕይ 7:13-14 የመከራውን ዘመን ቅዱሳን መነጠቅ፣ ራዕይ 7:1-8 እና 14:1-3፣ 12:5 የ144000 አይሁዶችን መነጠቅ፣ ራዕይ 11:12 የሁለቱን ነቢያት መነጠቅ የሚያመለክት ከሆነ ራዕይ 4:1 የቤተ ክርስቲያንን መነጠቅ የሚያመለክት ለመሆኑ ምንም አያጠራጥርም::

የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በራዕይ 4:1 ላይ ስመሆኑ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከታሪክ ማስረጃ ማግኘቱ ትክክል ሊታምን ይገባል:: ስለሆነም የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት::

### 6.2.2.1. ..ከዚያ በኋላም.. የተሰኘው ሐረግ

..ከዚያ በኋላም.. የሚለው በራዕይ 4:1 ላይ የተጠቀሰው ሐረግ የሚያመለክተው በዮሐንስ ራዕይ ከምዕራፍ 1-3 የሚታዩ: የሚደረጉና የሚነገሩ ነገሮች ወይም ትዕይንቶች ከተፈጸሙ በኋላ ያለውን ድርጊት የሚጠቁም ነው:: ..ከዚያ በኋላም.. የሚለው ሐረግ ከቤተ ክርስቲያን በኋላ ወይም ስለ ቤተ ክርስቲያን የተነገረው ሁሉ ከሆነና ከተፈጸመ በኋላ ወይም የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከሆነ በኋላ የሚለውን ሃሣብ ሁሉ ያካትታል::

ከራዕይ 2-3 የተነገረው ትንቢት ሁሉ በዮሐንስ ዘመን በነበሩት ሰባቱ ቤተ ክርስቲያናት ላይ ብቻ ያተከረ አይደለም:: ሰባቱ ቤተ ክርስቲያናት ታሪካዊ ዕውነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በትንቢታዊ መልኩ ደግሞ በመላው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ዘመንና ህልውና ሊገጥሙ ስለሚችሉት ሁነቶችም በምሳሌነት የቀረቡ ናቸው:: የቤተ ክርስቲያን ዘመን እስካበቃ ድረስ በዓለም የሚመሰረቱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ሁሉ ሊገጥማቸው ያለ ባህሪና አሰራር በዋና ደረጃ በእነዚህ በትንሹ እስያ ባሉት ቤተ ክርስቲያናት ተካትቶ ቀርቧል:: የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈ ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፏል ስለሚል ለእነርሱ የተጻፈውን በማንበብ እኛም ልንጠነቀቅ ይገባል::

እግዚአብሔር ለሰባቱም ቤተ ክርስቲያናት መልዕክቱ እንዲተላለፍ ሲያደርግ ቢያንስ ሰባት ያህል ደረጃዎችን የያዘ እውነት በውስጠ አስቀምጦ ነው:: ለምሳሌ 1. ስለ ክርስቶስ ማንነት የሚገልጡ ስሞችን 2. የቤተ ክርስቲያናቱን ብርቱ ጎንና 3. ደካማ ጎን 4. ማስጠንቀቂያ 5. የመንፈስ ቅዱስን መልዕክት ስለመቀበል 6. የንስሐ ጥሪ 7. ማበረታቻና ሽልማት ይገኙ ሉ:: በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ያሉትን ቤተ ክርስቲያናት ስንመለከት



በአብዛኛው ከላይ ከተጠቀሱት ሰባት ደረጃዎች የራቁ አይደሉም:: አንዳንዶች ምናልባት አይመስከተንም ማለት ይችሉ እንደሆን ራሳቸውን በትክክል መመዘን ከቻሉ አይከለከሉም:: ሆኖም ግን የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ልብና ኩላሊት መርማሪ ክርስቶስ ነው:: ራዕይ 2:23:: ከላይ የተጠቀሱት ሁነቶች በሙሉ ወይም በከፊል ከተፈጸሙ በኋላ የመነጠቅ ጊዜ ሲሆን አሁን ያሰችው የቤተ ክርስቲያን አኗኗር ያበቃል ማለት ነው:: ስለሆነም በዘመኑ ያለን ቤተ ክርስቲያናት በሙሉ ማንነታችንን በጥንቃቄ መመርመር አለብን::

..ከዚያ በኋላም.. ሲል ከቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በኋላ መሆኑን ያመለክታል:: ይህ ከሆነ እስከ ዛሬ ድረስ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ አልሆነም:: ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ዘመን አሁን ካለ ..መነጠቁ.. ወደፊት ይሆናል:: መከራውም አሁን ካልጀመረ እርሱም ወደፊት ይሆናል ማለት ነው:: የቤተ ክርስቲያን ዘመን (ራዕይ 2-3) ከተፈጸመ በኋላ በራዕይ 4:1 መነጠቅ ይሆናል:: መነጠቅ ከሆነ በኋላ ደግሞ ከራዕይ 4 ና 5 እንደምናየው ስተነጠቁት ቅዱሳን በሰማይ ፕሮግራም ይያዛል ማለት ነው::

### 6.2.2.2. ..በሰማይ የተከፈተ ደጅ.. (በር) የሚለው ሐረግ

ይህ ..በሰማይ የተከፈተ ደጅ.. የሚለው ሐረግ በቀጥታ የሚያመለክተው ደጁ በሚከፈትበት ወቅት በምድር ላይ በቀጣይነት ከሚፈጸሙ ነገሮች ጋር የተያያዘ ታሪክን ለመግለጽ መሆኑን ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስድስት ያህል ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች ሰማይ ተከፍቶ አይተዋል:: ከእነዚህም ውስጥ፣

6.2.2.2.1. ሕዝቅኤል (1:1) ሰማይ የተከፈተበት ምክንያት ራዕይን ከእግዚአብሔር ለመቀበል

6.2.2.2.2. ጌታ ኢየሱስ (ማቴ.3:16፣ ማር.1:10) ሰማይ የተከፈተበት ምክንያት ከእግዚአብሔር አብ ስለ ጌታ ማንነት: ስለ ሰው ልጆችና ስለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል መውረድ ምስክርነት ስመስጠት፤

6.2.2.2.3. ናትናኤል (ዮሐ.1:51) ሰማይ የተከፈተበት ምክንያት የእግዚአብሔር መላዕክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ለማሳየት፡

6.2.2.2.4. እስጢፋኖስ (የሐዋ.7:56) ሰማይ የተከፈተበት ምክንያት የአብና የወልድ ለእስጢፋኖስ መጽናኛ መታየት

6.2.2.2.5. ጴጥሮስ (የሐዋ.10:11) ከእግዚአብሔር ለጴጥሮስ መልዕክት ለማስተላለፍ (ምልክት ለማሳየት)

6.2.2.2.6. ሐዋርያው ዮሐንስ (ራዕይ 4:1፣ 11:19፣ 19:11)

በራዕይ 4:1 ላይ ግን የሰማይ ደጅ ለምን ተከፈተ ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ ለዮሐንስ መልዕክት ለማስተላለፍ እንደሆነ ነው:: የተላለፈለት መልዕክት፣ወደዚህ ውጣና ሲል ከምድር ወደ ሰማይ እንዲወጣና ቀጣዩን መልዕክት እንዲቀበል ነው:: ይህ ቀጣይ መልዕክት ምንድን ነው? ዮሐንስ ወደ ሰማይ የወጣው በዚህ አካሉ አይደለም፤ በመንፈስ ነው:: በመንፈስ ከሆነ ይህ ለምን ተፈጸመ ስንል የቤተ ክርስቲያንን የቅዱሳንን ወደ ሰማይ መሸጋገር የሚተነብይን (የሚገልጽን) እውነት በውስጡ እንደያዘ እናገኛለን:: በራዕይ 2 እና 3 ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ ሁሉ ነገር ከተፈጸመ በኋላ የሰማይ ደጅ የተከፈተው ያለ ምክንያት አይደለም:: በራዕይ ከ1-3 ባለው ትንታኔ ከሰማይ መልዕክት ሲመጣ ሐዋርያው ዮሐንስ መልዕክቱን የተቀበለው ወደ ላይ ሳይወጣ ከሆነ ልዩ ትዕይንት ከሌለ ለምን ወደ ላይ መውጣት አስፈለገ?

ራዕይ 19:11ን ስንመለከት ሰማይ የተከፈተበት ምክንያት ከመጀመሪያው መነጠቅ እስከ መጨረሻው መነጠቅ በበጉ ሰርግ ተካፋይ የሆኑት ቅዱሳን በሰማይ የሰርጉን ስርዓት እንደጨረሱና ወደ ምድር መመለሳቸውን ለማመልከት ነው:: ከእነዚህ ጥቅሶች እንደምንረዳው ሰማይ ሲከፈት በሰማይና በምድር መካከል የድምጽ፣ የራዕይ ወይም የእንቅስቃሴ ግንኙነት እንደሚሆን ነው:: ስለሆነም በራዕይ 4:1 ላይ ሰማይ ተከፍቶ ከታየ



ከራዕይ 2 እና 3 በኋላ ለቤተ ክርስቲያን መነጠቅ መንገድ እንደሚዘጋጅ ግንኙነትም እንደሚሆን ያመለክታል::

የሥነ ከዋክብት ጥናት ማስረጃ

የመጽሐፍ ቅዱሳችን ደራሲ ሁሉን የሚያውቅ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስመሆኑ ከሚያስረግጡልን እውነቶች ውስጥ በቅርብ የተገኘው የሥነ-ከዋክብት ተመራማሪዎች መረጃ ነው:: ብዙ የዓለም አዳዲስ የሚመስሉ ግኝቶች አስቀድመው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተተንብየዋል:: ዳን. 12:3-4:: ምርምርንና ዕውቀትን መሰረት በማድረግ በአሁኑ ጊዜ ሳይንቲስቶች ብዙ ግኝቶችን ለማቅረብ ሞክረዋል:: ከእነዚህም ውስጥ ከአራቱ የምድር ሰማያዊ ማዕዘናት ሦስቱ በከዋክብት ክምችት የተሞሉ ሲሆኑ አንደኛው ማስትም ሰሜናዊው ክፍል ክፍት የመሆኑ ጉዳይ ነው:: ይህ የከዋክብት አጥኚዎች በሰሜን በኩል ያገኙት ክፍተት ዲያሜትሩ 16 ትሪሊየን ማይልስ መሆኑን አረጋግጠዋል:: ይህ በሰማይ የሚገኘው ክፍተት በአሁኑ ዘመን አስትሮኖመሮቹ (የከዋክብት አጥኚዎቹ) ከማግኘታቸው በፊት እግዚአብሔር በመንፈሱ ለባሪያዎቹ (ለቅዱሳን አገልጋዮቹ) ገልጾ ነበር:: ከእነዚህም ውስጥ፣

በኢዮብ 26:7 ላይ ..እግዚአብሔር ሰሜንን በባዶ ስፍራ ላይ ይዘረጋል.. ይላል:: በመቀጠልም በዚሁ በሰሜን በኩል የሚያስፈራ ግርማ ያለው ወርቅ የሚመስል ብርሃን እንደሚወጣ ይገልጻል:: ይህም ጌጠኛ ወርቅ መሳይ ብርሃን ጌታ ኢየሱስ ነው::

በኢሳ. 14:13-14 ደግሞ የእግዚአብሔር ዙፋን በሰሜን በኩል መሆኑንና ሰይጣንም በሰሜንም ዳርቻ እቀመጣለሁ ሲል ከምድር ወደ እግዚአብሔር ዙፋን አቅጣጫ ትኩረት ማድረግንና መንገስን እንደፈለገ ያመለክታል::

በኢሳ.41:25 ደግሞ ..እግዚአብሔር አንዱን ከሰሜን አነሳሁ፣ መጥቷልም.. ይላል:: ይህ ከሰሜን የሚመጣው ማንነት ከምድራዊ ፖለቲካ ጋር ካልታያያዘ በስተቀር ጌታ ኢየሱስን የሚያመለክት ነው::

ይህንን ጥቅስ በማስረገጥ ሕዝቅኤል ደግሞ በምዕራፍ 1:4 ላይ ..እነሆ ከሰሜን በኩል አውሎ ነፋስና ታላቅ ደመና የሚበርቅም እሳት ወጣ ... የወርቅ ምስያ ነበር.. በማለት ጽፏል:: በዚህም ምዕራፍ ውስጥ ሕዝቅኤል ኢሳይያስ ባየው ክብር ዓይነት የእግዚአብሔርን ክብር አይቷል:: በዚህ የሰሜናዊ ክፍል ክፍተት ውስጥ ከአስትሮኖመሮች አንዱ ፕሮፌሰር ሴአርኪን እንደገለጹት አስደናቂ ነገር እየታየ መሆኑን ነው:: ይህም አስደናቂ ነገር ግሩም የሆነ ውበትና ቀለሙ በምድር ተወዳዳሪ የሌለው፣ እንደ መስታዎት አንጸባራቂ ወንዝ፣ በከበረ ድንጋይ የተሰሩ የሚያበሩ ምሰሶች፣ በዕንቁና በብዙ ሚሊየን አልማዝ ከተሰራ ግድግዳ በስተጀርባ አንጸባራቂ ብርሃን መሰል ከተማ ከበስተሰሜኑ ኦርዮን ባሻገር መኖሩን አረጋግጠዋል:: ይሄ የሰሜን ጉዳይ ምን ይሆን? እስቲ ምርምራችንን እንቀጥል! ሌላ ነገርስ ይኖር ይሆን?

ከዚህ መረጃ የምንረዳው ነገር ይኖራል:: ሁሉን ቻይ፡ ሁሉን አዋቂ፣ በሁሉ ቦታ ተገኚና ዘላለማዊ ባህሪ ያለው እግዚአብሔር ለኢዮብ፣ ለሕዝቅኤልና ለኢሳይያስ ሰሜናዊው የሰማይ ክፍል ክፍት መሆኑን፣ የእግዚአብሔርም የዙፋን ክብር በስተ ሰሜን በኩል መሆኑንም ገልጾላቸዋል:: ለሐዋርያው ዮሐንስ ግን በየትኛው አቅጣጫ መሆኑን ባይገልጽለትም (አልተጻፈም) ሰማይ ክፍት ሆኖ በራዕይ 4:1 እና 19:11 ላይ አሳይቶታል:: ከእነዚህ ጥቅሶች ሰሜናዊው ክፍል ከከዋክብት በከፍተኛ ደረጃ ነጻ የሆነው የእግዚአብሔር ብርሃን ያለበት፣ ዙፋኑም በዚያ ያለ፣ ወደፊትም ከሰማይ ወደ ምድር የሚመጣው ከዚሁ አቅጣጫ መሆኑን ነው:: ይህም ደግሞ በእግዚአብሔር ሰዎች ብቻ ሳይሆን የዓለም ሳይንቲስቶችም በደረሱበት ደረጃ ማረጋገጥ ችለዋል:: በራዕይ 4:1 ላይ የተጠቀሰው ..የተከፈተ ደጅ.. የሚለው ሐረግ የያዘው ሃሣብ በእግዚአብሔር ዙፋንና በምድር መካከል ግንኙነት



መደረጉን ነው:: ግንኙነቱም ከቤተ ክርስቲያን ዘመን (ከራዕይ 2 እና 3) በኋላ መሆኑንና ቤተ ክርስቲያንም በዮሐንስ 14:1-3 እንደተጠቀሰው ልትወሰድ መንገድ መዘጋጀቱን የሚያመለክት ነው::

## 6.2.2.3. ..ወደዚህ ውጣና.. የሚለው ሐረግ

ጌታ ኢየሱስ ከራዕይ 1:3 ያለውን ክንዋኔ ዮሐንስ በምድር በነበረበት ጊዜ አስተላልፎታል:: ሆኖም ግን በራዕይ 4:1 ላይ ለምን ..ወደዚህ ውጣና... ከዚህ በኋላ የሚሆነውን አሳይሃለሁ አለው? ቀድሞ እንዳስተላለፈለት ባለበት ሁኔታ ወደላይ ሳይወጣ ለምን አላስተላለፈለትም? ይህ የሚያመለክተን የዮሐንስ ቦታ መቀየር (ወደ ላይ መውጣት-ለመውጣቱም የበር መከፈቱ ጉዳይ) ወደፊት መከራ የሚጀምርና አስጨናቂ ዘመን የሚቀጥል በመሆኑ ከመሆኑም በፊት ሎጥና ኖህ ከጥፋት እንደተወሰዱ ለቤተ ክርስቲያን መነጠቅ/መወሰድ ምሳሌያዊ ነገርን ለመተው እግዚአብሔር ያዘጋጀው እንደሆነ ቢተረጎም ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ይስማማል እንጂ አይቃረንም::

## 6.2.2.4. ..ቤተ ክርስቲያን.. የሚለው ቃል አለመኖር

በራዕይ 4:1 ላይ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ለመሆኑ ለማስረጃነት ከሚቀርቡት ሐሳቦች ውስጥ አንዱ ..ቤተ ክርስቲያን.. የሚለው ስም በመከራው ዘመን ማለትም ከራዕይ ምዕራፍ 6-19 ውስጥ አንዴም አለመጠቀሱ ነው:: ..ቤተ ክርስቲያን.. የሚለው ስም (ቃል) ከራዕይ ምዕ. 1-3 ውስጥ 19 ጊዜ ተጠቅሷል:: ከራዕይ 6-19 አለመጠቀሱ ግን የሚያመለክተን የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ የመከራው ዘመን ከመጀመሩ በፊት በራዕይ 4:1 ላይ መፈጸሙን ነው:: ቤተ ክርስቲያን ለምን ከራዕ. 6-19 ትዕይንት ውስጥ አልተጠቀሰችም? ይህንን ቀጥሎ ካለው ታሪካዊ ማስረጃ እስቲ እንመልከት::

በ..ሴሎ.. ቤተ ክርስቲያን ኮንፍራንስ ቢዘጋጅና ለሰባኪነት የተጋበዘው ሳኦል ቢሆን አገልጋዩም ሳይመቸው ቢቀር የፕሮግራሙም ዝግጅት በሙሉ በቪዲዮ ቢቀረጽና የቪዲዮውን ቅንጅት ሌሎች ቢመለከቱ ሳኦል በቪዲዮው

ውስጥ ይታያል አይታይም? መልሱ ለሁላችንም ግልጽ ነው:: ለባኪው ፈጽሞ ሲታይ አይችልም:: ለባኪው ሳኦል ያልታየበት ምክንያት በፕሮግራሙ ላይ ባለመገኘቱ ነው:: ስለሆነም የመከራው ዘመን በቅድመ መከራ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ስለማይመለከት ነገር ግን በእስራኤልና በአህዛብ እንዲሁም በመከራው ዘመን ቅዱሳን (በመከራው ዘመን ቤተ ክርስቲያን) ላይ ያተከረ በመሆኑ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በትንቢት መልኩ በራዕይ 4:1 ላይ ተከናውኗል ማለት ነው:: በተግባር ወደ ፊት ይቀጥላል::

## 6.2.3. የ24ቱ ሽማግሌዎች በሰማይ ዙፋን መገኘት

እነዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ በ24ቱ ዙፋኖች የተቀመጡት ሽማግሌዎች የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን (የቤተ ክርስቲያን) ቅዱሳን ተወካዮች ናቸው:: በእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት ስልጣን በዘመናት መካከል ለእግዚአብሔር ክብር የቆሙ ታማኝ አገልጋዮች ስለሆኑ ተመርጠው በእግዚአብሔር ፊት ለመቀመጥ ችለዋል::

ቁጥራቸው 24 የሆነበትን ምክንያት በእርግጠኝነት ለመጥቀስ ቢያስቸግርም ከ1ኛዜና.24:1-9 የብሉይ ኪዳን የቤተ ክህነት አገልጋዮች ቁጥር 24 መሆኑን ማየት ይቻላል:: በተጨማሪም በራዕይ 21:10-14 በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ደጆች ላይ የ12ቱ የጌታ ደቀ መዛሙርትና የ12ቱ የእስራኤል ነገዶች ስም መጻፉና በአንድነት ቁጥራቸው 24 መሆኑ ሌላኛው ማስረጃ ነው:: ሌሎችም አመለካከቶች አሉ::

በሰማይ የታዩት እነዚህ 24 ሽማግሌዎች ቅዱሳን መላዕክት እንጂ ቅዱሳን ሰዎች አይደሉም የሚል አከራካሪ ሃሣብም አለ:: እነዚህ ሽማግሌዎች መላዕክት አይደሉም:: ላለመሆናቸውም የሚከተሉትን እውነቶች መመልከቱ ይጠቅማል::



### 6.2.3.1. ሰው ስሆነ ሽማግሌና ለመላዕክት የተሰጡት መጠሪያ ስሞች መለያየት

«ኢልደር» በአማርኛው ..ሽማግሌ.. የሚለው ቃል በራዕይ መጽሐፍ በግሪኩ ሲታይ ..ፐሪስቡቴሮስ.. በቀጥታ የሚያመለክተው ሰው ለሆነ ፍጡር የተሰጠ ስምን እንጂ መላዕክትን አይደለም:: ለመላዕክት የቆመው የግሪኩ ቃል ..አጌሎስ.. የሚለውና ..ማላክ.. የሚለው የእብራይስጡ ቃል ተመሳሳይነት ሲኖራቸው መንፈሳዊ ኃይላትን ያመለክታሉ:: በራዕይ 4:4 ላይ ለተጠቀሱት ሽማግሌዎች የቆመው ቃል ..ፐሪስቡቴሮስ.. እንጂ ..አጌሎስ.. ወይም ..ማላክ.. ስላልሆነ ፈጽሞ ቅዱሳን መላዕክትን አያመለክትም:: ስለዚህ የራዕይ 4:4ቱ ሽማግሌዎች ከመነጠቅ በኋላ በሰማይ በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ የሚቀመጡ የብሉይና የአዲስ ኪዳን ቅዱሳን ተወካዮች ናቸው:: ይህም ከከፈሉት ዋጋ አንጻር የተሰጣቸው ቦታና ክብር ሊሆን ይችላል::

### 6.2.3.2. ነጭ ልብስ መልበሳቸው

የራዕይ መጽሐፍ ብዙው ክፍል ነጭ ልብስ መልበስ የተሰጠው በክርስቶስ ኢየሱስ ለተዋጁ ቅዱሳን እንደሆነ አጠንክሮ ይገልጽልናል::ለምሳሌ፤በራዕይ 3:5 ላይ ድል ለነሱ አማኞች የነጭ ልብስ ሽልማት፣ ቁ. 18 ላይ ነጭ ልብስ የቅዱሳን የንጽህና ህይወት አቋም፤በራዕይ 6:11 ደግሞ ስለክርስቶስ ለሚገደሉ፤በራዕይ 7:9 ደግሞ ከመከራው ለተዋጁ ቅዱሳን፤በራዕይ 19:8 እና ቁ. 14 ..ለበጉ ሚስት.. ማለት በዘመናት ተነጥቀው ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለገቡ ሁሉ የተሰጠ መሆኑን እናያለን:: ነጭ ልብስ የቅዱሳንን የጽድቅ ሥራ ያመለክታል:: እነዚህ ነጩን ልበስ የለበሱት ቅዱሳን ናቸው:: የተገኙትም በላይ በሰማይ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ነው:: የቀሩት ቅዱሳን ነጭ ልብስ የመልበስ ስልጣን እንደተሰጣቸው ሁሉ እነዚህ ሽማግሌዎች ከሰዎች የተዋጁ ስለሆነ ድል ስላደረጉ ነጩን ልብስ ለብሰዋል::

#### 6.2.3.3. ከመላዕክት ተለይተው መሰለፋቸው

የራዕይን መጽሐፍ በጽሞና ስንመለከት በዙፋኑ ዙሪያና ፊት ያሉትን ክፍሎች ዘርዝሮ ይነግረናል:: በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያና ፊት 24ቱ ሽማግሌዎች፣ አራቱ እንስሳት፣ ከታላቁ መከራ የመጡ ቅዱሳን፣ ቅዱሳን መላዕክትና 144000 አይሁዶች (በገና ደርዳሪዎች) ይገኛሉ:: ይህንንም ከራዕይ 5:11፤ 7:13 እና 14:1-3 መረዳት እንችላለን:: ራዕይ 5:11ን ስንመለከት ቅዱሳን መላዕክት የሚገኙት በዙፋኑ፣ በእንስሶቹና በሽማግሌዎቹ ዙሪያ ነው:: ስለሆነም በራዕይ 4:4 የተጠቀሱት ሽማግሌዎች ከመከራው በፊት የተነጠቁት ቅዱሳን አማኞች ተወካዮች እንጂ መላዕክት እንዳይደሉ የእግዚአብሔር ቃል ያስገነዝበናል::

#### 6.2.3.4. ያላቸው አክሊልና በዙፋን መቀመጣቸው

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ አክሊል (ዘውድ) እና ዙፋን ሲጠቀስ ብዙው እጅ ድል ካደረጉ በኋላ ከሚሸለሙ ቅዱሳን ጋር በተያያዘ ነው:: በተለይ በራዕይ መጽሐፍ ውስጥ መላዕክት በዙፋን ተቀምጠውና አክሊል ተጭኖላቸው ፈጽሞ አልተጠቀሰም:: ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በማቴ. 19:28፤ ራዕይ 3:21 እና 20:4 እንደምናነበው በዙፋን መቀመጥ የተሰጠው ድል ላደረጉ ቅዱሳን ሰዎች ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በኢሳ. 14:12-14 እና ቆላ. 1:16 ውስጥ መላዕክት ከዙፋን ጋር በተያያዘ መልኩ ተጠቅሰዋል:: ይህም ቀድሞ ከነበረው የእግዚአብሔር አሠራር ጋር በተያያዘ እንጂ ከተጋድሎ በኋላ በሽልማት መልክ ስለሚሰጠው ሥልጣን አይደለም:: በተጨማሪም ከ1ኛቆሮ.9:25-27፤ ከራዕይ 2:10 እና ከ2ኛጢሞ. 4:8 የምንረዳው ለቅዱሳን አክሊል የሚሰጠው ታግሎ ከማሸነፍ በኋላ እንደሆነ በግልጽ መረዳት ይቻላል:: ህይወታቸውም ተሰውቶ ከሞት የተነሱም ናቸው:: ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በራዕይ 4:4 የተጠቀሱት ሽማግሌዎች ከመከራው በፊት የተነጠቁ ቅዱሳን ተወካዮች መሆናቸውን ማየት ይቻላል::



እነዚህ 24ቱ ሽማግሌዎች የመከራው ዘመንና 144000 እስራኤላውያን ሳይነጠቁ በፊት የተነጠቁት ቅዱሳን አማኞች ጉባኤ ተወካዮች ሊሆኑ ይችላሉ:: ሆኖም ግን መቼና የት እንደነበሩ እነማን እንደሆኑም ለማወቅ ይቸግራል::

### 6.2.4. የኖህና የሎጥ ዘመን መጽሐፍ ቅዱሳዊና ታሪካዊ ምስክርነት

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዓለም መጨረሻና ስለራሱ ወደዚህ ዓለም መመለስ ትንቢት ከተናገረባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ አንዱ ሉቃስ 17 ነው:: በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በ26ኛውና በ30ኛው ቁጥር ላይ ጌታ በኖህና በሎጥ ዘመን የሆነው ሁሉ እርሱም ሲመጣ እንደዚያው እንደሚሆን ገልጧል:: የዚህን ዝርዝር ለማወቅ ስለ ምልክቶች በዝርዝር መመልቱ የሚጠቅምና መልካም ነው::

ከኖህና ከሎጥ ዘመን ጋር ከተያያዙት ዐበይት ነጥቦች ውስጥ በይበልጥ መጥቀስ የምፈልገው የቅዱሳንን ሁኔታ ብቻ ነው:: የማያምኑት ክፍሎች ሲበሉ ሲጠጡ ሲዘፍኑ፣ ሲያገቡ ሲጋቡ፣ ሲሸጡ ሲገዙ፣ ቤት ሲሰሩና ሲተክሉ ነበር:: ኖህ ሎጥና ቤተሰቦቻቸው ግን በአመጸኛ ሥራቸው ጻድቅ ነፍሳቸውን ያስጨንቁ ነበር::2ኛጴጥ. 2፣7-8:: የሰዎቹ የሴሰኝነት ኑሮና የአመጸ ህይወት እነዚህን ጻድቃን ለመናቅና ለመወገዝ አሳልፎ ሰጥቷቸው ነበር:: ይገፉም ነበር:: በህብረተሰቡም ዘንድ የተናቁ ነበሩ:: በኃጢያተኞች መካከል ሲኖሩ በማያዩትና በማሰሙት፣ በእነዚህ ሁለት ታላላቅ ነገሮች ነፍሳቸው ከፍተኛ ችግር ውስጥ ገብታ ነበር:: በጴጥሮስ መልዕክት ውስጥ ጻድቅ ሎጥም በመካከላቸው ሲኖር ሳለ እያየና እየሰማ ዕለት ዕለት በአመጸኛ ሥራቸው ጻድቅ ነፍሱን አስጨንቆ ነበርና እንደተባለ ስቃያቸውም የሚቋረጥ አልነበረም:: ዕለት ዕለት ይሰቃዩ፣ ይጨነቁ ነበር:: ውጤቱስ? እነዚህን ጻድቃን እግዚአብሔር አዳናቸው ያዳነበትን መንገድ ስንመረምር እንደሚከተለው ነበር::

6.2.4.1. <u>ኖህና ቤተሰቡ</u>

ኖህ ሊመጣ ስለነበረው የእግዚአብሔር ፍርድ ከእግዚአብሔር መልዕክት በደረሰው ጊዜ ተቀበለ:: በታዘዘው መሠረት በወቅቱ የነበረውን የኃጢአተኞች ነቀፌታ ወደ ጐን በመተው መርከብ መስራት ጀመረ:: ቀኑም ሲደርስ ከቤተሰቦቹ ጋር ወደ መርከቡ ገባ:: ከእግዚአብሔር መመሪያ ተቀብሎ በሰራው መርከብ ከአስቃቂው የውኃ ጥፋት ዳነ::

እግዚአብሔር ለኖህ በሰራው መርከብ ላይ እንኳን በሩን ለመዝጋት ሥልጣን አልሰጠውም ነበር:: ዘፍ. 7:16:: የእግዚአብሔር ቁጣ ከተፈጸመ በኋላ ግን ኖህ የመርከቡን በር ለመክፈት ችሏል:: እግዚአብሔር ለምን በሩን ዘጋ? ኖህን እንዲዘጋ ለምን አልፈቀደለትም? በህዝቡ በደልና ሐጢአት እግዚአብሔር እንደተቆጣ፣ ሁሉንም ሊያጠፋቸው እንደወሰነና ቃሉን ሊፈጽም እንዳሰበ ያመለክታል:: ምናልባትም የኖህ ርህራሄ በሩን ሊያስከፍተውም እንደሚችል አስቦ ሊሆን ይችላል:: ጻድቅ ሰው ብዙ ጊዜ እንደ እግዚአብሔር ልብ ላይራራና ላይጨክን ይችላልና::

ዝናቡ መዝነብ፣ ቀላዩም መነደል ሲጀምር ሰዎችም ሲለቃዩ እንዲያይ ለኖህ አልተፈቀደለትም:: ለምን? ኖህ አስቀድሞ ኃጢአተኛው ዓለም ሲበላ ሲጠጣ በየዓይነቱ ሲደለት ተጨንቆ ነበር:: አሁን ግን ወደ እረፍት ገብቷል:: አሁን ሊያዝንም ፈጽሞ አይገባውም:: አስቀድሞ ሥራቸውን በማየትና ንግግራቸውን በመስማት እጅግ ብዙ ተሰቃይቷል:: በእግዚአብሔር ኃይል ስለተጠበቀና ወደ እረፍት ስለገባ ወደ ኋላ ሊመለስ አልተፈቀደለትም:: የጭንቀት ዘመን አልፏል:: የሥነ ልቡና ስቃይ ሊቀበል ፈጽሞ አላስፈለገም:: መዳን መዳን ነውና::

6.2.4.2. <u>ሎጥና ቤተሰቡ</u>

እግዚአብሔር የሰዶምና የገሞራን ከተሞች ለማጥፋት ወሰነ:: የእነዚህ ከተሞች ህዝብ ከኖህ ዘመን የበለጠ በርኩሰት የበዙበት ዘመን ነበር:: እግዚአብሔር ከቀድሞ ጀምሮ ብዙ ታግሷቸዋል:: የሎጥን የቅድስና ህይወት አይተው ለመመለስ ፈጽሞ ፈቃደኞች አልነበሩም:: ዘፍ. 19:1-11:: ሰማያዊና መንፈሳዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን በጐ ነገር የሚፈልግ ልብ አልነበራቸውም:: በአመጸኛ ሥራቸው ጌታን ያስቆጡ ስለነበር በኖህ ዘመን ኃጢአተኛውን ዓለም እንደ ቀጣ የሎጥንም ዘመን ሰዎች ሊቀጣ ተነሳ::

እግዚአብሔር ሎጥንና ቤተሰቡን የሚያድንበት መንገድ አዘጋጀ:: ሎጥ የእግዚአብሔርን የማዳን ዓላማ ቢረዳም እንደተገለጠለት ባስቸኳይ እርምጃ አልወሰደም ነበር:: ሎጥ ለአካባቢው ዘመዶቹ ሁኔታውን አሳወቀ፣ የእነርሱ የቸልተኝነት አቋም ልቡን አዛለበት:: ቶሎ ሊወጣ አልቻለም:: በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር በድጋሚ በመላዕክቱ በኩል እጁን ይዞ ከጥፋት ከተማ ሊያወጣው ቻለ:: ሎጥ ከሰዶም ከመውጣቱ በፊት እግዚአብሔር ከሰጠው ትዕዛዛት አንደኛው በጣም ለየት ያለ ነበር:: ይኸውም፤
...ወደ ኋላህ አትይ... የሚለው ነበር ::ዘፍ. 19:17:: ለምን ይህንን ትዕዛዝ ሰጠው? እግዚአብሔር ይህችን ከተማ በእሳት ማጋየት ከጀመረ፣ ሁሉ ነገር እየነደደ ከሆነ በዚህ ወቅት ሎጥ ወደ ኋላ መለስ ብሎ ቢመለከት ምን ይገጥመው ነበር? የከተማይቱ መቃጠል ጭንቀት ሃዘንና ሁከት ያመጣበታል:: ወይም ደግሞ እሳቱ ካልነደደ ለካስ ውሸት ነው፤ ቃዥቼ ሊሆን ይችላል:: ወደ ከተማዬ ልመለስ ሊልም ይችል ነበር::

የሎጥ ሚስት ከህያውነት ወደ ግዑዝነት በመለወጥ ጨው አምድ ሆነች:: ለምን? ይህ የደረሰባት በእውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል ላይ በመጠራጠርና በማመጺ ሊሆን ይችላል:: በተጨማሪም በከተማይቱ ላይ እየወረደ ያለው መቅሰፍት ያመጣባትን ድንጋጤ መቋቋም አቅቷት ሊሆን ይችላል:: ሎጥና የቀሩት ቤተሰቡ ግን ትዕዛዙን በመቀበላቸው ሊድኑ ቻሉ:: ዳኑ ማለት ፊት ለፊታቸው ለአመጸኞች ተዘጋጅቶ የነበረው የእግዚአብሔት ቁጣ ሳያገኛቸው ቀሩ፤ ተከለሉ፤ ተጠበቁ ማለት ነው::

በኖህና በሎጥ ዘመን የነበሩት ቅዱሳን ከዚህ አሰቃቂ ቁጣ ከዳኑ በሰው ልጅ ዘመን ደግሞ ልክ እንደዚሁ ከሆነ፣ እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑትን በተመሣሣይ ሁኔታ ያድናቸዋል 2ኛ ጴጥ.2:8:: እግዚአብሔር የሰው ፊት አይቶ አያደላምና:: ስለሆነም በዚህ ዘመን መጨረሻም ከራዕይ 6-1 ከተጠቀሰው ቁጣ ቤተ ክርስቲያንን ያድናል:: የሚያድንበትም መንገ ..መነጠቅ.. ነው:: የሚከተለውን ሠንጠረዥ እንመልከት::

| | የጠፉበት <u>ዘመን</u> | የዳኑት <u>ሰዎች</u> | የዳኑበት <u>መንገድ</u> |
|---|---|---|---|
| 1. | በኖህ ዘመን | እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ኖህና ቤተሰቡ | በኖህ መርከብ |
| 2. | በሎጥ ዘመን | ሎጥና ሁለት ልጆቹ | በመላዕክት እጅ |
| 3. | በሰው ልጅ ዘመን | ቅዱሳን (ቤተ ክ.) | በመነጠቅ (በጌታ መምጫ ጊዜ) |

እነዚህን ዘመናት ስንመለከት በሶስቱም ከፍተኛና ዓለም ዓቀፍ የጥፋት ጊዜአት ጌታ የተለያዩ የማዳኛ መንገዶች ነበሩት:: ደረጃቸውም ለየት ያለ ነበር:: የሰው ሐጢአቱ እየከፋ በመጣ መጠን የማዳኛ መንገዱም ከበድ እያለ መጥቶአል:: በሶስቱም ጊዜአት የማዳኛ መንገዶቹን የቀየሰው እግዚአብሔር ሲሆን የፈጸሙት ግን የተለያዩ ናቸው:: መርከብ የሰው እጅ ሥራ፡ መላዕክት ከመርከብ እጅግ የላቀ ጉልበት ያላቸው፤ መነጠቅን ደግሞ ተግባራዊ የሚያደረገው ክርስቶስ ከሁሉም እጅግ የላቀ ጉልበትና አቅም ያለው ናቸው::

### 6.2.4.3. <u>3ኛው በትንቢታዊ መልኩ ይታይ ሉቃስ 17: 26-30:</u>

በ6.2.4.2 ውስጥ ከተጠቀሱት የጥፋት ዘመናት ውስጥ ሶስተኛው የሰው ልጅ ዘመን ገና አልተፈጸመም:: ይህ ዘመን ለ2000 ዓመታት ያህል ቆይቷል:: በሰው ልጅ ዘመን (በጌታ መምጫ ጊዜ) በዳንኤል እንደተተነበየው (ዳን. 11:31፤ 12:11) የጥፋት እርኩሰት (የአውሬው አሰራር) በተቀደሰው ሥፍራበእስራኤል እኔ እግዚአብሔር ነኝ! በማለት ሲቆም የክርስቶስ መምጫ



እጅግ የተቃረበበትና በምድርም የሚቆምበትም ጊዜ እንደሆነ መረዳት ይቻላል:: ይህ ጊዜ በ2ኛጢ.ሞ. 3:13 እንደምናነበው የሰዎች ክፋት እየባሰ የሚሔድበት ጊዜ ይሆናል:: የጻድቃንንና የእግዚአብሔርን ልብ የሚያሳዝን የአመጽ፣ የኃጢአት ሥራ እጅግ የሚበዛበት ጊዜ ነው:: ይህንን ሁኔታ እግዚአብሔር ዝም ቢለው በጐ ነገር በክፉ ሊዋጥ ይችላል:: ይህ ደግሞ ከእውነት ውጭ ስለሆነ እግዚአብሔር አመጻን ሁሉ (እሰመታዘዝን) እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ደረጃ በደረጃ በፕሮግራም ክፉዎችን ይበቀላል:: በዚህ ጊዜ ግን እግዚአብሔር በእርሱ ያመኑትን ..የአምልኮ መልክ ብቻ ያልሆኑትን ያድናል..::

ታዲያ እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑትን እንዴት ነው የሚያድናቸው? ሠንጠረዡ እንደሚያሳየን በመነጠቅ ወዳዘጋጀላቸው ለማያዊ ስፍራ በመውሰድ ነው:: የመከራው ዘመን እስኪያልፍ በራዕይ 4:1 የተከፈተው በር በራዕይ 19:11 እስኪከፈት ዘግቶ በማስቀመጥም ነው:: ስለዚህ ኖህንና ሎጥን ቤተሰቦቻቸውንም ከአሰቃቂ ፍርዱ እንዳዳናቸው ከታላቁ መከራም እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ከመከራው በፊት ይወስዳል:: ስለሆነም የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከመከራው በፊት ይሆናል::

### 6.2.5. <u>ግልጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች</u>

እስከአሁን የተመለከትናቸው የቅድመ-መከራ መነጠቅ ማስረጃዎች ጥቂቶቹ በተዘዋዋሪ ሲሆኑ የቀሩት ደግሞ በቀጥታ የተቀመጡ ናቸው:: የሚከተሉት እውነቶች ግን ከመከራውና ከቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ጋር በተያያዘ ምንም የማያሻማ ግልጽ የሆነ መረጃን ማቅረብ የሚችሉ ናቸው::

### 6.2.5.1. <u>ሉቃስ 21:36</u>

በዚህ ክፍል ስለ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከመንካቴ በፊት የተያያዙ ሐረጐችን ይዘት መግለጽ እፈልጋለሁ:: የተጠቀሰው ዓረፍተ ነገር (እውነት)፡

..እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ፣ በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ ስትጸልዩ ሁልጊዜ ትጉ::.. የሚል ነው::

ጌታ ኢየሱስ ..ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ሲል በዚሁ ምዕራፍ ከቁጥር 5-35 የተዘረዘሩትን ለሰው ልጆች የማይበጁ አስከፊ ሁኔታዎች ለማመልከት ነው:: ደቀ መዛሙርቱ ይህንን ሁሉ ሲነግራቸው ለራሳቸውም ሆነ ከእነርሱ በኋላ ለሚመጡት ወገኖቻቸው በማሰብ ልባቸው ብዙ ሳይታወክ የቀረ አይደለም:: የሚሆኑትን ነገሮች በተለይ ከቁጥር 23-24 የተጠቀሱትን ሲያስቡ ልባቸው ታውኳል:: በዚህ ምክንያት ጌታ የማምለጫውን ዘዴ ነገራቸው:: ከሚመጣው አስቃቂ ሁኔታ መዳን ይቻላል በማለት ጳውሎስ ለተሰሎንቄ አማኞች እንደተናገረው በማረጋጋት፣ አጽናናቸው::

በታላቁ መከራ ዘመን የመንፈስን ዓይን የሚያሳውሩና ልብ የሚሰርቁ ሐሰተኞች ነቢያትና ክርስቶሶች፤ ጫፍ የደረሰ ጦርነትና የጦርነት ወሬ (ቀዝቃዛና የጋለ ጦርነት)፣ ሕዝብ በሕዝብ ላይ መነሳት (የእርስ በርስ ጦርነት) ረሃብና ቸነፈር፣ የመንግሥት በመንግስት ላይ መነሳት (የተለያዩ ብሔሮች ጦርነት)፣ የሐይማኖቶች መብዛትና መከፋፈል፣ እርስ በርስ አንዱ በሌላው ላይ ከጥላቻ ሙላት የተነሳ መነሳትና አሳልፎ መስጣጠት፣ ፍቅር ጭልጥ ብሎ ከብዙዎች መራቅ፣ ከፍተኛ የሆነ የሰውን ነፍስ የሚያስጨንቅ የተፈጥሮ አደጋ (የምድር ነውጥ፣ የውቅያኖሶች ማዕበል፣ እስከ 40 ኪሎ የሚመዝን የበረዶ ዝናብ በሰዎች ላይ ወዘተ እንደሚደርስ ጌታ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተናግሯል:: የእነዚህ ነገሮች ሁሉ መታያ ጊዜ ..እስከዛሬ ድረስ ያልሆነ እንግዲህም ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ እንደሚመጣ ተገልጿል::ማቴ. 24:21:: ጌታ ኢየሱስ ከእነዚህ ሁሉ ማምለጥ እንደሚቻል አስታውቋል::

ሌላኛው ሐሣብ ጌታ ኢየሱስ በዚህ ክፍል የተናገረው ***በፊቱ ስለመቆም*** ሁኔታ ነው:: ..በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ.. ሲል ይህ በፊቱ መቆም ምንድነው? ይህስ የሚፈጸመው የት ነው? ጌታ ከሞት ተነስቶ



ካረገበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን የሚገኘው በሰማይ በአብ ዘንድ ነው:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰማይ እስኪለቀቀው ድረስ ለቅዱሳኑ በመንፈሳዊ አካሉ አልታየም ::ሐሥ. 3:21::ከአሁን በኋላ ጌታ ለቅዱሳኑ የሚታየው በ1ኛተሰ. 4:17 መሰረት ከኋላኛው መለከት መነፋት በኋላ በአየር ስንነጠቅ ነው:: ለመጀመሪያ ጊዜም በፊቱ የምንቆመው በመነጠቅ ሰዓት ነው:: ከዚያ በኋላ በተለያዩ ሁኔታዎች በፊቱ ልንቆም እንችላለን:: በአንጻሩ ደግሞ በራዕይ 6:16-17 በጌታ ኢየሱስ ፊት መቆም የማይችሉም አሉ::

ለእኛ ለቅዱሳን በጌታ ፊት መቆም እጅግ የተከበረና ዘወትር ልንናፍቀው የሚገባ የልባችን ናፍቆት ነው:: ***<u>የዓለም ስውርና ግልጽ የክፋት ኅጹስ አሰራር ከውስጣችን ፍቆ ሊያወጣው የማይችል ሀያው ተስፋችን ሊሆን ይገባል</u>***:: ይህንን ማጨናገፍ ከቻለም ማስቀረት የዲያብሎስ መርህና ምኞት ነው:: ይህንን መገለጥና መታየታችንን እንኳን እኛ በእግዚአብሔር መስመር ያሉ ፍጥረታት ሁሉ የሚናፍቁት ጉዳይ ነው:: የእኛን በጌታ ፊት መቆም መላዕክት እንኳን ለማየት ይናፍቃሉ:: የሰማይ መላዕክት ስለምድር ሰዎች መዳን ይነገራቸውና ሐሴት ያደርጋሉ እንጂ እስከ አሁን አላዩንም:: ሉቃስ 15:7:10:: የእኛ በከበረው የጌታ ደም ከምድር መቤዠት (መዋጀት)፣ የጌታም እኛን ከአብ መቀበል በኤፌ. 5:27 እንደተጠቀሰው እኛን ለአብ ወስዶ በማቅረብ ፍጻሜ ይደመደማል:: ይህ ስጋችን ማንም ሊቀርብ በማይችል በድንቅ ብርሃን በሚኖረው በአብ ፊት መቆም ስለማይችል የጌታን ክቡር ስጋ እንዲመስል ይለወጣል (ፊልጵ. 3:21):: ከዚያም በአብ ፊት ይቀርባል በዚያም የጌታ ኢየሱስ የዘመናት ሥራ በእግዚአብሔር ቅዱሳን መላዕክት ፊት ይገለጣል:: ታላቅ መደነቅም ይሆናል:: ይህ ሁሉ የሚሆነው በሰማይ ነው::1ኛጴጥ. 1:12::

እንግዲህ ከላይ በተዘረዘሩት መሠረት ወደፊት በዓለም ኃጢአተኞች ከሚመጣው የእግዚአብሔር ቁጣ ማምለጥ (መሰወር) ይቻላል:: ይህም የሚቻለው በሰማይ ባለው ባልተገለጠው ሊመጣም ባለው በጌታ ኢየሱስ

በማመንና ፀንቶ በመቆም ነው:: ከዚህ ከመከራው በማምለጥ በሰማይ ባለው በጌታ ፊት መቆም የሚቻለው ..በመነጠቅ.. ስርዓት ውስጥ በማለፍ ብቻ ነው:: እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ነገር ይህ ሃሣብ በተለይ ከመከራው በፊት ለሚገኙት ቅዱሳን የቆመ (የተጠቀሰ) መሆኑን ነው:: በመከራው ዘመን የሚገኙ ቅዱሳን (የመከራው ዘመን ቤተ ክርስቲያን) ከእግዚአብሔር ቁጣ ይጠበቃሉ፤ አንዳንዶቹም በአውሬው ድል ይደረጋሉ፤ ድል በመሆንም ድል ያደርጋሉ:: በእግዚአብሔር ተቆጣጣሪነት በሰይጣን ቁጣ በጋለሞታይቱ አንገት እስከ መቆረጥ: መሰደድና ግድያ ይደርሰባቸዋል:: ራዕይ 13:10፤20:4-6:: ግማሾቹም በቅጽበተ ዓይን ተለውጠውና ከሞት ተነስተው ከመከራው ይነጠቃሉ:: ሆኖም ግን በመከራው ዘመን የሚኖሩ አማኞች የዚህ መነጠቅ ባለመብት የሚያደርጋቸው ትልቁ ነገር አብርሃም በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ይጸልይና ይማልድ እንደነበር በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ በትጋት መጸለይ ነው::

### 6.2.5.2. <u>1ኛተሰ.5:9.</u>

በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ ..እግዚአብሔር ለቁጣ አልመረጠንምና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ነው እንጂ ይላል:: ..ቁጣ.. የሚለው ቃል በቀጥታ የሚያመለክተው በአመጸኞችና በማይታዘዙ ሰዎች ላይ የሚደርሰውን ታላቅ መከራ፣ የእግዚአብሔር መቅሰፍትና በትር ነው:: ይህም ቁጣ በ1ኛተሰ. 5:2-3፤ በራዕይ 6:1-19፣ 21፤ እና በማቴ. 24:15-21 በዝርዝር ተገልጿል:: ይህ ቁጣ ከእግዚአብሔር በሰዎች ላይ የሚደርሰው ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ከእውነት ይልቅ ውሸትን ስለመረጡ ነው:: በዚህ ባህሪያቸው ሰዎች ራሳቸውን ለዚህ ቁጣ መርጠዋል:: ወይም ለይተዋል:: የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን እንዲድኑ ነበር::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በልዩ ልዩ ቦታ የእግዚአብሔር ቁጣ ሲወርድ ታይቷል:: ለምሳሌ፣



በ2ኛዜና 36:16 የአይሁድ ሕዝብ የእግዚአብሔርን እውነት ስላልተቀበሉ ቁጣው በህዝቡ ላይ ወጣ ውጤቱን ከቁጥር 17-23 ማየት ይቻላል:: በዚህ ጊዜ ግን ኤርምያስ የእግዚአብሔርን ቃል ስለሰማ ከጥቂቶች ጋር ተርፏል:: ቁጣው አላገኘውም ዘፀ. 22:24::

ዘሁልቁ 11:33-34 የእግዚአብሔር ቁጣ በህዝቡ ላይ ነደደ … እግዚአብሔርም ህዝቡን በታላቅ መቅሰፍት እጅግ መታ …::

2ኛዜና 12:12 … የእግዚአብሔር ቁጣ ፈጽሞ እንዳይጠፋው ከእርሱ ዘንድ ተመለሰ::

ራዕይ 6:16 … ከበጉ ቁጣ ሰውሩን

ራዕይ 6:17 … ታላቁ የቁጣው ቀን መጥቷልና …

ራዕይ 11:18 … አህዛብም ተቆጡ ቁጣህም መጣ::

ይህ ጥቅስ በተለይ (ራዕይ 11:18 እና 6:17) የእግዚአብሔር የቁጣ ቀንና ቁጣው (በትሩ ራዕይ 19:15) አስቀድሞ እንደተዘጋጀ ስለሰዎች መዳን ብቻ እግዚአብሔር ቁጣው እንዳይገለጽ እንደያዘው ያመለክታል::

ራዕይ 14:10 … እርሱ ደግሞ በቁጣው ጽዋ ሳይቀላቀል ከተዘጋጀው ከእግዚአብሔር ቁጣ ወይን ጠጅ ይጠጣል …

ራዕይ 14:19 … ወደ ታላቁ ወደ እግዚአብሔር ቁጣ መጥመቂያ ጣሉ …

ራዕይ 16:19 … የብርቱ ቁጣው ወይን ጠጅ የሞላበትን ጽዋ እንዲሰጣት በእግዚአብሔር ፊት ታሰበች::

ከላይ ከተዘረዘሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ውስጥ የእግዚአብሔር ቁጣ በአመጸኞች ላይ ሊገለጽ በዝ<u>ግጅት</u> ላይ እንዳለ ግልጽ ነው:: ከዚህ ቁጣ ጋር በተያያዘ የእግዚአብሔር እቅድ ወይም ፈቃድ በማቴ. 3:7፣ በሉቃስ 3:7 እና በራዕይ 18:3-5 እንደምናነብበው ሕዝቡ በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሁሉ ከኃጢአት እንዲለዩና እንዲድኑ ነው::

እንግዲህ ..እግዚአብሔር ለቁጣ አልመረጠንም.. ሲባል ከቁጣው ለመዳን ተጠርተናል፣ ተመርጠናል ማለት ነው ሮሜ. 5:9:: ስለሆነም ወደፊት የሚመጣውና በሐጢአተኛ ዓለም ላይ የሚፈስሰው የእግዚአብሔር ቁጣ ቤተ ክርስቲያንን አያገኝም:: አስቀድሞ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ይሆናል::

**6.2.5.3. 2ኛ ተሰ. 2:6-7**

በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ በሚስጢር ስለሚሰራው ሐሰተኛው ክርስቶስና በግልጽ እንዳይሰራ ስለሚከለክለው (ስለሚቋቋመው) ኃይል ጽፏል:: *የጻፈውም ቃል ..በገዛ ራሱ ጊዜም ይገለጥ ዘንድ የሚከለክለውን አሁን ታውቃላችሁ:: የአመጽ ሚስጢር አሁን ይሰራልና ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ::..* የሚል ነው::

..የሚከለክለው.. እና .. ከመንገድ እስኪወገድ.. የተሰኙት ቃላት ማንን እንደሚያመለክቱ በሦስት ሐሳቦች ከፍለን (አንዳንዶች በ5 ይከፍሉታል) እንመለከታለን:: የሚከለክለውና ከመንገድ የሚወገደው ማንነት: 1. የዓለም መንግሥታትን 2. ቤተ ክርስቲያንን 3. መንፈስ-ቅዱስን የሚጠቁሙ ናቸው የሚል ሀሳብ ይስነዘራል:: ይህም ብቻ አይደለም፤ አንዳንዶቹ የአውሬው ከልካይ 4. ሰይጣን 5. ሁኔታዎች ናቸው የሚሉም አሉ:: ወደ ትክክለኛው ወይም ቀራቢ. ትርጉም ለመድረስ በቅድሚያ የቃላቱን ፍቺ በደንብ መረዳቱ ጠቃሚ ነው::

..መወገድ.. የሚለው ቃል ወደ ሌላ ቦታ መወሰድን ወደ ላይ መሔድን፣ ከቀድሞ የእንቅስቃሴ ሁኔታና ቦታ ዞር ማለትን ሲያመለክት፤ሲሆን ..መከልከል.. ደግሞ አንድ ማንነት ወይም የሥራ እንቅስቃሴ ወደፊት እንዳይራመድ መቋቋምን ያሳያል:: ሐሰተኛው ክርስቶስ በግልጽ እንዳይሰራ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ቅዱሳን ከጻፈበት ጊዜ አንስቶ እስከዛሬና ወደፊትም የከለከለው (የሚከለክለው) ማነው? መንግሥታትና መንፈስ ቅዱስ ሊቋቋሙት ይችላሉ:: ሆኖም ..መወገድ.. ወደሚለው ቃል



ስንመጣ አይሰራም:: ምክንያቱም አውሬው በግልጽ መሥራት ሳይጀምርም ሆነ ሲጀምር ጀምሮም ሁለቱም ክፍሎች በምድር ይኖራሉ:: ቤተ ክርስቲያን ግን አይኖርም:: ምክንያቱም የመነጠቅ ስርዓት ስለሚሆን ነው::

አንዳንድ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስን በቤተ ክርስቲያን መኖር የሚረዱበት መንገድ ፈጽሞ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚስማማ አይደለም:: ለምሳሌ፣..መንፈስ ቅዱስ የሚኖረው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሆነ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በሚሆንበት ጊዜ የት ይኖራል? ስፍራ ስለማይኖረው እርሱም አብሮ ይነጠቃል፤የሚል ነው:: ይህ ሃሣብ መንፈስ ቅዱስ የሚኖረው በቤተ ክርስቲያን ማንነት ውስጥ ብቻ እንደሆነና፣ በዚያም እንደተወሰነ የሚያመለክት አዝማሚያ አለው:: በቅድመ ቤተ ክርስቲያን ምስረታ የነበረበትንና መለኮታዊነቱን መንፈሳዊ አካል እንዳለውና የማይወሰን መሆኑንም የመዘንጋት መልክ አለበት:: መንፈስ ቅዱስ ለዘላለም በቤተ ክርስቲያን (በቅዱሳን አካል) እንዲኖር ተሰጠ ማለት ከዚህ ስፍራ ሌላ መኖሪያ የለውም በሚል ሃሣብ ብቻ ከተተረጐመ ትልቅ ስህተት ነው:: ይህ የመንፈስ ቅዱስን ማንነት እንደ ሰው መንፈስ መወሰን ስለሚሆን ከእውነት ይርቃል::

የተለያዩ መረጃዎችንና ሌሎችንም የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ስናነጻጽር መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠና የቅዱሳንም ተግባርና ሕይወት መሪ ነው:: ከመከራው በፊት እንደሰ ሁሉ በመከራውም ዘመን ይኖራል፤አይነጠቅም:: እስከዛሬ አውሬውን የከለከለውና የተቋቋመው የቤተ ክርስቲያን ህልውና ነው እንጂ መንፈስ ቅዱስ አይደለም:: ቤተ ክርስቲያን ይህንን ሥልጣን የተቀበለችው ከመንፈስ ቅዱስ ነው:: ከላይ የተጠቀሰው ክልካይ ከመወገድ አንጻር በቀጥታ የሚያመለክተው ቤተ ክርስቲያንን ነው:: ምክንያቱም ክርስቶስ ሲመጣ ሲል በዚህ ምድር ላይ መንግስታት:ሰይጣን:መንፈስ ቅዱስ: ሁኔታዎችም ስለሚኖሩ ነው:: እነዚህ ፈጽሞ ከምድር አይወገዱም:: የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ሲሆን ሐሰተኛው

ክርስቶስ አሁንም የእግዚአብሔር መንፈስ በፈቀደለት መጠን ብቻ ይሰራል:: የቤተ ክርስቲያን አለመኖር ሥራውን በከፍተኛ ደረጃ አፋጥኖ እንዲያካሂድ ይረዳዋል:: ስለሆነም አውሬው በ70ኛው ሱባኤ መጀመሪያ ላይ ለ7 ዓመታት ቃል ኪዳን አድርጐ የሚነሳ ከሆነ (ዳን. 9:27) ይህም ጊዜ የመከራው ዘመን (ታላቁ የያዕቆብ የመከራ ጊዜ) ከሆነ በዚህ ጊዜ ደግሞ ከልካዩ ከተወገደ ይህም ከልካይ ቤተ ክርስቲያን ከሆነ የቅዱሳን መነጠቅ ከመከራው በፊት ይሆናል ማለት ነው:

### 6.2.5.3.1. መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን ይኖራል ወይስ ይነጠቃል?

ቀደም ባለው ክፍል ከልካዩ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነና በመከራውም ዘመን እንደማይኖር/ እንደማትኖር ተገልጦአል:: ከዚህ ሐሳብ ጋር በማዘያያዝ ዘርዘር ባለ መልኩ ስለ መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን መኖርና አለመኖር፣ ስለ አጠቃላይ ሁኔታዎችም እንመለከታለን::

ከላይ በተጠቀሰው ርዕስ-ጥያቄ ላይ ሁለት ዓይነት ሃሣቦች /አመለካከቶች/ አሉ:: እነርሱም፤

6.2.5.3.1.1. መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን ይሄዳል / ይነጠቃል/ የሚሉና

6.2.5.3.1.2. መንፈስ ቅዱስ አይሄድም: ይኖራል የሚሉት ናቸው::

6.2.5.3.1.1. መንፈስ ቅዱስ ይሄዳል/ይነጠቃል/ የሚሉት የሚያቀርቡአቸው ማስረጃዎች

(1). በ2ኛ ተሰ. 2:6-7 ያለውን (የሚከለክለው) እና (ከመንገድ እስኪወገድ) የሚለው ሃሣብ በዚህ ክፍል የሚከለክለው እና ከመንገድ እስኪወገድ የሚሉት የስም ምትኮች የሚያመለክቱት መንፈስ ቅዱስን ነው:: መጠሪያ ስሙ በወንድ ጾታ ስለሆነ በድንግልና ንጽህት ሴት የተመሰለችውን ቤተ ክርስቲያንን አያመለክትም:: ስለሆነም የሚወገደው መንፈስ ቅዱስ ነው::



(2). በብሉይ ኪዳን ዘመን መንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ እንዳልኖረ ሁሉ በመከራውም ዘመን መንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ የማይኖርበት ዘመን ይሆናል:: የመከራውና የብሉይ ኪዳን ዘመናት አንድ ዓይነት ይሆናሉ::

(3). መንፈስ ቅዱስ በሁሉ ቦታ በመገኘት ኃይሉ ይሰራል፤ ሆኖም ግን የማጥመቁ፣ በውስጥ የመኖሩ፣ የማተሙና የመሙላቱ ሥራ ይቋረጣል ወይም ያቆማል:: 1ኛ ቆሮ. 12:12-13፤ ኤፌ.1:13፤ 4:30 እና 5:18:: ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ይህንን የሚሰራው በአማኙ ውስጥ እየኖረ ከሆነ ከወጣና ከሄደ ሊሰራው አይችልም::

(4). መንፈስ ቅዱስ ከተወሰደ በመከራው ዘመን የመዳኑ ሁኔታና አሰራር እንዴት ይሆናል? ለሚለው ጥያቄ የሚሰጡት ማስረጃ፤

<u>በመጀመሪያ</u> መዳን በእምነት መርህ ይሆናል የሚል ሲሆን የሚጠቀሰው ክፍል /ዕብ.11:1-40፤ ሮሜ 4:2/ ነው:: በሁለተኛ ደረጃ መዳን በክርስቶስ ኢየሱስ ደም /በበጉ/ ነው:: ማስረጃ /ራዕ. 7:14፤ 12:7/ ይጠቅሳሉ:: በመጨረሻም መዳን በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ይሆናል ሲሉ ማስረጃቸው መንፈስ ቅዱስ በዮሐ. 3:5-6 እንደተጠቀሰው ሆኖ ባይሰራም በብሉይ ኪዳን ጊዜ ሰዎችን የማዳኑን ሥራ ስለሰራ ዛሬም በቅዱሳን ውስጥ ሳይኖር እንደቀድሞው የማዳን ሥራውን ይፈጽማል:: የዳግም ልደቱንም ሥራ ሊሰራ ይችላል ይላሉ::

6.2.5.3.1.2. <u>መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን አይሄድም (አይነጠቅም)</u>

ማስረጃዎቹም የሚከተሉት ናቸው::

<u>*(1). የ2ኛ ተሰ. 2:6-7 ከልካይ መንፈስ ቅዱስ ስለመሆኑ*</u>

ብዙዎቹ የመንፈስ ቅዱስን ከመከራው በፊት ከዚህ ዓለም መሄድ የሚደግፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች የሚጠቅሱት 2ኛ ተሰ. 2:6-7 ን ነው:: ለዚህም ***የሚከለክለው*** የተባለው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነና ለመሆኑም ማረጋገጫው በወንድ ጾታ መጠቀሱ ነው የሚል ነው:: ከዚህም ጋር

በማያያዝ *የሚከለክለው* የሚለውና *ከመንገድ የሚወገደው* ቤተ ክርስቲያን ብትሆን ኖሮ በንጽህት ድንግል /በሴት/ ትጠራ ነበር ይላሉ:: ሆኖም ግን የአተረጓጐም ልዩነት ካልሆነ በቀር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን "እርሱ" በሚል የወንድ ጾታና ያለ ጾታም መጠራቷን መረዳት ይቻላል:: አንዳንዶች ግን ቤተ ክርስቲያንን እንደ ንጽህት ሴት ድንግል ብቻ የሚመለከቱም አሉ:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን /በኤፌ. 2:15፤ 4:13/ እንደ ወንድ ጾታ *አዲስን ሰው፤ ሙሉ ሰው* /በ1ኛ ቆሮ. 12:12-13፤ ኤፌ. 1:22-23፤ ቆላ.1:18/ ደግሞ *የክርስቶስ አካል* በመባል ተጠርቷል:: እነዚህ ጥቅሶች የሚያመለክቱት ቤተ ክርስቲያንን ነው:: ሆኖም ግን ቤተ ክርስቲያንን በንጽህት ድንግል መመሰል ስህተት አይደለም:: ስለዚህ በ2ኛ ተሰ. 2:6-7 የተጠቀሰው አውሬውን የሚከለክለው የክርስቶስ አካል ተብሎ የተጠራው ቤተ ክርስቲያን እንጂ መንፈስ ቅዱስ አይደለም:: ይህም ከመንገድ እስኪወገድ በሚለው መንፈስ አኳያ ብቻ ማለት ነው::

### <u>(2). የሰማይ ርስት መያዣ መንፈስ ቅዱስ መሆኑ</u>

በኤፌ. 1:13-14 ...*እርሱም የርስታችን መያዣ ነው* ሲል አንድ ሰው ወደ ጽዮን ተራራ፣ አዲሲቱና ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም፣ ወደ ጻድቃን መንፈሶች ጉባኤ መግባት የሚችለው በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ሲታተም ነው:: በአዲስ ኪዳን ስሚገኝ ለማንኛውም እውነተኛ ንስሃ ለገባና ጌታን ለተቀበለ ይህ የልጅነት መንፈስ ተሰጥቶታል:: በዚህም ዮሐ. 1:12-13 የልጅነት ስልጣን መሠረት በሮሜ 8:17 እንደተጠቀሰው በዮሐ. 14:1-3 በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የተዘጋጀውን ሰማያዊ ርስት ይወርሳል:: ይህ የተስፋ መንፈስ ቅዱስ ቀድሞውኑ ከተሰጠና ይህም ደግሞ የፈሰሰው በአዲስ ኪዳን ከሆነ በመከራውም ዘመን ለሚገኙ ሁሉ ስጦታው መስጠት እስከሚያቆምበት ጊዜ መስጠቱ ይቀጥላል::



### <u>(3). የመንፈስ ቅዱስ በሰው ለዘላለም መኖርና ቅዱሳንን በማጽናናት የሚሰራቸው ነገሮች፤</u>

ጌታ ኢየሱስ ይህንን ዓለም ለቅቆ ከመሄዱ በፊት ስለ መንፈስ ቅዱስ የተናገራቸውን የተስፋ ቃሎች እስቲ እንመርምር:: በዮሐ. 14:17፤ 26 ምዕ. 16:7 ላይ መንፈስ ቅዱስ "አጽናኝ" ተብሏል "አጽናኝ" ማለት ደካማውን / በቂ ኃይል የሌለውን ሐይል በመስጠት/አይዞህ ወይም በርታ በማለት ለመርዳትና ለማማከር ከጐን የማይጠፋ መካሪና አበረታች ማለት ነው:: የመከራው ዘመን በጣም አስፈሪ ነው:: እንኳን በሰባቱ ዓመታት የመከራ ዘመን ይቅርና ጌታም እንኳን ምድርን በለቀቀበት ጊዜ ለደቀመዛሙርቱ የነበረው የጊዜው አስፈሪነት ቀላል አልነበረም::

የሰባቱ ዓመታት ባለስልጣኖች አውሬውና አበሮቹ በምድር በሚገለጡበት ጊዜ በርኩሳን መናፍስት ኃይል ተሞልተው ስለሚሰሩና ኃይላቸውን በከፍተኛ ደረጃ ስለሚለቁ በዚያን ዘመን፤ ያለ መንፈስ ቅዱስ አጽናኝነትና ረዳትነት የመከራውን ሁኔታ መቋቋም /መታገስ/ እጅግ ከባድ ነው:: ስለሆነም የመንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን መኖር ምንም አሌ የማይባል እውነት ነው::

### <u>(4). የመንፈስ ቅዱስ ወቃሽነት</u>

ጌታ ኢየሱስ በዮሐ. 16:8 ላይ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ <u>ዓለምን</u> ስለ ኃጢአት፣ ፍርድና ስለጽድቅ <u>እንደሚወቅስ</u> አስተምሯል:: በዚህ ክፍል የተጠቀሰው <u>"ወቀሳ"</u> የሚለው ቃል አንድ ሰው እየተጓዘበት ያለው መንገድ ልክ አለመሆኑን በማሳየት ገስጾ፣ መክሮ ትክክለኛውንም ጐዳና አሳየ ማለት ነው:: ዓለም ማለት ማንኛውም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ሃሣብ ያልሆነ በስውርም ሆነ በግልጽ የጽድቅ ጠላት የሆነ ስርዓት የሚካ<u>ሄድበት ማንነት</u>ና ስርዓቱ ሁሉ ነው:: በ70ኛው ሱባኤ የዓለም ስርዓት እጅግ በተጠናከረና በከፋ ሁኔታ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ በከፍተኛ ፍጥነት የሚራቅበትና የሚረከስበት ጊዜ ነው:: *ታዲያ* መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን የሚሄደው

የወቀሳ ሥራውን ጨርሶ ነው? አይደለም:: እንዲያውም የመንፈስ ቅዱስ ወቃሽነት የሚያይለው ሰዎችንም ወደ ንስሃ የሚመራው በዚህ ወቅት ነው:: ስለዚህ የዓለም ስርዓት በመከራው ዘመን ካለ የመንፈስ ቅዱስም ወቀሳ እጅግ በጠነከረ ሁኔታ ይኖራል ማለት ነው:: ለዚህም ነው ቁጥሩ የበዛ ሰው በመከራው ዘመን የሚድነው ::ራዕ. 7:8-13::

## (5). የጌታ ኢየሱስ አለመመለስ

ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ወደ አባቱ እንደሚሄድ በነገራቸው ጊዜ ልባቸው ታውኮና አዝኖ ነበር ዮሐ. 14:1-3:: ከዚህም ሁኔታቸው በመነሳት ሦስት ታላላቅ አበረታችና አጽናኝ የሆኑ ተስፋዎችን ሰጥቶአቸዋል:: እነዚህም ተስፋዎች፤ስፍራ ላዘጋጅላችሁ እሄዳለሁ፤ተመልሼ እመጣና እወስዳችኋለሁ፤አጽናኙን መንፈስ ቅዱስ እልክላችኋለሁ የተሰኙት ነበሩ::

የዮሐንስን ወንጌል በተለይ ከምዕ. 14-16 ብንመለከት፤ ጌታ የደቀ መዛሙርቱን ልብ ለማጽናትና ለማበረታታት የማጽናኛና የተስፋ ቃሎችን የተናገረበት ምዕራፎች ናቸው:: ጌታ በማስተማር ብቻ ሳይሆን በ17ኛው ምዕራፍ ላይ የደቀመዛሙርቱን አጠቃላይ ሁኔታ በጸሎት ለአባቱ አቅርቧል:: እነዚህን ነገሮች ከፈጸመ በኋላ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት በዮሐ. 16:7 ላይ አንድ ልዩ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባን እውነት ተናግሯል:: ይኸውም፤ "እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፣ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል:: እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፣ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ::" የሚል ነበር:: በዚህ ጥቅስ መሠረት ጌታ ኢየሱስን በመተካት ለደቀ መዛሙርቱ በጌታ እንደሚደገፉና እንደሚጽናኑ ሊሆንላቸው የሚችለው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን እንረዳለን:: የተጻፈ ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፏል እንደተባለ ያ ለደቀ መዛሙርቱ እጅግ አስፈልጓቸው የነበረ የተስፋ መንፈስ 1/ ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ እስከዛሬ ላሉ ቅዱሳን 2/ ወደፊትም በመከራው ዘመን ለሚድኑ ቅዱሳን ያለ ጥያቄ አስፈላጊ ነው::



ጌታ ኢየሱስን የተካ መንፈስ ቅዱስ ነው:: ጌታ ካረገበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ምድር ለመኖር በሚታይ ክብሩ አልተመለሰም:: ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ የመጣበትን ዓላማ ከፍጻሜ ሳያደርስ አይተውም:: በመከራውም ዘመን በጌታ ቦታ ሆኖ ይሰራል፤እውነትነም በመግለጽ ሰዎችን እየወቀሰ ወደ ጌታ መንግሥትም ያፈልሳል::

## (6). የምህረት በር አለመዘጋት

ምንም እንኳ የመከራው ዘመን የእግዚአብሔር ቁጣ በአስቃቂ ሁኔታ በምድር ላይ የሚፈስበት ጊዜ ቢሆንም፣ በእግዚአብሔር መልክና አምሳል የተፈጠሩ ሁሉ አመድ ይሆናሉ፣ ሰው ከምድር ገጽ ይጠፋል ማለት አይደለም:: የመንፈስ ቅዱስን ከምድር መሄድ ሃሣብ ከሚያጠብቁ የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚዎች ውስጥ ጥቂቶቹ የምህረቱ በር ይዘጋል የሚል ሃሣብ ያላቸው ናቸው:: ለዚህም ደግሞ መነሻው የመንፈስ ቅዱስ መሄድ ነው የሚሉ ናቸው:: ሆኖም ግን ራዕ. 7:9ኙን ስንመለከት ማንም ሊቆጥራቸው ያልቻለ ታላቅ ህዝብ ከታላቁ መከራ እንደወጡና ልብሳቸውን በበጉ ደም በማጠብ እንደዳኑም ያሳያል:: በመከራውም ውስጥ አልፈው ለሺሁ ዓመታት ስርዓትም ለመብቃት የደህንነት ወንጌል የሚሰበክላቸው አሉ:: የሰዎች መዳን የእግዚአብሔርን ምህረት ማለትም የመንፈስ ቅዱስን አለመወሰድ ያሳያል::

(7). የቤተ ክርስቲያን መነጠቅና የመንፈስ ቅዱስ አለመነጠቅ ከዓላማ አንጻር.

በክፍል 8 ውስጥ "የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ዓላማዎች /ምክንያቶች/" በሚለው ዐቢይ ርዕስ ሥር ቤተ ክርስቲያን የምትነጠቅባቸውን ዋና ዋና ምክንያቶች ተገልጠዋል:: መንፈስ ቅዱስ በቅድመ መነጠቅ የሠራቸውን ሥራዎች ሁሉ በድህረ መነጠቅና በሺህ ዓመት መንግሥትም ይሰራል::

(8). <u>የመንፈስ ቅዱስ በወንዶችና በሴቶች የእግዚአብሔር ባሪያዎች ላይ መፍሰስ</u>

ኢዩ. 2:18-29 ስንመለከት እግዚአብሔር *በመጨረሻው ዘመን በስጋ ለባሽ* ሁሉ ላይ በተለይም *በወንዶችና ሴቶች ባሪያዎቹ* ላይ ከመንፈሱ እንደሚያፈስ በነቢያቱ ተናግሯል:: በዚህ ምዕራፍ የመጨረሻ ዘመን የተባለው፤

- ጌታ ኢየሱስ ከተወለደበት ዘመን አንስቶ ሐዋርያት እያገለገሉ ቤተ ክርስቲያን ተመስርታ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ እየሰራ ያለበት ዘመን /1ኛ ዮሐ. 2:18/
- የ70ኛው ሱባኤ: የሰባቱን ዓመት መከራ ወይም የያዕቆብ የመከራ ዘመን /ዘዳ. 4:30፤ ኤር. 23:20፤ 30:24፤ ዳን. 9:24-27::
- ጌታ ኢየሱስ ለመንገሥ ወደዚህ ዓለም በመምጣት የአርማጌዶንን ጦርነት የሚዋጋበት ጊዜ /ህዝ. 38:8፤ 16፤ 1ኛ ጴጥ. 1:5/
- የሺሁን ዓመት ስርዓትና ጊዜ /ኢዮ. 19:25/
- የመነጠቅ ጊዜ /ዮሐ. 6:39፣ 40፣ 44፤ 11:24/ ናቸው::

የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ባሪያዎች ደግሞ እግዚአብሔር በአይሁዶችና በአህዛብ መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳ አፍርሶ ከሁለቱ ያወጣው "አንድ ሰው" "የክርስቶስ አካል" ቤተ ክርስቲያን ነው:: ወንጌልን ለማስራጨት የእግዚአብሔርን ልጅነት ስልጣን የተቀበሉት አይሁዶችና /ከጌታ መወለድ ጌዜ እስከ አሁን የዳኑ አይሁዶችና ወደፊትም የሚታተሙት 144000 እና ሌሎችም አይሁዶች/ በተጨማሪም አህዛብ የጌታ ባሪያዎች ናቸው:: ስለሆነም በዚህ ዘመን መጨረሻ በመከራው ዘመን ጌታ መንፈሱን በነዚህ ባሪያዎቹ ላይ ያፈስሳል ማለት ነው:: ሥጋ ለባሽ የተባሉት የምድር ነዋሪዎች ናቸው::



(9). <u>የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ዓላማ.</u>

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ96 ጊዜ ያላነሰ መንፈስ ቅዱስ የሚያከናውናቸው ሥራዎች ተገልጸዋል:: ከነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹን ከዚህ እንደሚከተለው አቀርባለሁ:: መንፈስ ቅዱስ ወደዚህ ምድር ከመጣባቸው ዋና ዋና ዓላማዎቹ ውስጥ፤

- ያመኑ ሰዎችን ከዓለማዊነት /ከሰይጣን ልጅነት/ ወደ እግዚአብሔር ልጅነት ሊሰውጥ ሮሜ 8:15፤ 9:4፤ ገላ. 4:5 እና ኤፌ. 1:5::
- በሰዎች አድሮ ለሌሎች ሊናገር፤ 2ኛ ሳሙ. 23:2፤1ኛ ጢሞ. 4:1::
- በስውር ጠላት የሚሰራውን ነገር /የተደበቀውን/ ሊገልጽ 1ኛ ዜና 28:12፤ ሐሥ. 11:28፤ 21:4::
- ስለ እውነት ወይም ስለ ክርስቶስ ሊመሰክር ነህ. 9:20፣ 30፤ ዮሐ. 15:26፤ 1ኛ ዮሐ. 5:7::
- ውበትን ሊሰጥ /ኢዮ. 26:13/ በመከራው ዘመን ሰዎች በውስጣዊም ሆነ በውጪአዊው ማንነታቸው በከፍተኛ ደረጃ የሚወላልቁበትና የሚበላሽበት ጊዜ ስለሆነ የመንፈስ ቅዱስ መኖር በመከራው ዘመን እጅግ አስፈላጊ ነው:: ኦጺ_ን_ በመከራው ዘመን ይቅርና በቅድመ-መከራ ያለችውም ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ችግር ውስጥ ገብታለች::
- በሰዎች ላይ በማረፉ ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ሊያድል ኢሳ. 11:2 ማቴ. 3:16፤ ዮሐ. 1:3::
- በልዩ ኃይልና ስልጣን ሰዎችን ለአገልግሎት ሊለይ ኢሳ. 61:1፤ ሉቃ. 4:18::
- ለሰዎች/አማኞች/ ፀጋንና የምልጃን ህይወት መስጠት፤ዘካ. 12:10-13፤ ኤፌ. 6:18፤ ዕብ. 10:29::
- ቀድሞ በጌታ የተነገረውን ማስታወስ /ዮሐ. 14:26/ ነገሮች በተምታቱበትና ግራ በሚያጋባ የጨለማ ዘመን የሰው የማስተዋሉ ደረጃ በሚጠፋበት በመከራው ዘመን በተሰጠው የተስፋ ቃል፤ኢዩ. 2:28-29 መሠረት በሙላት ይሰራል::

- ሰዎች ካመኑ በኋላ በቀጥታ መዳናቸውንና በሰማያዊ ስፍራ በሕይወት መጽሐፍ መመዝገባቸውን ያረጋግጣል፣ ያጸናል:: ሮሜ 8:16::
- በእውነተኛ አማኞች ተአምራትንና ድንቅን መሥራት ሮሜ 15:19፤ 1ኛ ቆሮ. 12:7-11፤በራዕ. 13 ውስጥ ሐሰተኛው ነቢይ እንኳን እሳት በሰዎች ፊት እያወረደ ህዝቡን ሲያስደንቅ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በተከታዮቹ የማይሰራበትና በሙሴ በኩል የፈርኦንን ቃላተኞችና አስማት አዋቂዎች እንዳሳፈረ በመከራውም ዘመን የማይሰራበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለም::
- ሰዎችን በክርስቶስ አካል ማጥመቅ /1ኛ ቆሮ. 12:13/ ለሰዎች ማለትም ጌታን አምነው ለሚከተሉ የዳግመኛ መወለድን ስልጣን ሰጥቶ ወደ ክርስቶስ አካል ቤተ ክርስቲያን የማስገባት ሥራ የመንፈስ ቅዱስ ነው::
- የእግዚአብሔር ባህሪይ በአማኝ ውስጥ ለማስቀመጥ፤ ገላ. 5:22::
- ከሞትና ከሐጢአት ህግ ነጻ ለማውጣት፤ ሮሜ 8:1-2::
- በሰዎች ሕይወት ውስጥ ፍቅርን ለማፍሰስ፤ ሮሜ 5:5፤ 15:30::
- የውስጥ ሰውነትን ለማጠንከር ኤፌ. 3:16::
- ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለዘላለም ሕይወት ሊጋብዝ ራዕ. 22:17
- ባጠቃላይ ትክክለኛ መስዋዕትን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ የሚረዳ፣ የአማኞች የጽድቅ ምንጭ፣ በሥጋ ኃይል ላይ ድልን የሚሰጥ፣ መንፈሳዊ መልካችንን ወደ ክርስቶስ መልክ የሚለውጥ፣ 2ኛ ቆሮ. 3:18፣ የትንሳኤን ሕይወት ሰጪ፣ ወደ ፍጹምነት ለመድረስ ረዳትና ከመርገምም ሁሉ የሚያነጻው መንፈስ ቅዱስ ነው::

ከላይ የተዘረዘሩት የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች በጣም ጥቂቶቹ በብሉይ ኪዳን የታዩ ሲሆኑ የተወለኑት ግን በአዲስ ኪዳን በብዛት ታይተዋል:: መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ሥራዎች ያከናወነው በመጨረሻው ዘመን ከሰዎች



ጋር በተያያዘ እንጂ ከመላዕክት ጋር አይደለም:: የአሁኑና የወደፊቱ የመከራ ዘመን በሰው ሕይወት ከማናቸውም ጊዜ ይልቅ ክፋት የሚበዛበት፣ ልዩ ልዩ ወደ ሐጢአት መንገዣ መስመሮች የሚበዙበት ጊዜ ስለሆነ ከላይ በተዘረዘሩት ተግባሮች አንጻር ከመቼውም ጊዜ በበለጠ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሰርቶ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ አካል /ቤተ ክርስቲያን/ የሚያመጣበትም ጊዜ ነው:: የመንፈስ ቅዱስ ዓላማ በክርስቶስ ቦታ ሆኖ በመሥራት ሰዎችን ወደ ደህንነት /ወደ ክርስቶስ/ ማምጣት እስከሆነ ድረስ መዳን በሚያስፈልግበት የመከራው ዘመን መንፈስ ቅዱስ ምድርን ለቅቆ ይሄዳል የምህረቱም በር ይዘጋል ማለት ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ውጪ ነው::

### (10). መንፈስ ቅዱስ የሚወርድባቸው ሦስት ዘመናት

ወደዚህ ርዕስ ዝርዝር ሃሳብ ከመግባቴ በፊት አንባቢን የምጠይቀው ጥያቄ አለ:: ይኸውም በሺሁ ዓመት ስርዓት መንፈስ ቅዱስ በአዲስ ኪዳኑ ሁኔታና ይዘት በምድር ይኖራል ወይስ አይኖርም? የሚል ነው::

መንፈስ ቅዱስ በሺሁ ዓመት እንደሚኖር የሚነግሩን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ኢዩ. 2:28-32፤ ኢሣ. 32:15፣ 44:3፤ ሕዝ. 36:26-27፣ 39:29 እና ዘካ. 12:10 እና ሌሎችም ናቸው:: አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚዎች በኢዩ. 2:28-32 በመጨረሻው ዘመን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ እግዚአብሔር ከመንፈሱ ሲያፈስ የሰጠው ተስፋ ሦስት የተለያዩ ቅደም ተከተላዊ ጊዜአት አሉት ይላሉ:: ይኸውም

- የበዐለ ሃምሣውና ከዚያም በኋላ ያሉት ጊዜአት ሐሥ. 2:28::
- የመከራው ዘመን /ሰባቱ ዓመታት/ እና ኢዩ. 2:28-32ይህ
- የሺሁ ዓመት ስርዓት /ኢዩ.2:28-32፤ ሐሥ. 2:16-17፤ ኢሣ. 32:15፣ 44:3፤ ሕዝ. 36:26-27፣ 39:26 እና ዘካ. 12:10 ናቸው:: ይህ ሃሳብ ከዚህ ጽሑፍ የመጨረሻ ዘመን ትርጉም ሰጪ ሃሳቦች ጋር አይቃረንም::

ከላይ የተጠቀሱት ሦስት ጊዜያት የተከሰቱትና ሊከሰቱ ያሉት በዚህ ዘመን መጨረሻ ላይ ለመሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ብቻ ሳይሆኑ ታሪክም ይመሰክራል:: ከላይ በተራ ቁጥር 3 የተጠቀሰው ሃሣብ ለአይሁዶች ብቻ የተጠቀሰ ቢመስልም በሺሁ ዓመታት ውስጥ ግን መንፈስ ቅዱስ የማዳኑን ሥራ በአይሁዶችና በቅዱሳን አማኞችም ሕይወት ይሰራል::

እዚህ ቦታ ልብ ልንለው የሚገባ እውነት አለ:: ከላይ በተዘረዘሩት ሦስት ሃሣቦች ላይ በመቆም የመንፈስ ቅዱስን ሁኔታ ከመከራው ዘመን ጋር በተያያዘ እንድንመረምር ነው:: ቀደም ካሉት የእግዚአብሔር ነቢያት አንዱ ኢዩኤል በመጨረሻ ዘመናት መንፈስ ቅዱስ በምድር እንደሚወርድ ተናግሯል:: ይህ በእግዚአብሔር ቅዱሳን የተነገረው ትንቢት ፍጻሜው ሲቀርብ ጴጥሮስ በሐሥ. 2:38-39 እንደተነገረው የተስፋው መንፈስ በሐሥ. 2:1-4 ፈስሶ ሰዎችም ተቀብለውታል:: እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ ከበዐለ ሐምሳ ጀምሮ እስካሁን ካለና ከሰራ፡ እንዲሁም በሺሁም ዓመት የሚሰራ ከሆነ በመሐል በመከራው ዘመን የሚያቆምበት ምንም ምክንያት አይኖርም:: የመንፈስ ቅዱስ ከበዐለ ሃምሳ ጀምሮ እስካሁን ካለ በሰባቱ ዓመታት መከራ መጨረሻም /ዘካ. 12/ በሺሁ ዓመታት ከእስራኤልና አህዛብ ጋር በተያያዘ ካለ በሰባቱ ዓመታት ውስጥ ወደ ላይ የሚሄድበት ምክንያት ስለማይኖር መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን ይኖራል::

## <u>(11). የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አስፈላጊነት</u>

ቀደም ተብሎ እንደተጠቀሰው በመከራው ዘመን በአለማችን የሚከሰተው የአመጽ ሁኔታ ዲያብሎስና አጋንንቱ ለሺህ ዓመትና ለዘላለም ሊፈረድባቸው ጥቂት ዘመን እንደቀራቸው አውቀው /ራዕ. 12:11-12/ በታላቅ ቁጣ የሚወርዱበት ጊዜ ስለሆነ አስጨናቂነቱ እጅግ በጣም ከፍተኛና ከባድ ነው:: 2ኛ ጢሞ. 3:1-9፤ ሮሜ 1:18-32፤ ማቴ. 8:28-29:: በማቴዎስ ውስጥ "ጊዜው ሳይደርስ ልታሰቃየን ወደዚህ መጣህን" የሚለው የአጋንንቱ ጥያቄ የሚሰቃዩበት ቀን እንዳለና ያም ቀን ወደ እነርሱ እየገሰገሰ እንደሆነ መረዳታቸውን ያሳያል:: ያ ቀን ግን ከመድረሱ በፊት ለመሥራት አጋንንቱ



በአሰቃቸው በዲያብሎስ አማካይነት ቁጣ ውስጥ መግባታቸውንም ከራዕይ 12:11-12 እንረዳለን:: በመከራው ዘመን ለሚኖሩ ቅዱሳን ከማናቸውም ጊዜ ይልቅ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚያስፈልጋቸው በዚህ ዘመን ነው:: ራዕይ 13:10::

የኤልያስ ተከታይ የነበረው ኤልሳዕ ኤልያስን ከአንተ ሳልወሰድ /ሳልለይ/ የምትፈልገውን ለምን ባለው ጊዜ፣ መንፈስ በእርሱ ላይ እጥፍ ሆኖ እንዲወርድ የጠየቀው የመብለጥ መንፈስ ናፍቆት ይዞት ወይም ከኤልያስ የበለጠ ዝነኛና ክቡር ሆኖ ለመታየት ስለፈለገ አልነበረም:: ይህ ቢሆን እግዚአብሔር ባልመለሰለትም ነበር:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ትዕቢትን ስለሚቃወም ነው:: ነገር ግን ከኤልያስ ጊዜ ይልቅ በኋላ ያለው የከፋና የማይመች ስለሚሆን ያንንም ሁኔታ በህይወቱ በሚሰራው የመንፈስ ኃይል ለመግጠም ስለፈለገ ነው::

ጌታ ኢየሱስም በሉቃ. 24:49 እና በሐሥ. 1:8 ኃይልን እስክትለብሱ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ ያለው፤ በዚያን ወቅት የእግዚአብሔር ኃይል ለሥራው እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ስላወቀና አስቀድሞም ስለተመለከተ ነው:: ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል አስፈጊነት አንጻር ጌታ ኢየሱስ በዚያን ጊዜ የነበረው አቋም ዛሬም አልተለወጠም:: በኤልሳዕ ጊዜ ያስፈለገው የኃይል መጠን ሁለት እጥፍ ነበር በሐዋሪያት ዘመን ያስፈለገው የኃይል መጠን በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ ሆኖ በመከራው ዘመንስ የሚያስፈልገው የኃይል መጠን ከጊዜው አስፈሪነትና አስከፊነት አንጻር ምን ያህል እጥፍ እንደሚሆን በመንፈስ ቅዱስ የሚመሩና የሚያስተውሉ ይመልከቱት /ይገምቱትም/::

<u>በመከራው ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለሚከተሉት ዋና ዋና ነገሮች ያስፈልጋል</u>::

- ***የእግዚአብሔርን ቃል ሀያውነት ለመግለጽ፣***

ሳዘኑ መጽናኛ፣ ለተሰበሩ መጠገኛና መፈወሻ መድኃኒት፣ ግራ ለተጋቡ መንገድ አመልካች ለመሆን፤ ለሰዎችም በትክክል ገልጦ

ለማስረዳትና ወደ እውነትም ሁሉ ለመምራት፤ የጌታ ኢየሱስን ለሰ ኃጢአት መሞትና መነሳት፣ ማረግና ተመልሶ መምጣት ለመመስከር::

- ***ለጸሎት፤***

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሐዋርያትና ነቢያት ጉልበታቸው መ እስኪያወጣ በመጸለይና በእምባ የጌታን ፍለጋ የተከተሉት (ዕብ. 5:7) ጌ ኢየሱስም ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን ያቀረበ ካረፈበት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተነሳ ነው:: በሮሜ 8:28 መንፈስ ቅዱ የቅዱሳንን ድካም የሚያግዝ፣ የአጸላለይን ዘዴ የሚያስተምርና በማይነገ መቃተት የሚማልድ ሆኖ ተገልጧል:: ከመከራው በፊትም ሆነ በመከራው ጊዜ ለሚገኙ የወንጌል ምርኮኞች ማጥቂያና ድል ማድረጊያ መሣሪያ ጸሎ ነው:: ለዚህም መንፈስ ቅዱስ እጅግ ያስፈልጋል::

- ***ከገሃነም ደጆች ጋር ለመጋደል***

ጌታችን ኢየሱስ (ቤተ ክርስቲያኔን በዚች ዓለት ላይ እሰራለሁ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም (ማቴ. 16:18) ሲል ወደ ክብሩ ወንጌል የተጠሩ ቅዱሳን ምን ያህል ጦርነት /ተጋድሎ/ እንደሚጠብቃቸው ማመልከቱ እሙን ነው:: የገሃነም ደጆች ማለትም ሰይጣን፣ ርኩሳ መሳዕክት፣ አጋንንትና እነዚህ የሚገለገሉባቸው መሣሪያዎች /ሰው፣ እንስሳ ግዑዝ ነገር፣ .../ ቀላል ሰራዊት አይደሉም:: /ኤፌ. 6:12-18/ ስላልሆኑም ከእነዚህ ጋር ትግል ገጥሞ ለመዋጋትና የድል ባለቤት ለመሆን ኃይል ያስፈልጋል:: ሁለተኛው ሺህ አልቆ በሦስተኛው ሺህ ውስጥ የአዲሱ ዘመ እንቅስቃሴ ተከታዮች ሰው ሁሉ ወደ አምላክነት ደረጃ ይደርሳል በማለት ያስተምራሉ:: ለዚህ የሚጠቀሙበት ዘዴ ርኩሳን መናፍስትን ወ ውስጣቸው በማስገባት ነው:: በመከራው ዘመን ሰው እግዚአብሔር ነው በሚባልበትና በርኩሳን መናፍስት ሰዎች በተሞሉበት ዘመን ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይልና እርዳታ እንዴት መቋቋም ይችላሉ? ስለሆነም ለዚህ ሥራ መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን አስፈላጊ ነው ማለት ነው::

- ***የወንጌልን ሥራ ለማንቀሳቀስ /ለማስፋፋት/***



ወንጌል ከተሰበከበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬና ወደፊትም ይሰበካል፤ ይሰራጫል:: በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በሐሥ. 11:12፣ 19፤ 8:4-10፤ 29፣ 39-40፤ 16:7፤ ራዕ. 2:7፣ 11፣ 17፣ 29፤ 3:6፣ 13 እና 22 ስንመለከት መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን /አገልጋዮችን ሲመራ እናያለን:: በመከራው ዘመን ለሚኖሩ ቅዱሳን የዚህ ዓይነት ምሪት እንደሚሰጥ አያጠራጥርም:: ይህም ግን በበአለ ሃምሣ ዕለት በወረደው ዓይነትና ዛሬም በተለያዩ አገሮች በሚሰራው ዓይነት እንጂ በብሉይ ኪዳኑ ሁኔታ ብቻ አይደለም::

እንግዲህ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለማናቸውም ዓይነት የእግዚአብሔር ሥራ ያስፈልጋል:: እንዲያውም ከመነጠቅ በፊት በአሁኑ ዘመን ያለን አማኞች በልዩ ኃይል ተሞልተን በስልጣንና በእውነተኛነት ወንጌሉን ልንሰብክ የተዘጋጀን ነን:: ስለሆነም የምንጠብቀው ከዛሬ 30 ዓመት በፊት በኢንዶኔዢያ በኮሪያና በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ወይም የዛሬ 2000 ዓመታት በኢየሩሳሌም የፈሰሰው መንፈስ ቅዱስ በኢትዮጵያም እንደሚያልፍ ነው:: ይህም ሲባል መንፈስ ቅዱስ በኀይል ባይወርድም ልንሰራው ያለውን በትጋት እየሰራን መጠበቅ ይኖርብናል:: ሐይል እስኪመጣ ብለን ቁጭ እንዳንል ልንጠነቀቅ ያሻናል::

## (12). <u>የእግዚአብሔርና የሰይጣን እቅድ /ዓላማ/ አፈጻጸም</u>

መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና በዚች ዓለም ላይ ዓላማ ያለው እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ሰይጣንም እንደሆነ ነው:: ኤፌ. 1:4፤ 2ኛ ጴጥ. 3:9፤ በራዕ. 20:3፣ 12:9:: በራዕይ 12:12 ዲያብሎስ ዕቅዱን ተፈጻሚ ለማድረግ በታላቅ ቁጣ ወደዚህ ምድር ነዋሪዎች ሲመጣ የእግዚአብሔርስ ሁኔታ ምን ይሆናል ብለን እንገምታለን ወይም እናምናለን? እግዚአብሔር አስቀድሞ በልጁ በኢየሱስ የጀመረውን ሥራ ሙሉ በሙሉ አልፈጸመም:: የጌታ ኢየሱስን ጠላቶች ገና ከእግሩ ሥር ሙሉ በሙሉ አላስገዛለትም:: ገና ልዩ ልዩ ጥበቡን በስብከት ሞኝነት በሚያምኑ የክርስቶስ አካልና /ቤተ

ክርስቲያን/ በመከራው ዘመንም ቅዱሳን/ አማካኝነት ይገልጻል:: ኤፌ. 3:10፤ 1ኛ ቆሮ. 12:7-11::

እግዚአብሔር ክብሩን የገለጸውና የሚገልጸውም በህዝቡ ነው:: በ1ኛ ቆሮ. 12:8-11 የተጠቀሱት የፀጋ ስጦታዎች ሥራቸው እግዚአብሔርን መግለጽ (በግሪክ ፋኔሮሲስ) ነው:: ይህም ከመንፈስ ቅዱስ ነው:: ስለሆነም በመከራው ዘመን ሰዎች በጨለማና ግራ በመጋባት ውስጥ እያሉ የአፍቃሪውንና የቸሩን አምላክ እጅና ፊት በሚናፍቁበት ወቅት መንፈስ ቅዱስ አላማውን ሳይፈጽም ይነጠቃል ማለት አያስደፍርም::

## (13). ማንም ሊቆጥራቸው የማይችል ታላቅ ህዝብ ሁኔታ

በሐሥ. 4:12 ውስጥ መዳን በክርስቶስ ብቻ እንደሆነ ተገልጿል:: አንድ ሰው ዳነ የሚባለው መንፈሱን ገድሎት የነበረው ኃጢአት ሲነሳለት ነው:: ኃጢአት ደግሞ ከሰው ላይ የሚሠረየው ከጥቂቶች በቀር በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው:: 1ኛ ዮሐ. 1:7:: በራዕ. 7:9-17 ውስጥ የተጠቀሱት ታላቅ ህዝብ በተለይ በቁጥር 14 ላይ ያሉት በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምነው በፈሰሰው ደሙ ከሐጢአት መንጻታቸውን ያመለክታል:: እነዚህን ቅዱሳን *የመከራው ዘመን ቤተ ክርስቲያን* እንላቸዋለን:: አስቀድሞ በምድር የነበሩና በኋላ ግን በሰማይ ርስታቸውን ጨብጠው ከተገኙ ስዚህ የበቁት በመንፈስ ቅዱስ ታትመው ነው ማለት ነው:: ሮሜ 8:16::

## (14). የመጽሐፍ ቅዱስ በመከራው ዘመን መኖር

በመከራው ዘመን ለሚኖሩ ሰዎች ወንጌል ይሰበካል ወይስ አይሰበክም? ወንጌል እስከ ዓለም ፍጻሜ ለዓለም ሁሉ ይሰበካል:: የሚሰበክ ከሆነ መንፈስ ቅዱስ በመከራው አይኖርም የሚሉ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለመንፈስ ቅዱስ የተነገረውን እውነት ምን ያደርጉታል?

የሰባቱ ዓመታት መከራ ከፖለቲካ ከኢኮኖሚና ከህብረተሰባዊ አኗኗር አንጻር በተጨማሪም የአገሮችንና የመልክአ ምድርን አቀማመጥና ይዘት



ስንመለከት በውጪአዊ መልኩ አሁን ካለንበት እምብዛም የማይለይ ሲሆን በይዘቱ ግን ከፍተኛ አሉታዊ ለውጥ ይኖረዋል:: 2ኛ ጢሞ. 3:1-9:: መከራው በጣም ያይላል:: የሰው ስቃይ ይጨምራል:: ለሰው ጠቃሚ የሆኑ /ሮችም በአብዛኛው በእግዚአብሔር ቁጣ ይጠፋሉ:: ሆኖም ግን ሰው በሚሻውና በሚያቅደው መንገድ በቴክኖሎጂ የፈጠራ ሂደት ይራቀቃል፤ ይመራመራል:: በዚህ ሁኔታ ሳለ የመከራው ዘመን ይጀምራል:: በዚያን ዘመን ፀሎት ቤቶች ይዘታቸው በተወሰነ ደረጃ ቢለወጥም ቅርጻቸው ይኖራል:: በእውነተኛ አማኞች ዘንድ ከመጋረጃ በስተኋላና በአደባባይ ወንጌል ይሰበካል:: ወንጌል በቅንነት ይሁን በማመካኘት መሰበኩ አይቀርም:: በቅርብ ጊዜ በብዙ ሚሊዩን የሚቆጠሩ አማኞች ቅዱሳን ከዚህ ዓለም በመነጠቅ ሲጠፉ፣ ብዙ ሰዎች በከፍተኛ ናፍቆትና ፍርሃት በዳን. 12:4 እንደተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢት ይመረምራሉ፤ ያጠናሉ:: መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሰዎችን በመውቀስ ወደ እውነት ይመራል:: ከዚህም የተነሳ ብዙ ሰዎች ወደ እውነት ይመጣሉ::

ከመከራው በፊት የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ሲሆን ዛሬ በየፀሎት ቤቱ የሚሰብኩ፣ የሚያስተምሩ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ዲግሪ፣ ዲፕሎማ፣ ዶክትሬት እና ፒ.ኤች.ዲ. ያላቸው ነገር ግን ያልተለወጠ /ያልዳነ/ ሕይወት ያላቸው ሲቀሩ፣ ሁለት ባልና ሚስት /አማኝና የማያምን / በአልጋ ተኝተው ወይም በመንገድ እየተጫወቱም ሆነ እየተጨቃጨቁ አሊያም በመደባደብ ላይ ሳሉ አንዱ በቅጽበት ዓይን ቢሰወር /ቢነጠቅ/፣ አንድ ቅዱስ የዩኒቨርሲቲ ምሁር /ሌክቸረር/ በብዙ ተማሪዎች ፊት እያስተማረ ቢነጠቅና በየትምህርት ቤቱ፣ መሥሪያ ቤቱ፣ በየቤቱ፣ በየመንገዱ፣ ስፖርት ሜዳው፣ ወዘተ ያሉ ቅዱሳን ሁሉ ቢነጠቁ /ከዚህ ዓለም ቢጠፉ/ በአካባቢው ያለው ተመልካች ምን ይላል? በዚህ ወቅት በየአቅጣጫው የዘመድ ፍለጋ፣ የልጅ ፍለጋ፣ የስልክ መደወል፣ የደብዳቤ መጻፍ፣ የሬዲዮ ግንኙነትና በየመስመሩ መሯሯጡ የማይቀር የተለመደ ነገር ነው:: ማንም ሚስቱ ጠፍታ አርፎ የሚቀመጥ፣ ልጆቹ ...

ተሰውረው ዝም ብሎ የሚቀመጥ አምብዛም ነው:: ይህ ሁኔታ ሰዎችን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ይመራቸዋል::

በዚህ ወቅት ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ይመረምራሉ፤ ያጠናሉ፤ ይጠያይቃሉ:: መንፈሳዊነት አይኑራቸው እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ያላቸው ብዙ ከሃዲዎች በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ወደ ንስሃ ይመጣሉ:: በዚህም ጊዜ ነው እግዚአብሔር ለክብሩ ያዘጋጃቸውን ሰዎች የሚያስነሳው:: 144000 አይሁዶችም በዚህ ወቅት ወንጌልን ይሰብካሉ:: ሰዎችም በንስሃ ወደ ክርስቶስ ይመለሳሉ:: ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ለመግለጽ በመከራው ዘመን ይኖራል:: ምክንያቱም የቃሉ ዋነኛ ደራሲ መንፈስ ቅድስ ስለሆነ ነው::

## (15). የስላሴዎች የአሰራር ግንኙነት

በዮሐ. 15:26 መንፈስ ቅዱስ ወደዚህ እንደሚመጣ ጌታ ኢየሱስ ተናግሯል:: በዮሐ. 16:14 ላይ ደግሞ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል ይላል:: የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በዚህ ክፍል ምንድነው? የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጌታ ኢየሱስን ለሰዎች መግለጽ ሲሆን የጌታ ኢየሱስ ደግሞ አብን መግለጽ ወይም መተረክ ነው:: /ዮሐ. 15:26፤ 1:18/::

በእነዚህ ምዕራፎች የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ክርስቶስ በስጋ ወደ ምድር በመምጣት፤ ለሰው ልጆች በመስቃየት በሞትና በትንሣኤም በማለፍ በአብ ቀኝ ከሆነ በኋላ ወደፊት ወደ ምድር በመመለስ የሚፈርድ መሆኑን መመስከር ከሆነ በመከራው ዘመን ደግሞ መዳን ካለ መዳንም በኢየሱስ ከሆነ ያለ መንፈስ ቅዱስ ሰዎች ይሄንን የጌታ ሥራ እንዴት ይረዱታል? በመከራው ዘመን ጌታ ኢየሱስ በምድር የለም:: ግን ስለ እርሱ ወንጌል ይሰበካል በዮሐ. 16:13-14 እግዚአብሔር አብ መንፈሱን ለወልድ ሰጥቷል:: ወልድም መንፈሱን አፍስሷል:: ክርስቶስ መጥቶ እስኪነግሥ መንፈስ ቅዱስ የማተም ሥራውን ይቀጥላል:: ስለሆነም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከጌታ ኢየሱስ ወስዶ ሰዎችን ወደ እውነት /ኢየሱስ/ መምራት ከሆነ በመከራው



ዘመን ለሚድኑ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ይነጠቃል ማለት ከቃሉ ጋር ተባራሽ ነገር መፍጠር ነው::

## (16). የብሉይና የአዲስ ኪዳን አገልግሎት

እግዚአብሔር ለህዝቡ ከመዳናቸው ጋር በተያያዘ የሚበጃቸውን ኪዳን በተለያዩ ዘመናት ሰጥቷቸዋል:: መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስንመረምር በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል ቢያንስ ከ80 የሚበልጡ የአገልግሎት ልዩነቶችን እናገኛለን:: ከእነዚህም ውስጥ፤

| ብሉይ | አዲስ |
| --- | --- |
| የሥጋ ህግ ሮሜ 7:5-6 | የመንፈስ ህግ ሮሜ 8:2 |
| የእስራት ቀምበር /ገላ. 5:11 | የነጻነት ቀምበር /ህግ/ ያዕ. 1:25 |
| ጥላ የሆነ ሥራ ቆላ. 2:14-17 | እውነት የሆነ/የማያልፍ/ ሥራ ዕብ.10:1-18 |
| ጽድቅ በእንስሳት ደም ዕብ.9:16-22 | ጽድቅ በክርስቶስ ደም ማቴ. 26:28 |
| እግዚአብሔር የማይረካበት ኢሣ. 1:13-14 | እግዚአብሔር የሚደሰትበት/ የሚረካበት ዕብ. 10:5-18 |
| ለለውጥ የተዘጋጀ ዕብ.9፤ገላ.3 | የማይለወጥ/ዘላለማዊ ኪዳን/ዕብ.13:20 |
| ተፈጥሮአዊ ፕሮግራም ዕብ. 9:10-13 | መንፈሳዊ ፕሮግራም 2ኛ ቆሮ. 3:6፣ 18 |
| ወደ ፍጹምነት የማያደርስ ዕብ. 7:19 | ወደ ፍጹምነት የሚያደርስ ዕብ. 10:14 |
| በውድቀትና ድካም የተሞላ ዕብ. 10:11 | በብርታትና በክብር የተሞላ ዕብ. 10:10-18 |
| ምህረት የሌለበት ዕብ. 10:28 | ምህረት ያለበት /ፍጹም/ ዕብ. 8:12 |

| | |
|---|---|
| መርገምን የሚያመጣ ገላ. 3:10 | ከመርገም የሚያነጻ ገላ. 3:13 |
| ለእስራኤል ብቻ የተሰጠ ዘዳ. 4:7-8፣ 5:8 | ለሰው ሁሉ የተሰጠ ማቴ. 26:28 |

ከላይ የተዘረዘሩትን ጥቅሶች ከ2ኛ ቆሮ. 3:6 ጋር ማለትም እርሱም ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን፤ ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ህይወትን ይሰጣል ከሚለው ጋር በማነጻጸር ስንመለከተው የአዲስ ኪዳን አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ እንደሚሰራ ይጠቁመናል:: ታዲያ ይህ ከሆነ በመከራው ዘመን ለእስራኤልና ለአህዛብ የተገባው የአዲስ ኪዳን አገልግሎት ይቆማል ማለት ነው? አይደለም:: የመከራው ዘመን በዓይነቱ ከሁሉም ጊዜ ይልቅ የከፋ ይሁን እንጂ የአዲስ ኪዳንን ሁኔታ ለውጦ ወደ ፍዳነት የሚለውጥ አይሆንም:: ስለዚህ በመከራው ዘመን መንፈስ ቅዱስ አለ::

## (17). የራዕይ መጽሐፍ ምስክርነት

ራዕ. 12:17፣ 19:10 መንፈስ ቅዱስ በምድር እንዳለ ያመለክትታል:: በዚህ ክፍል ***የኢየሱስ ምስክር*** የሚለው ሐረግ በዮሐ. 15:26 እና ራዕ. 19:10 እንደተጠቀሰው የጌታ ኢየሱስን ማንነት ለአይሁዶችም ሆነ ለአህዛብ የሚመሰክር መንፈስ ቅዱስ ነው:: ዘካ. 12:10-13:: ቤተ ክርስቲያን የሚሰው ቃል በራዕይ ውስጥ ከመከራው በፊት ባለው ሁኔታ አንዴም አልተጠቀሰም ይህም አለመኖሩን ያመለክታል:: መንፈስ ቅዱስ ግን በዚህ በድቅድቅ የህይወት ጨለማ ዘመን ጌታ ኢየሱስን ሲገልጽ እናያለን:: መንፈስ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስን ይተርካል፤ ወልድ ደግሞ አብን ይተርካል:: ይህም መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን ታላቅ ሥራ እንዳለው ያሳስበናል::



## (18). የመንፈስ ቅዱስ የፀጋ ስጦታዎች መኖር

ስለ መንፈስ ቅዱስ የፀጋ ስጦታዎች በጥቂቱ ቀደም ባሉት ቁጥሮች ውስጥ አለፍ አለፍ ብዬ ጠቅሻለሁ:: በተጨማሪ ግን በመከራው ዘመን ከእግዚአብሔር ዓላማ አንጻር የፀጋ ስጦታዎች ሥራ ምን እንደሚመስል ከዚህ እንደሚከተለው አቀርባለሁ:: የመከራው ዘመን የሰይጣን የሥራ ጊዜ ሊያበቃ ጥቂት ዘመን እንደቀረው የሚያመለክት የሽግግር ወቅት ነው:: በተጨማሪም ደግሞ የእግዚአብሔርም ቁጣ የሚሰለጥንበት ጊዜ እንደመሆኑ በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል ታላቅ ተጋድሎ የሚደረግበት ምዕራፍ ነው:: ሰይጣን ዙፋኑን ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ አድርጐ የልዑልነት ቦታውን ለመቀማት መጋደል የጀመረው ከብዙ ዓመታት በፊት እንደሆነ ኢሣ. (14:12-14) ይነግረናል:: ይህ እቅዱ እስከ ዛሬ ተግባራዊ አልሆነለትም:: ሆኖም ግን ትግሉን ፈጽሞ አልተወም:: ትግሉንም በስውር በማካሄድ ላይ ይገኛል:: የዲያብሎስን ማንነትና ባህርይ በአስቆሮቱ ይሁዳና በአቤሴሎም በግልጽ ማየት ይቻላል:: 2ኛ ሳሙ. 14 እስከ 15:: አቤሴሎም በውስጡ ንጉሥ የመሆን አንድ ትልቅ ምኞት አደረበት:: ከዚህም የተነሳ ብዙ ሰዎችን አስከትሎ መስዋዕትም በማቅረብ እንደነገሠ መለከት ያስነፋል ያሳውጃል:: ሆኖም ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰለሞን እንዲነግሥ ስለነበር:: አቤሴሎም ጊዜና ሁኔታን ፈልጐ መፈንቅለ መንግሥት ለማካሄድ ብዙ እንደጣረ በኋላ ግን ለሞት አልፎ እንደተሰጠ እናያለን:: የአስቆሮቱ ይሁዳም ጌታን በመሳም አሳልፎ ለመስጠት እርምጃ ቢወስድም የመጨረሻ ዕድሉ ሞት ነበር:: በጣም በተመኙና በናፈቁ መጠን ራሳቸውን ለአደጋ አጋለጡ:: መጽሐፍ ቅዱስ ምኞት እንደሲኦል ጨካኝ እንደሆነች ይነግረናል::

ዲያብሎስን እግዚአብሔር አስቀድሞ ከተቀደሰው ተራራው /መንግሥቱ/ ጣለው፤ ቀጥሎ ደግሞ በመከራው ዘመን ወደ ምድር ይጥለዋል:: በድጋሚ ደግሞ ለሺህ ዓመታት አስሮ ወደ ጥልቅ ይጥለዋል:: በመጨረሻም ወደ ገሃነም ይጥለዋል:: ለዚህም ሁሉ ያበቃው ምኞቱ ነው:: በዚህ ሁሉ ግን ሰይጣን ከትግሉ ወደ ኋላ አላለም:: መጨረሻው እንደ ልጁ

እንደ ሐሰተኛው ክርስቶስ ይሆናል:: የዲያብሎስ በፈጣሪው ሥልጣን ላይ አምጾ ባለሥልጣን የመሆን ምኞቱ እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ በዚህ ዘመን መጨረሻም ሰዎችን ወደ ራሱ ማርከ በእግዚአብሔር ላይ በይበልጥ እንዲያምጹ ለማድረግ ልዩ ልዩ ሐሰተኞች ምልክቶችን፣ ድንቆችንና ተዓምራትን ያደርጋል:: ከዚህም የተነሳ ሰውን ወደ ገሃነም የመጣል እቅዱ በተወሰነ ደረጃ /መጠን/ ይከናወንለታል:: 2ኛተሰ.2:9-12፤ ራዕ.13:13-14:: ሰይጣን ያለ ኃይሉን በየአቅጣጫው አጠናክሮ የሰውን ልጆች በከፋት ሊበቀል ሲሰራ እግዚአብሔርም ዝም ብሎ አያየውም:: ለመንገሥ ካለው ምኞቱም የተነሣ ብዙ ሰዎችን ያስታል ዳን. 8:23::

የእግዚአብሔር እቅድ ሰውን ማዳን ወደ እውነት ሁሉ መምራት እንደሆነ ሁሉ በሐሥ. 2:22 እንደተጠቀሰው ልጁ በምድር በነበረበት ጊዜ በተዓምራት፣ በድንቆችና በምልክቶች ሰዎች ወደ ድነት እንዳመጣ ነገም በመከራው ዘመን በ144000 አይሁዶች፣ በአህዛብ፡ በሚድኑ ቅዱሳንና በሁለቱ ነቢያት አማካይነት የዲያብሎስን ሐሰተኞች ድንቅና ተዓምራት በሚውጥ ሁኔታ ክንዱን ይገልጣል::

በ1ኛ ቆሮ. 12:7-11 ያለው የመንፈስ ቅዱስ አሰራር አይለወጥም:: በመከራው ዘመን በሚኖሩም አማኞች ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ እንደተባለ መንፈስ ቅዱስ በፀጋ ስጦታዎቹ አማካይነት ራሱን፣ ወልድንና አብን ይገልጣል:: 1ኛ ቆሮ. 12:7፤ ዮሐ. 15:26:: በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ጌታ ተዓምራት ያደረገው ሰዎች እንዲያምኑ ነው፤ተዓምር ማለት ከተፈጥሮአዊው ነገር ለየት ያለ የመለኮታዊነት ሥራ ባህርይ ያለውና ሰው የማይሰራው ማለት ሲሆን ሰዎች ይህንን ሲያዩና ሲያምኑ ወደ እግዚአብሔር ከሚቀርቡበት መንገድ አንደኛው ነው:: ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ ሰይጣን በከፍተኛ ደረጃ እየሰራ ባለበትም ዘመን /በመከራው/ ጌታ ኢየሱስን ለማስተዋወቅ ክንዱን በደካማ ሸክላዎቹ እንደሚገልጽ ነው:: ይህም



የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በተሰጠው የተስፋ ቃል መሠረት እንጂ በብሉይ ኪዳኑ አሠራር ብቻ አይደለም:: ሐሥ. 2:16-17::

ከላይ የተብራሩት 18 ማስረጃዎች በድጋሚ ከሌሎች ጥቅሶች ጋር በማገናዘብ ብንመለከታቸው የመንፈስ ቅዱስን በመከራው ዘመን መኖር የሚጠቁሙ ናቸው:: መንፈስ ቅዱስ በመከራው ይሄዳል ቢባል ግን ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስን ሌሎች እውነቶች እርስ በርስ ማጋጨትና ብዙ ችግር መፍጠር ይሆናል:: ከዚህም በመነሳት መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን ይኖራል እንላለን::

የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከመከራው በፊት እንደሚሆን የተለያዩ ዋና ዋና ማስረጃዎችን በዐቢይና በንዑስ ርዕሶች ከፋፍለን ተመልከተናል:: ከጊዜና ከሁኔታ አንጻር መከልከል ስላለ እንጂ ሌሎችንም ማቅረብ ይቻላል:: ለምሳሌ፣..የዳንኤል 70ኛው ሱባኤ..፣ ..የእስራኤልና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ግንኙነት..፣ ..የመነጠቅ ዓይነቶች መነጻጸር.. የመሳሰሉት ጥቂቶቹ ማስረጃዎች ሊሆኑ ይችላሉ:: እስካሁን ባደረኩት ጥናት ስለ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ጊዜ ለአመለካከቶች መብዛትና መለያየት መንስኤው የመነጠቅ ዓይነቶችን መኖርና ቅደም ተከተል በደንብ አለማወቅ ነው:: በቅድመ መከራ መነጠቅ እንዳለ ሁሉ በድህረ መከራና በመንፈቀ መከራም መነጠቅ እንዳለ ጠንቅቆ ማወቁ እጅግ መልካም ነው:: ይህ የመካከል ለፋሪነትንና የተጠራጣሪነትን አቋም ለመያዝ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል እውነተኝነት ለመግለጽ ነው::

# ክፍል ሰባት

# ትዕይንተ መነጠቅ

**ልዩ ትኩረት:**

***ስለ ትእይንተ መነጠቅ ሲነሳ በሌሊት ይሁን በቀን ሰዎች በተለያዩ መስኮች ላይ መሆናቸው የማይቀር ነው:: ያኔ በየቦታው ያሉ ቅዱሳን ሲነጠቁ ሊፈጸም ያለውን ትእይንት በራሳችን ማስተዋልና በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ ማሰብ እንችላለን:: በአንጻሩ ደግሞ አንዳንድ ክርስቲያን አርቲስቶች ሳይንቲስቶች ሊሆን ያለውን ነገር በክርስቲያን ፊክሽን መልክ ገልጠው ማስቀመጥ እንደሚፈልጉትም አይነት ማየቱ ክፋት ላይኖረው ይችላል:: ስለሆነም በዚህ ክፍል የተገለጡትን ትዕይንቶች በሆነ መልኩ ብትተረጉሙት ውጤቱን ለታሪክና ለታሪክ ባለቤት ለጌታ እንድንተወው እናሳስባለን::***

በዘመናት መካከል ያልጠፋው መጽሐፍ ቅዱስ በያዛቸው ታላላቅ የእውነተኛ አማኞች ተስፋ ውስጥ አንዱ በሆነው በቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ነው:: መነጠቅ አፈ-ታሪክ ወይም ልብ ወለድ ሳይሆን በእግዚአብሔር የታቀደ ሊፈጸም ያለ ትንቢታዊ እውነት ነው:: የእግዚአብሔር ጊዜ ሲደርስ በዓለም የሚገኙ ቅዱሳን ከዚህ ምድር ይሰወራሉ:: ወደ ተዘጋጀላቸውም ስፍራ ይወሰዳሉ ::ዮሐ. 14:1-3:: እነዚህ ቅዱሳን የሚኖሩት በኅብረተሰቡ መካከል ነው:: ስለሆነም በህይወታቸው የሚያልፈውን ነገር ሁሉ ከሃዲዎችና ስማዊ ክርስቲያኖች እንዲሁም በሌላ እምነት ያሉ ሁሉ ይመለከታሉ:: ከመንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደትን ያገኙ እውነተኛ ክርስቲያኖች ከዚህ ዓለም ከከሃዲዎች መካከል ተለይተው ሲነጠቁ ወይም ሲወሰዱ ብዙ ነገር ይፈጸማል:: ታይቶ የማይታወቅ ለአንዳንዶችም ተሰምቶ የማይታወቅ ፈጽሞም ያልታሰበ ያልተጠረጠረ ነገር ይሆንባቸዋል:: በመነጠቅ ጊዜ በዚህ ምድር ሊፈጸሙ ይችላሉ ተብለው የታሰቡትን አንዳንዶችም በጽሁፎቻቸው ያሰፈሩአቸውን አብዛኞቹም በእርግጥ ሊሆኑ የሚችሉትን ነገሮች ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን::



## 1. በመነጠቅ ጊዜ ሊፈጸሙ የሚችሉ ትዕይንቶች

### 1.1. የቤተ ሰብ ሁኔታ

ጌታ ኢየሱስ በማቴ.19:13-14 እና በ18:1-10 እንዲህ ሲል ናግሯል:: .....ሕጻናትን ተዉአቸው፣ ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ ትከልክሏቸው፤ መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉት ናትና...:: ከዚህ ቃል መነሳት የእግዚአብሔር እስትንፋስ የተሰጣቸው ሕጻናት ሁሉ ይነጠቃሉ ለት ነው:: የእድሜው ጣሪያ ሙሉ በሙሉ አይታወቅም፤ ይህ ሚስጢር እኛ አልተገለጠም:: አንዳንዶች ከ7-9 ዓመት እድሜ ያላቸው በሕጻናት ልል ይጠቃለላሉ የሚል አቋም አላቸው:: የቀሩት ደግሞ ከ5 ዓመት በታች ሉ፤ ከሌሎቹ ደግሞ ልጆች ከፋና መልካሙን የሚለይ ህሊና እስካሌላቸው ረስ ይነጠቃሉ የሚሉም አሉ:: የልጃቸው እድሜ 7 ዓመት ከአንድ ቀንና 9 መት ከ5 ወር የሆኑ ወላጆች ይህንን በተመነው ሰው ላይ ፈራጅ እንዳይሆኑ ድሜውን ገደብ ለጌታ እግዚአብሔር ትተን ወደ ትእይንቱ መመለሱ የተሻለ ው::

#### 1.1.1. ሙዋዕለ ሕጻናት

ታዳጊ ሕጻናት በወላጆቻቸው አማካይነት ወደ መዋዕለ ሕጻናት ልከዋል እንበል፤ አስተማሪዎቻቸው በሙሉ ወይ በከፍል እያስተማሯቸው ሊያም ደግሞ ለእረፍት ወጥተው ሕጻናቱ ሲሯሯጡ፤ ሲጣሉ ሲታገሉ፣ ሳሳቁ እየተመለከቱ ሊሆን ይችላል:: ምናልባት ይህ የታዳጊ ሕጻናት መዋያ ተማ መካከል ሊሆን ይችላል:: ብዙ የከተማው ህዝብ በአጥር ላይ ንጠልጥሎ ወይም አሾልኮ የሚሆነውን እየተመለከተ ቢሆን፣ በዚህ ወቅት መለከት ቢነፋ፣ እነዚህ ሕጻናት ምን ይሆናሉ? የተገባቸው ሁሉም ባሉበት ቅጽበተ ዓይን ተለውጠው ይነጠቃሉ ማለት ነው:: ወደ ቤታቸው ሚመለሱበት ሰዓት ደርሶ ወላጆቻቸው መኪኖቻቸውን አዘጋጅተው ጠብቋቸው የሕጻናቱ መሰወር ሪፖርት ሲደርሳቸው ምን ይላሉ? በዚህ

ሁኔታ ከሕጻናት ታሪክ ጋር ብቻ በተያያዘ በመላው ዓለም የሚወራውንና በወላጅ ህይወት የሚያልፈውን ስቃይ አእምሮ ያትኩርና ይረዳው:: ልጅን መልሶ ለመሳምም ሆነ ለማየት መንገዱ አንድ ብቻ ነው:: ይኸውም ቶሎ ንስሀ ገብቶ ጌታን በመቀበል ዳግመኛ መወለድ ነው::በእናት እቅፍ ያሉ ሕጻናት ዘጠኝ ወር ተሸክማ፣ መቼ ወልጄ አቅፌ ስሜ በማለት ለረጅም ጊዜ ትናፍቅ የነበረች እናት ወልዳ ከባሏ ጋር ቁጭ ብለው ልጃቸውን ወደ ላይ ሽው ሽው እያደረጉ ሲያጫውቱ መለከት ተነፍቶ በቅጽበተ ዓይን ልጃቸው ስትሰወር (ሲሰወር) ክርስቶስን የማያምኑ ወላጆችና የቅርብ ተመልካችስ ምን ይሉ ይሆን?

### 7.1.1.2. <u>የልጆች የልደት ቀን</u>

ወላጆች በየዓመቱ የልጃቸውን ልደት ያከብራሉ:: ዘመድ ጓደኛ ፎቶ አንሺ (ካሜራ ማን) የልጃቸው ጓደኞች ሁሉ ለታላቅ ደስታ ይጠራሉ፤ የሚበላው የሚጠጣው ስጦታውም ሁሉ ይጎርፋል:: ሁሉ ነገር ተዘጋጅቶ ፌሽታው ሊጀምር ደቂቃ ሲቀር ኃጢአት የማያውቃቸው ሕጻናት በሙሉ ቅዱሳን የሆኑ ጌታን በትክክል ያመኑ ወላጆች ከሕጻናቶቻቸው ጋር ከዚህ ዓለም ሲነጠቁ በስመ ክርስትና እየኖሩ እግዚአብሔርን የሚያሳዝን በደል የሚፈጽሙ ሰዎች ልጅ አልባ ሆነው በድንጋጤ ሲፋጠጡ ማየት እጅግ ያሳዝናል:: ተጠያቂው ማነው? ተከሳሽስ ይኖር ይሆን? ከዚህ ለመዳን ብቸኛው መፍትሄ ቶሎ ዳግመኛ መወለድና እንደ ሕጻናቱ መሆን ነው:: መቴ.18:3::

### 7.1.1.3. <u>የሞት አፋፍ ሕጻን</u>

ወላጆች ልጃቸው በከፍተኛ ሕመም እየተሰቃየ ተቸግረው ወደ ሆስፒታል ይዘው ይሄዳሉ እንበል፤ እንደደረሱ የሕጻናቱ ዶክተር ተቀብሎ እያገላበጠ ካየ በኋላ መርፌና መድኃኒት እየለጠ እያለ ሕጻኑ በመነጠቅ ቢጠፋስ? ወላጆች ምን ይላሉ? ዶክተሩስ? የዘመኑ ዶክተሮች ከአስማት ጋር ጥብቅ ወዳጅነት ጀምረዋል:: በአስማት ልጃችንን ሰወረብን ብለው ዶክተሩን



ከሰስ ይጀምሩ ይሆን ወይስ ባልየው መሣሪያ ይዞ ከሆነ ልጃችንን ውሰድ ሎ ዶክተሩን አፋጥጦ ይይዝ ይሆን? የወላጆቹስ ልብ? በእንቅርት ላይ ጆሮ ግፍ አይደል? ጌታ እግዚአብሔር ከዚህ ውርደት ና ሐዘን ይጠብቀን:: የቤተ ርስቲያን መነጠቅ እንደሆነ ወዲያው የመከራው ዘመን ይጀምራል:: ናልባት እግዚአብሔር ሐጢአተኞችን ከሚቀጣባቸውና ለመከራ ሚገልጥባቸው መንገዶችና አሰራሮች ውስጥ አንዱ ልጃቸውን በመከራው ጀመሪያ ላይ ከእጃቸው ነጥቆ በመውሰድ ይሆን? አንዳንድ የሥነ መለኮት ሁራን እግዚአብሔር ሕጻናትን ለመከራው ዘመን አሳልፎ ቢሰጥ በእውነት ይህ ለእርሱ የጽድቅ ሥራ ስለማይሆን በመነጠቅ ሥርዐት ወደ መንግሥቱ ማሳለፍ ይታደጋቸዋል ይላሉ:: በዚህ ቅጣትና መከራ ጌታ የክፉ ወላጆችን ልብ የሚያገኝና የሚመልስ የሚያድናቸውም ቢሆን ድንቅ አሰራር አይደል?

ይህንንና ሌላውንም የመሰለ ነገር ማሰብ ይቻላል:: አእምሮን ሰፋ አድርጉ በጽሞና ተቀምጦ በቅንነት ለመረመረ ሰው በእግዚአብሔር እርዳታ ነገር ሊሰወርበት አይችልም:: እናንተ ወላጆች ዛሬ የጋለሞታይቱን ቤተ ክርስቲያን ድምጽ (ስብከት) ሳይሆን የእውነተኛይቱን ቤተ ክርስቲያን ድምጽ ብትሰሙ እጅግ ይመረጣል:: በእውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል እንጂ በብዙሃን ድምጽ፣ በሆያሆዬ ድምጽ አትሂዱ:: የማንም ንግግር አይጎትታችሁ የማንም ወሬ አይግፋችሁ:: ነገር ግን በቃሉ አማካይነት እውነትን በመመርመር መኖር ይበጃል::

### 7.1.1.4. <u>ባልና ሚስት</u>

በአሁኑ ጊዜ በዚች ምድር ላይ ከሚኖሩት ውስጥ ጥቂቶቹ ባልና ሚስት ናቸው:: ሁለቱም ጌታን ክርስቶስን በትክክል አምነው መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ሊሆን ይችላል:: አሊያም ከሁለት አንዱ ሊያምን ይችላል:: ሚስት ብታምንና ባልየው ባያምን ይህም ባል ተሳዳቢ፣ ተጨቃጫቂ፣ ነገረኛ ስኒ ሰባሪ: ቴሌቭዥን ረጋጭ ...ቢሆንና አንድ ቀን በሆነ ነገር ይጣላሉ እንበል:: ባልም እንደልማዱ በትሩን አንስቶ ሚስቱ በተኛችበት ያለ ርህራሄ በያዘው

በትር ወይም መሳሪያ ሲመታ ሲል መለከት ቢነፋና ያቺ ክርስቲያን በቅጽበተ ዓይን ብትሰወር ያም በትር አልጋው ላይ ቢያርፍ ባል ምን ይላል? ዱላው ተመልሶ የሚመታው መስሎት በድንጋጤ ይወድቅ ይሆን? የሚያምኑ ባሎቻቸውንም የሚያሰቃዩ ሚስቶችም እንዲሁ አሉ:: እነርሱስ ምን ይገጥማቸው ይሆን?

### 7.1.1.5 ልጆችና ወላጆች

በአሁኑ ጊዜ የቤተሰብን አቋም ስንመለከት፣ በሙሉ አማኝ የሆኑ፣ እናትና አባት ዳግም ያልተወለዱ ልጆች ግን በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉና የዳኑ፣ ጥቂት ልጆች ጌታን የተቀበሉ ጥቂት ያልተቀበሉ፣ አባትና ልጆች ወይም እናትና ልጆች ጌታ ኢየሱስን አምነው የቀሩት ያላመኑ ቤተሰብ ያሉአቸው ይኖራሉ እንበል:: ከዚህ ሁኔታ ውስጥ እናትና አባት ጌታን ያልተቀበሉና በመንፈስ ቅዱስ ያልተጠመቁ ሆኖም 10 ልጆች ያሉት ቢሆኑ ልጆቻቸውም በሙሉ ዳግም የተወለዱና ጌታቸውን በተለወጠ ሕይወት የሚያመልኩና የሰርጋቸው ቀን በተከታታይ የቀረበ የሃብታም ልጆች ናቸው እንበል:: አንድ ቀን ቤተዘመዱ ጎረቤቱም ሁሉ ያሰበት ልዩ ግብዣ ቢደረግና እየበሉ እየጠጡ እየተደሰቱ ሳለ መለከት ቢነፋ ልጆቹ ሁሉ ሲነጠቁ ወላጆች ግን ይቀራሉ:: ይህንን ነገር ወላጆችና ሌሎች እድምተኞች ምን ይሉት ይሆን?

### 7.1.1.6. ሰካራም አባት

እስከ ሌሊቱ 6 ሰዓት ሲጠጣ ቆይቶ በጣም ሰክሮ ወደ ቤቱ ሲሄድ ሳለ ልክ በሩ ላይ ሲደርስ ጭንቅላት የሚፈነክት የበረዶ ናዳ ያለው ዝናብ ቢጥል፣ በሩ የተቆለፈና አማኝ ቤተሰቡ ከ15 ደቂቃ በፊት ተነጥቀው ቢሆን ይህ ሰው ምን ይደርስበታል? በማለዳስ ምን ይል ይሆን?



### 1.1.7. ከእንቅልፍ በኋላስ

ቤተሰብ በሙሉ ማታ በሰላም ተኝቶ ጠዋት ወደ ስራ ለመሄድ ሲነሱ ማሹ የሚያምነው ሲጠፋ ግማሹ ሲቀር ይህ በተመልካቹና በአስተዋዮች ይወት ምን ይፈጥርና ያሳድር ይሆን? ምንስ ይከተላል?

### .1.2. የተሽከርካሪዎች ሁኔታ

### .1.2.1. መኪኖች

በዓለም ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ ያለበት በቀን እስከ ሦስት ሚሊዮን መኪኖች የሚመላለሱበት መንገድ (አደባባይ) በሜክሲኮ ይገኛል:: ማለዳ ሰው ሁሉ ወደየ ሥራው ሲሮጥ ከእነዚህ ሁሉ መኪኖች ውስጥ 28 መቶው የቅዱሳን ናቸው እንበል:: በዚህ የከፍተኛ ፍጥነት ጉዞ ላይ እያሉ ኋለኛው መለከት ቢነፋ እውነተኛ ክርስቲያኖች ሁሉ ሲነጠቁ መኪኖቹ ያለ ሾፌር በከፍተኛ ፍጥነት የመብራት ህግ ጥሰው ሌላውን ሲገጩ የሚፈጠረውን እልቂት፣ የንብረት መውደም ማሰብ ይቻላል:: መኪኖች ከመንገድ በመውጣት ትልልቅ ህንጻዎችን ሲያፈርሱ፣ እግረኛውን ተጓዡና እንስሳውን፣መናፈሻ የቆሙትን ሌሎች ልዩ ልዩ ተንቀሳቃሾችን ሁሉ ሲያነጉዱ ምን ይባል ይሆን?

ሁኔታው ሁሉ እጅግ አሳዛኝ ይሆናል:: ከተገዛች ሁለት ቀን ያልሞላት ዘመናዊ መርሰዲስ፣እየተነዳች ሳለ መልስ የሚሰጥ ባለቤት የሌለው መኪና ከኋላ መጥቶ ሲገጫትና እንዳልነበረች ሲያደርጋት ሌሎችም መኪኖች ርስ በርስ ተነባብረው ሲጋጩና ብዙ ሰው ሲያልቅ እንዴት ይከብድ ይሆን? ከአዲስ አበባ ወደ ጂማ ወይም ድሬዳዋ ሲኬድ በግራና በቀኝ መኪና ላይ ሆኖ በሚታየው ገደል ሲደረስ መለከት ቢነፋና ሾፌሩ ዳግም የተወለደ ከሆነ ይነጠቃል:: ሌሎች ግን ጌታን ያልተቀበሉ ሁሉ ባለው ገደል ውስጥ ከነመኪናቸው ይሰምጣሉ::

### 7.1.2.2. <u>አውሮፕላን</u>

በቀደሙትም ሆነ በአሁኑ ጊዜ ቅዱሳን የሆኑ ፓይለቶች (አይሮፕላን አብራሪዎች)በየ አገሩ ይገኛሉ:: አንድ ፓይለት ከአንድ አገር ተነስቶ ወደ ሌላው አገር በበረራ ላይ ቢሆን፤ ምናልባት አውሮፕላኗ በሕንድ ወይም ሰላማዊ ውቅያኖስ ላይ ስታንዣብብ መለከት ቢነፋ ፓይለቱ አማኝ ከሆነ በቅጽበተ ዓይን ተሰውሮ ይነጠቃል:: አውሮፕላኗ እየተምዘገዘገች እየተገላበጠች በውስጧም ያሉ በመንፈስ ቅዱስ ያልተጠመቁ አማኝ (ክርስቲያን) ነን ባዮች ወደ ውቅያኖሱ ውስጥ መስጠማቸው የማይካድ ሐቅ ነው:: በተመሣሣይ ሁኔታና መልኩ በዓለም ልዩ ልዩ ቦታዎች ይቀጥላል::

### 7.1.2.3. <u>ብስኪሌት (ሞተር ብስኪሌት) የሚነዳው</u>

በከተማም ሆነ በገጠር መንገዶች ላይ ተራ ተጫዋቾችና ኮርሰኞች ሲወዳደሩ እናያለን:: ውድድር ሲካሄድ በመኪና እየተከታተሏቸው ቆይተው ማብቂያው ላይ ሲደርሱ ከእነዚሁ ኮርሰኞች (ተወዳዳሪዎች) ሁለቱ ህያው አማኞች ቢሆኑ ህዝቡ እያጨበጨበ ሊቀበላቸው ሲወጣ መነጠቅ ቢሆን እነርሱ ሲነጠቁ ሰው የሌበት ቢስክሌት (ሞተር ሳይክል) እየሮጠች መጥታ ስትገጫቸው ምን ይባላል? አንድ ሌላ ተራ የሆነ ብስኪሌተኛ እየነዳ ቢነጠቅ ሰው የሌለባት ብስኪሌት ከኋላ መጥታ በሰላም የሚሄደውን መንገደኛ ስትለትመውስ? በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሌሎች ብዙ ነገሮችን ማሰብ ይቻላል::

### 7.1.3. <u>የቅዱሳን (ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች) ሰርግ</u>

በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሙሽራውና ሙሽሪት ከአጃቢዎች ጋር ገብተው የምሳ ግብዣ ስነ ሥርዓት ሲፈጽሙ ሁሉም በዝግጅት ላይ ነው እንበል:: ከዚህ ሰርግ እድምተኞች ውስጥ የሙሽሪትና የሙሽራው ከፊል ዘመዶችና ጓደኞች በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ያልተወለዱና በፈጣሪ መኖር የማያምኑ ቢሆኑ ለሙሽሮቹና ለእድምተኞቹ የምሳ ግብዣው ሊቀርብ ሲል ሁሉም በዝግጅት ላይ እንዳሉ መለከት ቢነፋ በሠርጉ ያሉ ሙሽሮችና የዳኑ



ዝብ በሙሉ በመነጠቅ ይሰወራሉ:: በዚህ ሁኔታ ላይ ያሉና ይህንን ሚመለከቱ ወላጆችና ሌሎች ታዳሚዎች ምን ይሉ ይሆን? ወይኔ ልጄ ከርግሽ እለት እንዲህ ተዋረድሽ! ወይኔ ልጄ! ቀኝ እጄ ተቆረጠ! ከአሻሮ ይነት ወጣሁ ስል እንዲህ ሆኖ ቀረ! አዬ! አዬ! ጉድ ይባል ይሆን?:: ወይስ ሉም ግራ ተጋብቶ ዝም ይባል ይሆን? ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች ግን ነጥቀዋል:: በዚህ ትዕይንት ህዝብ ምን ይሰማው ይሆን?

እውነተኛ ክርስቲያኖች ያልሆኑ እናት አባቱን ወይም የሌላ ዕምነት ከታይ የሆኑ ወላጆቹን በመኪና ይዞ ከአዲስ አበባ ወደ ሐረር የሚጓዝ ዛዥር ልጅ አማኝ ነው እንበል:: መተሃራ ሐሩር ሲደርሱ መለከት ቢነፋ ቅጽበተ ዓይን እንደሚሰወርና ወደ ተዘጋጀለት ሰማያዊ ስፍራ እንደሚሔድ ሙን ነው:: መኪናው ውስጥ ያሉ እነዚያ ሰዎች ምን እንደሚደርስባቸው ገመት አያስቸግርም? በጣም ጨለማና አስቃቂ ለአዕምሮም የሚከብድ ሉታዊ ትዕይንት ሊሆን ይችላል::

እነዚህንና ሌሎችንም የመሳሰሉ ነገሮች መልካቸውና አቀራረባቸው ንሽ ለወጥ ቢልም በቅርብ ጊዜ በዚህ ምድር ኀጢአተኞች ነዋሪዎች ላይ ደርሳሉ:: ሊመጣ ያለው ይህ ክፉ ነገር እንዳይደርስብን ከሚመስልና ተሳሳተ ሃይማኖት (እምነት) ወጥቶ እውነተኛውን የሚያድን ዕምነት ሬውኑ መያዝ ነው:: ልበ ጠንካራና ግትር ከመሆን ግራና ቀኙን ማየቱና ግስተዋሉ ትክክለኛ አቋም ነው:: ቶሎ ወደ አዳኙ ጌታ ኢየሱስ ተመለስ::

### .1.4. <u>በየሥራ መስኩ ያሉ ቅዱሳን</u>

በአሁኑ ጊዜ የእግዚአብሔር ልጆች (መንፈሳዊ ሰዎች) በትምህርት ቶች በዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች በፍርድ ቤቶች በሆስፒታሎችና ወዘተ ታዎች በብዛት ይገኛሉ:: ባሉበት ሁኔታ ሳሉ መለከት ቢነፋ በቅጽበተ ዓይን ሰውጠው ወደ ሰማይ ይወሰዳሉ:: ለምሳሌ አንድ ክርስቲያን መምህር ዩኒቨርሲቲ ወይም በኮሌጅና በከፍተኛ መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

በብዙ ተማሪዎች ፊት እያስተማረ ሳለ መለከት ቢነፋ ይነጠቃል። ይህ መምህር በጥቁር ሰሌዳው ላይ እየጻፈ፣ ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ንግግር እያደረገ ሊሆን ይችላል መለከት ቢነፋ ወይም ወደዚህ ውጣ የሚል ድምጽ ቢሰማ ሁሉም እያዩት ወዴት እንደሔደ ሳይታወቅ በቅጽበተ ዓይን መሰወሩ አሌ የማይባል ሐቅ ነው። በዚህ መምህር መሰወር ብቻ እንኳን የሚወራው ወሬ ዓለምን ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ ሊያጥለቀልቅ ይችላል። እንኳን በሺህና በሚሊዮን የሚቆጠሩ መምህራን ከምድር ገጽ ጠፍተው (ተሰውረው) ይቅርና። በየአገሩ በዚህ ዓይነት መልኩ ብዙ ክርስቲያን ሰራተኞች ቢጠፉ ለአንዲት አገር ቀላል ውድቀት ይሆን? በዚሁም የሰባቱ ዓመታት መከራ ይጀምራል። ታላቅ ቀውስም ይሆናል። በዚህም መንገድ እግዚአብሔር ወንጌል ለሰዎች እንዲነገር ያደርጋል። በኢዮብ 33:14 ላይ እግዚአብሔር በአንድ መንገድ በሌላውም ይናገራል፤ ሰው ግን አያስተውለውም ይላል። ይህ መነጠቅ ሲሆን ስታዩ ወንዶችም ሆናችሁ ሴቶች ይህ የጻፍኩላችሁ ምልክት ይሁናችሁ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ አማኝ ክርስቲያኖች ከምድሪቱ ላይ ሲጠፉ ስትገነዘቡ ያ መነጠቅ እንደሆነ ልብ በሉ፤ አስተውሉ፤ ይህ እንደሆነ ወዲያው የሰባቱ ዓመት ወይም የ3 ተኩል ዓመታት መከራ ይጀምራል፡ አውሬውም በሐይል ስለሚሰራ መከራው ይደርስባችኋል። ንስሀ ከገባችሁ ግን ቆይታችሁ በመነጠቅ ወይም በመሞት ወደ ዘላለም ህይወት ትደርሳላችሁ። ጌታን በትክክል ያልተቀበላችሁና ያላገኛችሁ ከሆናችሁ ከወዲሁ አዳኙን ክርስቶስ ኢየሱስ ክርስቶስን ብትቀበሉ አብረን እንነጠቃልን፤ሆኖም ግን ይህ የመነጠቅ ዕድል ቢያመልጣችሁ ፊታችሁ የታላቁ መከራ ዘመን ይጠብቃችሁአል፤ ንስሐ ከገባችሁ የአውሬውን መከራ ተቀብላችሁ ትድናላችሁ።

ብዙ ክርስቲያን (ቅዱሳን) ዶክተሮች በአሁኑ ጊዜ በየሆስፒታሉ ይገኛሉ። ሁለት ወይም ሦስት ዶክተሮች አንድን በሽተኛ ቀዶ ጥገና በማድረግ እያስተናገዱ ነው እንበል። ሌሎች ጌታን ያልተቀበሉ ዶክተሮችም ቢኖሩ የህመምተኛውም ቤተሰቦች በውጭ በሃዘን ላይ ቢሆኑ ወደ ሰማይ ጥሪ



ቢደረግ ቅዱሳን ዶክተሮች በሙሉ ከሆስፒታሉ ይሰወራሉ። አካባቢው (ተመልካቹ) ይህንን ምን ይላል? የበሽተኛው ቤተ ዘመዶች ያንን ሁኔታ ቢሰሙ ዶክተሮች ሲጫወቱ ሲቀልዱ ዘመዳችንን ገደሉት ብለው ክስ ይመሰርቱ ይሆን? ሊላም ማሰብ ይቻላል።

እናንተ ክርስቶስን እናምናለን፣ ክርስቲያኖች ነን ወይም ደግሞ መንግስተ ሰማይ እንገባለን የምትሉ ሆኖም ግን ጌታ ኢየሱስ በማቴ.8:22 እንደተናገረው <u>በቁም መንፈሳችሁ የሞተ</u>፣ ረጋ ብሉ በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ ራስን በመመርመርና የታማኝ አገልጋዮችንም ምክርና ምሪት በማግኘት ህይወታችሁን አስተካክሉ። (***<u>ዝርዝር ነገሮችን ከክፍል 10 እና 12 ውስጥ ይመልከቱ</u>***) የመንፈስ በኩራት የሌላችሁ የወደዱት ሁሉ በምኞት አይገኝምና ቶሎ ብላችሁ ዳግመኛ ተወለዱ። ለዚህም ትክክለኛውን የደህንነት መንገድ ምሪት የሚያሳዩአችሁ ቅዱሳን አማኞች በየቦታው ይኖራሉ። ከእነዚህም ውስጥ ብዙዎች <u>ጴንጤ</u> ብለው የሚጠሩአቸው ቅዱሳን ናቸው። እነዚህ ጴንጤ የሚባሉ ቅዱሳን በአሁኑ ጊዜ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናቱም፡ በግልም፡ በካቶሊኩም፡ በኦርቶዶክሱም፡ በፕሮቴስታንቱም፡ ወዘተ ይገኛሉ። ከፍሬአቸው ስለሚታወቁ ጠጋ ብላችሁ ካሁኔው ሳይነጠቁና ሳይጠፉ አነጋግሩአቸው። አሁን ያለው ጭላንጭል ተስፋ ወደ ድቅድቅ ጨለማ (ጭንቅ) ሳይለወጥ መጽሐፍ ቅዱስን አንብቡ፡ የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ጠይቁ፡ እነርሱንም አማክሯቸው። ከሁሉም በላይ ከተማጸናችሁት መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል ።ዮሐ. 8:11-13። እርሱ የመጣው ለስራ ነው።

## 7.1.5. <u>ልዩ ልዩ አካባቢዎችና ስፍራዎች</u>

በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ የታወቁ መንፈሳዊ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች በውስጣቸው እውነተኛ አማኝ ሳይሆኑ ነን ብለው የገቡትን፣ በውጭ ቆንጆ መስለው ውስጥ ለውስጥ ጌታን የካዱትን፣ በግልጽ ተቃዋሚ የሆኑትን፣ እውነተኛ የሆኑትንና ለውጥ ያላቸውን ቅዱሳን ይዘዋል። ከመምህራኑም፣

ከተማሪዎቹም፣ ከቢሮ ሠራተኞቹም የእነዚህ ዓይነት ሰዎች ይኖራሉ:: መስከት ሲነፋ የቆሙ የሚመስላቸው መውደቃቸውን የሚያውቁት አብሯቸው ይፈጭ(ተመሳሳይ ሥራ የሚሰራው) የነበረው ከአጠገባቸው ሲነጠቅ ነው:: ሰዎች ይህንን ሁሉ ሲያዩ ንስሀ ይገባሉ ወይም ልባቸውን ያደነድናሉ:: ከተመለሱ ደግሞ ይድናሉ::

በዓለም እጅግ ታላቅ የሆነ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ቅዱሳንን የያዘ ፀሎት ቤት አለ እንበል:: በዚህ ፀሎት ቤት ዓመታዊ ኮንፍራንስ ቢዘጋጅና ብዙዎች ቢጋበዙ በዚህ ግብዣ የሰው አባቦችና እፉኝቶች፣ ችግር ያባረራቸው መንታፊ ሌቦች፣ እውነተኞች፣ ሞራሊስቶች፣ ለማኞች፣ ሆድ የባሳቸው: ለመዝናናት የመጡ መኖራቸውን ልብ እንበል:: ከወደ ሰማይ የጥሪ መለከት ቢነፋ ዳግም የተወለዱ ሁሉ ሲነጠቁ ሌላው እንዳለ ይቀራል:: ሰዎቹ ሲነጠቁ ወርቃቸው: በሰውነታቸው ላይ ያሉት ጌጣ ጌጦች አብረው አይነጠቁም፤ መኪኖቻቸውን: በመኪኖቻቸው ውስጥ ያሉትን ንብረቶች በሙሉ ትተው ነው የሚነጠቁት፤ ታዲያ ሌቦቹም ሆኑ ሌሎች ያንን ሁሉ ሐብት መሬት ወድቆ ሲመለከቱ ዝም ብለው ትተው ይሄዱ ይሆን? ወይስ ከሌቦቹ ጋር ይተባበሩ ይሆን? ስንቱንስ ትተው ስንቱን ይወስዱ ይሆን? ወስደውስ ምን ያህል ይባረኩበት ይሆን? ዳሩ ምን ያደርጋል ወዲያው የመከራው ዘመን ይቀጥል የለ? መንግስት ደግሞ በቤቶቻቸውና በማምለኪያ ቦታዎቻቸው ላይ ምን አዋጅ ያወጣ ይሆን? እውነተኛ ለውጥ ያላቸው ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች ሁሉ ያላቸውን ጥሪት በሙሉ ጥለው ይሄዳሉ:: መጨረሻው ይሔው ነው:: አንተም እውነተኛ ቅዱስ ሆይ መመሪያህ ቆላ. 3:1-3 ይሁን:: ልብህ አይክበድ ተጠንቀቅ(ቂ)ም: ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንደዚህ ወዳለው የክበረ ሕይወት ሲያመጣን ነውና የክበረ የህይወት የሆነውን ወርቃችንን በእርያ አፍንጫ ላይ አናውለው :: ትጋ(ጊ)ና የመነጠቁ ባለቤት ለመሆን ተፋለም(ሚ):: እንፋለም::

ሌላው አስደናቂ ትዕይንት ከሚካሔድባቸው ስፍራዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የመቃብር ሥፍራዎች ናቸው:: አንዳንዱ ዘመዱን ከቀበረ አንድና ሁለት ቀን ሲሆን ይችላል:: ሰው ሁሉ ወደ መቃብር ስፍራዎች ሩጫ



ይቀጥላል:: ታይቶና ተሰምቶም የማይታወቅ አዲስ ነገር ለብዙዎች ሰዎች ይሆናል:: መቃብሮች ባዶ ናቸው:: በድኖች ተነስተዋል:: ለቅሶ ይሆን ደስታ? ወይም ትካዜ ወይስ መቀወስ? አንዳንድ ለውኮ በድን ተነስቶ ጠፋብኝ ብሎ ያለቅስ ይሆናል? ግራ ሲገባ እኮ እንዲህ ያደርግ ይሆናል:: ሰው ከእውነተኛ ፈጣሪው ሲርቅ እኮ ይዘበራርቀውና ይዘበራረቅበታል:: አያድርስ ሲባል የሚገባው ይሄ ነበር:: ምን ይሆን ይህንን ህዝብ የሚገጥመው?

አንዳንድ ቀልጣፋ የሆኑ የመሰላቸው ቤተሰቦች ልጆቻቸውን በመንፈሳዊ ተቋሞች አስገብተዋል:: ለካስ ልጆቹ እዚያ ገብተው ጌታን አግኝተው ኖሮአል:: መለከቱ በተነፋ ገዜ ተነጥቀዋል:: የመነጠቅን ወሬ ሰምተው ወደ ኮሌጆች እየሮጡና መኪና እያበረሩ ሲደርሱ አብዛኞቹ ተነጥቀው የራሳቸውም ልጅ ተነጥቆ ያገኙታል:: በአንድ በኩል ደስታ በሌላ በኩል ደግሞ ኃዘን ይሆናል::

እናንተ በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠራችሁ ሁሉ ምርምራችሁ ጥሩ ቢሆንም (ዳን. 12:4) መስመር የሳተ ምርምርና እውቀት ለትንሽና ዘለቄታ ለሌለው ህይወት ብቻ ይጠቅማል:: ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን በትክክል እንዳታውቁና በህይወታችሁም ክርስቶስ ገዢና ጌታ ሆኖ እንዳይኖር እንዳይጠቅማችሁም የሚከለክልን ምርምር ሁሉ ልትቃወሙት ይገባል::

ዛሬ በዓለማችን ይጐዳል የተባለው ሲጠቅም ይጠቅማል የተባለው ደግሞ ሲጐዳ፤ ክፉ የተባለው ደግ፣ ደግ የተባለው ክፉ ሲሆን ይታያል:: ስው ወድዶ አይሰክር፣ ወድዶ አይወድቅ፣ ወድዶ አይሰበር:: አንተም ስው ሆይ ህይወትህ ለአንተ እንቁ ነው:: ገና ስትፈጠር ልትንዝበት የሚገባ የህይወት ህግ በአንተ ውስጥ ተቀምጧል:: ያስቀመጠውም እንደዲያብሎስ ሐሰት የሌለበት እውነተኛው ፈጣሪ እግዚአብሔር ነው:: ያንን ፈልገህ በማግኘትና የሙጥኝ በማለት ፈጽሞ ልትመራበት ይገባል:: ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ተመለስ:: መጽሐፍ ቅዱስን ከዓለም መጻሕፍት ሁሉ ልዩ የሚያደርገው

የእግዚአብሔር መንፈስ ስላለበት ነው:: ስለዚህ ማንበብ ማንበልበል ብ
ሳይሆን አጥናው (ብላው) ለሁሉም ጸታ እውነቱ አንድ ነው:: ሕዝ. 3:1-3
ኤር. 16:16፣ ቆላ. 3:16::

## 7.2. የመነጠቅ ውጤቶች

ይህ የመነጠቅ ሥርዓት እንደተፈጸመ በተከታታይ የሚፈጸሙ እጅግ ብዙ ነገሮች ይኖራሉ:: ከእነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው::

7.2.1. በሎጥና በኖህ ዘመን እግዚአብሔር በእርሱ ያመኑትን ቅዱሳን በመርከብና በመላዕክት ኃይል ከለያቸውና ካዳናቸው በኋላ ቁጣውን በኃጢአተኞች ላይ አፍስሷል:: አሁንም ደግሞ በልጁ በክርስቶስ ዘመን የእርሱ የሆኑትን በመነጠቅ ሥርዐት ይወስድና በቀሩት አመጸኞች ላይ ቁጣውን ያፈሳል::

በምድር የቀረ ሰው ሁሉ በተወሰነ ደረጃ በራዕይ ከ6-19 የተጠቀሱት መቅሰፍቶች ደረጃ በደረጃ ይደርሱበታል:: ይህም የሚሆነው በተነገረው ትንቢት መሰረት ነው:: በራዕይ 11:10-12 ላይ

*«...አህዛብ ተቆጡ፤ ቁጣህም መጣ:በሙታንም ትፈርድ ዘንድ ዘመን መጣ: ለባሪያዎችህም ለነቢያትና ለቅዱሳንህ ስምህንም ለሚፈሩ ለታናናሾችና ለታላላቆችም ዋጋቸውን ትሰጥ ዘንድ ምድርንም የሚያጠፉአትን ታጠፋ ዘንድ ዘመን መጣ»* ተብሎ ተጽፎአል:: ይህ ዘመን ጌታ የሚበቀልበት ዘመን ይሆናል ማለትነው:: የሰሰው ልጅ ይህ ወቅት እጅግ አሰቃቂ ይሆናል::

7.2.2. በሰማይም በእግዚአብሔር ቅዱሳን መላዕክትና በዲያብሎስ መላዕክት መካከል ጦርነት ይሆናል:: የእግዚአብሔር ወገኖች ሲያሸንፉ ርካሳኑም ወደ ምድር ስለሚወድቁ ለምድር ነዋሪዎች አሰቃቂ በትር ይሆናል::ራዕይ 12:12-17::

7.2.3. በየቤቱ ስልክ ሊደወል ይችላል:: አባትና እናት ልጃቸው፣ እህት ወንድማቸው፣ ልጆች ወላጆቻቸው ወዘተ ስለጠፉ ሁሉም በጥያቄ ይሞላሉ::



ሰብ አማኝ ልጆቻቸውን ሊድሩ ብዙ ወጪ አድርገው ሰርጉ እንደነገ ሆኖ መነጠቅ ቢሆን ምግቡ እንዳለ ሊተውና ሊበላሽ ነው:: የሚበላውም ዘን ይኖናል:: በሁሉም አቅጣጫ የመፈላለጉ ጉዳት ይቀጥላል::

4. የሐሰት ወሬ ከከሃዲ መንግስታት ሊወጣ ይችላል:: በቅዱሳን መሰወር ያምኑ ከሃዲዎች ክርስቲያኖች የተጠሉ ስለሆኑ በተዓምር በአቶሚክ ል አጠፋናቸው በማለት ማስተባበል ይቀጥላል:: በዚህም የብዙ ሰዎች በሐዘን ይመታል:: ስለሆነም የመዳን ቀን የጥንካሬ ቀን ዛሬ ነውና ችንን እንመርምር:: እንጠንቀቅ:: ወደ ፈተና እንዳንገባ ተግተን ፀልይ::